ESD

# ኢዱኬሽን ፎር ሰስተነብል ዲቨለፕመንት

## የቅድመ መደበኛ መምህራን ስልጠና ሥርዓተ ትምህርት

ሕዳር 2007 ዓ.ም.

ማውጫ


ክፍል አንድ ........................................................................................ 1

1.መግቢያ ........................................................................................ 1

2.የሥርዓተ ትምህርቱ አጠቃላይ ዓላማዎች ........................................................................................ 2

3.የማሠልጠኛ ዘዴዎች ........................................................................................ 2

4.የክፍለ ጊዜ ሥርጭት ........................................................................................ 4

5.የኮርስ ስርጭት ማብራሪያ ........................................................................................ 5

6.የምልመላ መስፈርት ........................................................................................ 6

7.የሥርዓተ ትምህርቱ አጠቃቀም ........................................................................................ 6

ክፍል ሁለት ........................................................................................ 7

I. ከሙያ ጋር የተያያዙ የትምህርት ዓይነቶች ........................................................................................ 7

1. የሕፃናት ዕድገትና መዳበር ........................................................................................ 7

2.የቅድመ መደበኛ ሥነ - ትምህርት ........................................................................................ 18

3.የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት አደረጃጀትና አመራር ........................................................................................ 30

4.ጤናና ሥርዓተ -ምግብ ........................................................................................ 38

5.የልዩ ፍላጎት ትምህርት ........................................................................................ 45

II. በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ከሚከናወኑ ተግባራት ጋር የተያያዙ ትምህርቶች ........ 50

7.ጨዋታ ........................................................................................ 50

8. የአካባቢ ትምህርት ........................................................................................ 59

9.የሕጻናት ቋንቋ መዳበር ........................................................................................ 64

10.የሥነ- ስእልና ቅርፃ ቅርፅ ትምህርት ........................................................................................ 71

11.ቅድመ ሂሳብ ........................................................................................ 77

12.የሙዚቃ ትምህርት ........................................................................................ 82

13.የሰውነትማጎልመሻ ትምህርት ........................................................................................ 88

14. መሠረታዊ የኮምፒውተር ትምህርት ........................................................................................ 93

15. የመጫወቻና መርጃ መሣሪያዎች ........................................................................................ 99

16.ፕራክቲክም ........................................................................................ 101

# ክፍል አንድ

## 1.መግቢያ

ለራሳቸውም ሆነ ለሀገር የሚጠቅሙ ዜጎችን የማዘጋጀት ተግባር መሠረት የሚጣለው በለጋ ህፃንነት ዕድሜ እንደሆነ በርካታ የዘርፉ ምሁራን ይጠቁማሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ዕድሜ የአካል፣ የአዕምሮ የማህበራዊ ኑሮና የስሜት መዳበር መሠረት እንዲጣል ትኩረት መስጠት ችላ የማይባል ጉዳይ ነው፡፡በለጋ ህፃንነት ዕድሜአቸው ስለአካባቢ ሁኔታ የመረዳት ወይም አካባቢአቸውን የመተዋወቅ ዕድል ያገኙ ሕፃናት ተለዋዋጭ በሆነ የአካባቢ ሁኔታ እንኳን በቀላሉ ራሳቸውን ከሁኔታዎች ጋር የማዛመድ አቅም ይኖራቸዋል፡፡ የራሳቸውን ችግር በራሳቸው ለመፍታት ጥረት የማድረግ ዝንባሌም የሚታይባቸው ሲሆን ከአካባቢያቸው ማህበረሰብ ጋር የመግባባት የመተባበር ወ.ዘ.ተ. ችሎታቸውም እየዳበረ ይሄዳል፡፡ ስለዚህ በለጋ ህፃንነት ዕድሜ ለሚከናወኑ ተግባራት ልዩ ትኩረት በመስጠት ተገቢውን አቅጣጫ ይዘው እንዲሄዱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡  ይህ ዕድሜ ለደረጃው የሚገባውን መሠረት ይዞ እንዲሄድ በቀጣይም በመደበኛ ትምህርት ቤት ለሚካሄደው የተማሪነት ሕይወት እግዱ ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ እገዛ ከሚያደርጉ ተቋማት አንዱና ዋናው የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ነው፡፡

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ህፃናትን ማነቃቂያ ፣ ማበረታቻ ያላቸውን አቅም ተጠቅመው አባባቢን ለማወቅ የሚጥሩ ፣ የሚመራመሩና በህብረተሰቡ ተቀባይነት ያለው ማህበራዊ መስተጋብር ያላቸው እንዲሆኑ ዕገዛ የሚያደርግ ነው፡፡  ይህንን ለማድረግ በተቋሙ የሚሰሩ መምህራን የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ስለሆነ መምህራን የሕፃናትን ዕድገትና ባህሪ የሚያውቁ ፣ የዕድገት ለውጦቻቸውን የሚረዱ፣ በአካል፣ በአዕምሮ፣ በማህበራዊ ኑሮ እና በስሜት ሕፃናትን የማዳበር ችሎታ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡ መምህራን ሕፃናትን ሲቀበሉ ያላቸው ኃላፊነት ከፍተኛ ነው፡፡  ለሕፃናት ሁሉንም ሆነው ሊንከባከቡአቸው የሚችሉ እንደሆኑም ይታሰባል እንደ እናት በፍቅር መንከባከብ ፣ ማነቃቃት ፣ ማዝናናት ፣ ማስደሰት በዕድሜአቸው ሊደርሱ በሚችሉበት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህን ለማድረግ የአፀደ ሕፃናት መምህርነት ሙያን በጥልቀት ማወቅ ያስፈልጋቸዋል ስለዚህ የሕፃናት መምህራን ስልጠና መምህራን ለጋ ሕፃናትን ተቀብለው በተገቢ አቅጣጫ ማዳበርና ለመደበኛ ትምህርት ቤት የተማሪነት ህይወት ማብቃት እንዲችሉ እጅግ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ አጠያያቂ አይሆንም፡፡

ይህ የቅድመ መደበኛ መምህራን ስለጠና ሥርዓተ ትምህርት ከላይ የተጠቀሱትን ሊያሟሉ የሚችሉ መምህራንን ለማሰልጠን እንዲቻል ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ሥርዓተ-ትምህርቱ ዓላማዎቹን፣ የማሰልጠኛ ዘዴዎችን፣ የእጩ መምህራን መመልመያ መስፈርቶችን ፣ የክፍለ ጊዜ ስርጭትን፣ የትምህርቶቹን ዝርዝር ሂደት በሠንጠረዥ አካቶ ተዘጋጅቷል፡፡

## 2.የሥርዓተ ትምህርቱ አጠቃላይ ዓላማዎች

- እጩ መምህራን ስለ ሕፃናት ዕድገትና መዳበር ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ጤናማና ደረጃውን የጠበቀ ዘላቂነት ያለው የሕፃናት መዳበርን ማምጣት የሚችሉ እንዲሆኑ ለማድረግ፣
- ስለ ቅድመ መደበኛ አስተዳደግና ትምህርት አሰጣጥ ተገቢ እውቀትና ክህሎትን አዳብረው የቅድመ መደበኛ መርሀ- ትምህርትን በተግባር ላይ የማዋል ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ፣
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት አደረጃጀትና አመራርን ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ሊደረግ የሚገባውን ግኑኝነት ተረድተው ተቋሙን የማደራጀት፣ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር የመሥራት ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ፣
- ስለጤናና የተመጣጠነ ምግብ እና ስለመጀመርያ ዕርዳታ አሰጣጥ ግንዛቤ ጨብጠው ሕፃናትን የመንከባከብ ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ፣
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም መከናወን ያለባቸውን የየዕለት ተግባራት ተረድተው የማቀድ፣ የመተግበርና የሕፃናትን መዳበር የመመዘን ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ፣
- ልዩ እንክብካቤና ትምህርት እለሚያስፈልጋቸው ሕፃናት ግንዛቤ እንዲጨብጡና አስፈላጊውን ዕርዳታ የማድረግ ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ፣
- ስለመጫወቻዎችና መርጃ መሳሪያዎች አስፈላጊነት ዓይነትና አዘገጃጀት ግንዛቤ ጨብጠው የማዘጋጀትና የመጠቀም ክህሎት እንዲኖራቸው ለማድረግ
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ምልከታና የማስተማር ልምምድ በማድረግ የተማሩትን በተግባር ላይ የማዋል አቅማቸው እንዲዳብር ለማድረግ ናቸው፡፡

## 3. የማሠልጠኛ ዘዴዎች

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ዋና ትኩረት የቀለም ትምህርቶችን ማስተማር ላይ ሳይሆን ሕፃናት በአካል በአዕምሮ ፣ በማህበራዊ ኑሮ በስሜት ታንፀው ለመደበኛ ትምህርት ቤት የተማሪነት ሕይወት እንዲዘጋጁ ማድረግ ነው፡፡ ይህም የሚከናወነው ሕፃናትን ባማከለ አሳታፊ ዘዴ ሊሆን ይገባል፡፡

መምህራን ሚያስተምሩ የሚችሉት እነርሱ በተማሩበት መንገድ እንደሆነ ይነገራል፡፡ እጩ መምህራን በገለፃ ብቻ ከተማሩ ይህንኑ በተማሪዎቻቸው ላይ ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ይታመናል፡፡ ስለዚህ ውጤታማ ስልጠና ለመስጠትና የሕፃናት መምህራን በሥራ ዓለም ላይ ተገቢውን ዘዴ እንዲጠቀሙ ለማድረግ አሳታፊ የሆነ የማስተማር ዘዴንና ተሞክሮዎችን በመጠቀም ማስተማር ከአሰልጣኞች ይጠበቃል፡፡

በዚህ ስልጠና በአብዛኛው በተግባር ላይ ያተኮረ ዘዴዎች ከንድፈ ሐሳብ ጋር ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ እጩ መምህራን በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ሊጠቀሙባቸው የሚገቡትን ዘዴዎችም በተግባር እንዲመለከቱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በክፍል ውስጥ ገለፃ፣ የትንንሽና ትልልቅ ቡድን ሥራዎች በግል የሚሰሩ የክፍልና የቤት ሥራዎች፣ የርስ በርስ መማማር ፣ የተለያዩ የማስተማሪያ ናሙናዎችን ማሳየትን፣ የፕሮጀክት ሥራዎችን እንዲያዘጋጁና እንዲያቀርቡ ማድረግን አሰልጣኝ መምህራን ሊጠቀሙ ይገባል፡፡ ተማሪዎች አብሮ ለመማር ዝግጁ የሆነና ሙከራዎቻቸውን የሚደግፍ መምህርን ያከብራሉ ይወዳሉም ስለዚህ አሰልጣኝ መምህራን በተቻለ መጠን ተማሪዎቻቸው ወደ ስራ ቦታቸው ሲሄዱ እንዲሆኑ የሚፈልጉትን ሆነው በማሳየት ተማሪዎቻቸውን ቢያነቃቁ የድካማቸውን ውጤት በተሻለ መልኩ የማየት ዕድል ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡

እጩ መምህራን ያዘጋጁአቸውን የማስተማሪያ ማሳሪያዎች በመጠቀም እርስ በርስ መማማርን እንዲለማመዱ ማድረግና ያዩትን መገምገምን ማለማመድ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራበት የሚያስፈልግ ዘዴ ነው፡፡ የመማር ማስተማሩ ሂደት በተለያዩ መርጃ መሳሪያዎች ማለትም ፖስተሮች ፣ ቻርተሮች ፣ ስላይዶች፣ ቪዲዮ ፊልሞች ፣ የሕፃናት መጫወቻዎችና መርጃ መሳሪያዎች ሊደገፍ ይገባል፡፡

እጩ መምህራን በክፍል ተሳትፎ፣ በቡድንና በግል ሥራዎች፣ በፕሮጀክቶት፣ ሙከራዎችና የማጠቃለያ ፈተናዎች መመዘን አለባቸው፡፡ ስለዚህ አሰልጣኝ መመህራን የእጩ መምህራንን ውጤት ለማጠቃለል ከላይ የተጠቀሱትን በማድረግ ተከታታይ ምዘናን መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

ፕራክቲከም/ ምልከታና የማስተማር ልምምድ/ እጩ መምህራን የተማሩትን በመስክ ላይ የሚያዩበትና የሚሞክሩበት ፕሮግራም ነው ስለዚህ መምህራን የተለያዩ ለምልከታ የሚረዱ ጥያቄዎችን በመስጠት የተሻለ የልምምድ ወይም የምልከታ ጊዜ እንዲኖራቸው በማድረግ ቢተባበሩ የተሻለ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ይታመናል፡፡

## 4.የክፍለ ጊዜ ሥርጭት

| ተ.ቁ. | የኮርስ መጠሪያ | በሳምንት የተፈቀደ ጊዜ | የክፍለ ጊዜ ብዛት |
|---|---|---|---|
| | **I. ከሙያ ጋር የተያያዙ ኮርሶች** | | |
| 1 | የሕፃናት ዕድገትና መዳበር | 3 | 60 |
| 2 | የቅድመ መደበኛ ሥነ-ትምህርት | 3 | 60 |
| 3 | የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት አደረጃጀትና አመራር | 2 | 40 |
| 4 | ጤናና ሥርዓተ ምግብ | 2 | 40 |
| 5 | የልዩ ፍላጎት ትምህርት | 2 | 40 |
| 6 | መሰረታዊ የኮምፒዩተር ትምህርት | 2 | 40 |
| | **II በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ከሚከናወኑ ተግባራት ጋር የተያየዙ ኮርሶች** | | |
| 7 | ጨዋታ | 2 | 40 |
| 8 | የአካባቢ ትምህርት | 2 | 40 |
| 9 | የሕፃናት ቋንቋ መዳበር | 2 | 40 |
| 10 | ሥነ-ሥዕልና ቅርፃ ቅርፅ | 2 | 40 |
| 11 | ቅድመ ሂሳብ | 2 | 40 |
| 12 | ሙዚቃ | 2 | 40 |
| 13 | የሰውነት ማጎልመሻ | 2 | 40 |
| 14 | የመጫወቻና መማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት | 3 | 60 |
| | **III. የቀለም ትምህርቶች** | | |
| 15 | የእንግሊዝኛ ቋንቋ | 2 | 40 |
| 16 | የአማርኛ ቋንቋ | 2 | 40 |
| | **ጠቅላላ** | **35** | **700** |
| | **IV ፕራክቲከም** | | |
| | ፕራክቲከም አንድI | በወር 1 ቀን | በ3 ወራት 3 ቀናት |
| | ፕራክቲከም ሁለት | 2 ሳምንታት በተከታታይ | |

## 5.የኮርስ ስርጭት ማብራሪያ

እጩ መምህራን በስድስት ወራት ቆይታቸው የሚማሩአቸው ኮርሶች በአራት አቅጣጫ የተከፋፈሉ ናቸው፡፡

1. የእጩ መምህራንን ሙያዊ እውቀት ለማዳበር የሚሰጡ ኮርሶች፣
2. በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ከሚከናወኑ የተለያዩ ተግባራት ጋር የተያያዙ ኮርሶች
3. የእጩ መምህራንን የቋንቋ ችሎታ ለማዳበር የሚሰጡ የቋንቋ ትምህርቶች
4. በፕራክቲከም ላይ ያተኮሩ ተግባራት ሲሆኑ
    - ፕራክቲከም አንድ እጩ መምህራን ከቅድመ መደበኛ ተቋም እና ሥራው ጋር ለመተዋወቅ ምልከታ የሚያደርጉበት ሲሆን በመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት በወር አንድ ቀን (ባጠቃላይ ሦስት ቀናት) በቅድመ መደበኛ ትምህራት ቤት በመገኘት ምልከታ የሚያደርጉበት ይሆናል፡፡
    - ፕራክቲከም ሁለት እጩ መምህራን በሁለተኛዎቹ ሦስት ወራት ከማጠቃለያ ፈተና በፊት ለሁለት ተከታታይ ሳምንታት አፀደ ሕፃናት በመመደብ የማስተማር ልምምድ የሚያደርጉበት ይሆናል፡፡

ሥርዓተ ትምህርቱ የተዘጋጀው ለ24 ሳምንታት ሲሆን ሳምንታቱ እንደሚከተለው ተከፋፍለዋል፡፡

1.የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት

- 10 ሳምንታት የትምህርት ጊዜ
- 3 ቀናት (በወር አንድ ጊዜ) በአፀደ ሕፃናት ምልከታ (ፕራክቲከም አንድ) ይካሄዳል፡፡
- የመጨረሻው አንድ ሳምንት የዕረፍት ጊዜ ይሆናል፡፡

2.ሁለተኛዎቹ ሦስት ወራት

- 9 ሳምንታት የትምህርት ክፍለ ጊዜ
- 2 ሳምንታት ፕራክቲከም ሁለት
- 1 ሳምንት የማጠቃለያ ፈተና ይሆናል፡፡

## *6.የምልመላ መስፈርት*

6.1. 10ኛ ወይም 12ኛ ክፍልን ያጠናቀቁ በበሔራዊ ፈተና 1.57 እና በላይ ውጤት ያላቸው

6.2. ሥልጠናው የሚካሄድበትን ቋንቋ መረዳት ፣ መናገርና መፃፍ የሚችሉ

6.3 የአካልም ሆነ የአዕምሮ በሽታ የሌለባቸው

6.4 ከህፃናት ጋር ለመሥራት የሚያስችል የስብዕና ባህርያትን የተላበሱ

## *7.የሥርዓተ ትምህርቱ አጠቃቀም*

በዚህ ሥርዓተ ትምህርት ከኮርስ ድልድል በላይ ለእያንዳንዱ ኮርስ (የትምህርት ዓይነት) ርዕስ፣ ዓላማ፣ ይዘት፣ የክፍለ ጊዜ ድልድል ፣ የማስተማሪያ ዘዴዎች፣ የመርጃ መሳሪያ ፣ እና የምዘና ዘዴ በሠንጠረዥ ተቀምጠዋል በተጠቀሱት ክፍሎች የተቀመጡት ሐሳቦች በተለይ የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመርጃ መሳሪያዎች ለሚመለከተው ሰው አቅጣጫ ለመጠቆም የተቀመጡ ናቸው። አሰልጣኝ መምህራን የራሳቸውን ፈጠራ በመጠቀም ርዕሱን የተሻለ ላስተላልፍበት ወይም ለተማሪዎች ላስጨብጥበት እችላለሁ የሚሉትን መንገድ ጨምረው መጠቀም ይችላሉ።

የማስተማሪያ ዘዴን በተመለከተ ዋናው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነገር የእጩ መምህራን ተሳትፎ እንደሆነ ከዚህ በፊት በፊት ገፆች ተጠቀሷል። እጩ መምህራንን ለማሳተፍ የትንንሽና ትልልቅ ቡድኖችን ውይይትና ዕብረቃን መጠቀም ጥሩ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ በቡድን ውስጥ ሊሸፈኑ (ላይመዘኑ) የሚችሉ ተማሪዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ የቡድን ሥራን በተቻለ መጠን የቡድኑ አባላት እየተሳተፉበት የሚንፀባረቅበትን ሁኔታ ማመቻቸት የሚጠቅም ይሆናል።

ክፍለ ጊዜን በተመለከተ ለየርዕሶቹ የተቀመጡት ጊዜአት እንደመምህሩ አጠቃቀም በመጠኑ ማሻሻያ ሊደረግባቸው ይችላል። ይህ በሚደረግ ጊዜ ግን የተቀመጠሙን ርዕስ ለመሸፈን የማይበቁ ወይም የሚበዙ እንዳይሆኑ ፣ ለኮርሱ ከተቀመጠው አጠቃላይ ክፍለ ጊዜ ብዛት በላይ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።በምዘና ዘዴዎች ላይ ለጥቆማ ያህል የተቀመጡ የምዘና ሐሳቦች አሉ ሆኖም አሰልጣኝ መምህራን በክፍለ ጊዜ መጀመሪያ ፣ በትምህርቱ ሂደት እንዲሁም በክፍለ ጊዜው ማጠቃለያ የሚያቀርቡአቸው ለምዘና የሚረዱ ጥያቄዎች ስለሚኖሩ አብረው ይካሄዳሉ ወይም የተሻለ መመዘኛ ይሆናሉ። የሚሉአቸውን የተለያዩ ዘዴዎች መጠቀም ይችላሉ።

# ክፍል ሁለት

## *I. ከሙያ ጋር የተያያዙ የትምህርት ዓይነቶች*

## *1. የሕፃናት ዕድገትና መዳበር*

በሳምንትየተፈቀደ ጊዜ - 3

አጠቃላይ ዓላማዎች

ይህንን ኮርስ ካጠናቀቁ በኃላ እጩ መምህራን፡-

- የሕፃናት ዕድገትና መዳበርን መሠረታዊ ሐሳቦችና የጥናት አቅጣጫዎች ይገነዘባሉ፡፡
- በቅድመ ወሊድና ድህረወሊድ የመዳበር ደረጃዎች የሚታዩትን ለውጦችና ባህርያት ሲደረግ የሚገባውን እንክብካቤ ተገንዝበው አስፈላጊውን የማድረግ ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡
- ሕፃናትን የማጥኛ ዘዴዎችን በመገንዘብ የማጥናት ዝንባሌ ይኖራቸዋል፡፡
- የሕፃናትን የመዳበር ዘርፎች የሚያሳዩትን ለውጥና የሕፃናት ፍላጎቶች ተገንዝበው አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይችላሉ፡፡
- የልዩ ትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ሕፃናት ባህሪ በመረዳት ተገቢውን እንክብካቤና እርዳታ የማድረግ ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡
- ሕፃናት የተሟላ ዕድገትና መዳበር እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይችላሉ፡፡
- የሕፃናትን ዕድገትና መዳበር የመከታተልና የመገምገም ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡

**የኮርሱ ይዘቶች**

1. የሕፃናት ዕድገትና መዳበር

   1.1. የዕድገትና መዳበር መሠረታዊ ሐሳቦች

   - የትኩረት አቅጣጫዎች
   - የጥናቱ አስፈላጊነት

2. የሰው ልጅ ዕድገትና መዳበር

   2.1. የዕድገት ፣ የመዳበርና፣ የብስለት ትርጉም

   2.2. የዕድገትና መዳበር መርሆች

   2.3. በመዳበር ላይ ሚና የሚጫወቱ ሁኔታዎች

      2.3.1. ዘር

      2.3.2. አካባቢና አስተዳደግ

   2.4. የመዳበር ደረጃዎች

2.4.1. ቅድመ ወሊድ

2.4.2. ድህረ ወሊድ

3. የመዳበር ዘርፎች

3.1. የመዳበር ዘርፎች

3.2. የመዳበር ዘርፎችና እንክብካቤአቸው

3.2.1. የአካል መዳበርና እንክብካቤው

- በህፃንነት ዘመን
- በቀዳማይ ልጅነት ዘመን

3.2.2. የእንቅስቃሴ መዳበርና እንክብካቤው

- በሕፃንነት ዘመን
- በቀዳማይ ልጅነት ዘመን

3.2.3. የአዕምሮ መዳበርና እንክብካቤው

- በሕፃንነት ዘመን
- በቀዳማይ ልጅነት ዘመን

3.2.4. የቋንቋ መዳበርና እንክብካቤው

- በሕፃንነት ዘመን
- በቀዳማይ ልጅነት ዘመን

3.2.5. የማህበራዊ ኑሮ መዳበርና እንክብካቤው

- በሕፃንነት ዘመን
- በቀዳማይ ልጅነት ዘመን

3.2.6. የስሜት መዳበርና እንክብካቤው

- በሕፃንነት ዘመን
- በቀደማይ ልጅነት ዘመን

3.2.7. የክብረ ህሊና(የሞራል) መዳበር እንክብካቤው

- በሕፃንነት ዘመን
- በቀዳማይ ልጅነት ዘመን

4. በልጆች ላይ ጉልተው የሚታዩ ባህርያዊ ክስተቶች

4.1. ጨዋታ

4.2. ፍርሀት

4.3. ቁጡነት

4.4. እረፍተቢስነት

4.5. እምቢተኝነት

5. የወላጅ ተሳትፎ

5.1. የወላጆች ሚና

5.2. ወላጅን የማሳተፊያ መንገዶች

6. የሕፃናት መብቶች

6.1 የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን

6.2 የሕፃናት ጥቃትና ችላ መባል

7.የሕፃናትን እድገትና መዳበር ግምገማና ምዘና

7.1 የግምገማና ግምገማ ትርጉም

7.2 የምዘና መሳሪያዎች

7.3 የምዘና ቴክኒኮች

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | ክ/ጊዜ | የመምህር አቀራረብና የማስተማርያ ዘዴዎች | የመርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሕፃናት ዕድገትና መዳበር | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• የሕፃናት ዕድገትና መዳበርን የትኩረት አቅጣጫዎች ያውቃሉ፡፡<br>• የጥናቱን አስፈላጊነት ይገነዘባሉ | 1.1 የሕፃናት እድገትና መዳበር<br>• የትኩረት አቅጣጫዎች<br>• የጥናቱ አስፈላጊነት | 3 | - ስለሕፃናት ዕድገትና መዳበር ቀደም ሲል የነበራቸው መረጃ ምን እንደሆነ መጠየቅና ማወያየት<br>- የትኩረት አቅጣጫዎችን ማስረዳትና ማወያየት<br>- ስለ ሕፃናት ዕድገትና መዳበር ማወቅ ለምን እንደሚያስፈልግ<br>መጠየቅና ማወያየት | - መድሐፍት<br>- ለተማሪዎች ለመረጃነት የተዘጋጁ ፅሑፎች<br>- ፍሊፕ ቻርት ወይም ነጭ ሠሌዳ | - በተሳትፎአቸው የሚያንፀባርቁትን በማዳመጥ ምን ያህል እንደተረዱ መገመት |
| 2 | የሰው ልጅ ዕድገትና መዳበር | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• የዕድገትን ትርጉምና ባህርያት ይገነዘባሉ፡፡<br>• ዕድገት የልዩ ልዩ ዘርፎች ቅንጅት መሆኑን ይረዳሉ፡፡<br>• የመዳበርን ትርጉምና ባህርያት ይገነዘባሉ፡፡<br>• የብስለትን ትርጉም ይረዳሉ፡፡<br>• የመዳበር መርሆችን ይረዳሉ፡፡ | 2.1 የእድገት ትርጉምና ባህርያት<br>• እድገትን ሊያስገኙ የሚችሉ ሁኔታዎች<br>• የመዳበር ትርጉም<br>• የእድገትና መዳበር ህግጋት<br>• የብስለት ትርጉም | 5 | - እድገት (Growth) ምን እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት<br>- የእድገትን ትርጉምና ባህርያት ማስረዳት ቻርትን በመጠቀም እድገት ከየት ወደየት እንደሚሄድ ማሳየት ማወያየት<br>- የመዳበርን ትርጉም ከዕድገት ይለይ እንደሆነ መጠየቀና ማወያየት የመዳበርን ትክክለኛ ትርጉም ማስጨበጥና ከዕድገት ጋር የሚለይበትን ሁኒታ ማስረዳት<br>- ብስለት ምን ማለት እንደሆነ መጠየቅና ከዕድገትና ከመዳበር ጋር የሚለይበተን ነገር በ4 አባላት ቡድን እንዲወያዩና እንዲያንፀባርቁ ማድረግ ትክክለኛውን አቅጣጫ ማስያዝ | -የሳይኮሎጂ መጽሐፍ<br>- የእድገትን አካሄድ የሚያሳይ ቻርት<br>- ጥቁር ሠሌዳ<br>-ነጭ ሠሌዳ | - የእድገትና መዳበርን ትርጉም መጠየቅና መረዳታቸውን ማረጋገጥ<br><br>-የቡድን ፅብረቃቸውን በማየት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | ክ/ጊዜ | - የመምህር አቀራረብና የማስተማሪያ ዘዴዎች | የመርጃ መሣሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1.1. መዳበር መርሆች | 3 | - የመዳበር መርሆችን መስጠትና በትንንሽ ቡድን እንዲወያዩበት ማድረግ የተረዱትን ካንፀባረቁ በኋላ መርሆቹን ማስረዳት | | ምን ያህል እንደተረዱ መመዘን<br>- ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- በእድገታዊ ሳይኮሎጂ ስር ባሉት ርዕሶችና በዚህ ክፍል ባሉት ርዕሶች ላይ ሙከራ መስጠትና መመዘን |
| | | • በመዳበር ላይ ተፅዕኖ ስለሚያደርጉ ሁኔታዎች ግንዛቤን ይጨብጣሉ።<br>• በአካባቢና በዘር መካከል ያሉትን ልዩነቶች መገንዘብ ይችላሉ።<br>ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• የመዳበር ደረጃዎችን ይረዳሉ<br>• በየደረጃዎቹ የሚታዩትን አስፈላጊ ባህርያት ይለያሉ<br>• የየደረጃውን ለውጦች ይገነዘባሉ<br>• በየደረጃው ለውጦች ላይ ተፅዕኖ ሊያደርጉ የሚችሉ ሁኔትዎችን ይለያሉ | 2.3. በመዳበር ላይ ሚና የሚጫወቱ ሁኔታዎች<br>2..3.1 ዘር<br>2.3.2.. አካባቢ<br><br>2.4. የመዳበር ደረጃዎች<br>2.4.1 ቅድመ ወሊድ<br>• የፅንስ አጀማመር<br>• ፅንስ<br>• ቅሪት<br>• ሽል | 4<br><br>5 | - እርስ በርሳቸው በመተያየት እያንዳንዳቸው ልዩ እንዲሆኑ እንዲያስተውሉ ማድረግ ልዩነታቸው ከምን የተነሳ እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት<br>- የመዳበርን ትርጉም እንዲያስተውሉ ማድረግና በመዳበር ላይ ሚና ስለሚጫወቱ ዘርና አባባቢ (አስተዳዳግ) የተለያዩ በአካባቢ ሊታዩ የሚችሉ ምሳሌዎችን በመጠቀም ማስረዳትና ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ<br><br>- ስለ ሰው ልጅ መዳበር ደረጃዎች መጠየቅ ስለ ደረጃዎቹ ግልፅ ማብራሪያ መስጠት ስዕሎችን በማሳየት የእያንዳንዱን ደረጃ ምንነትና ባህሪ ማስረዳት | - የተለያዩ የፀጉር ቀለም የፊት ገፅታ ፣ ቁመት፣ ያላቸውን ሰዎች የሚያሳዩ ስዕሎች | - ጥያቄዎች በመጠየቅ የቡድን ሥራ ተሳትፎአቸውን በማየት ምን ያህል እንደተረዱ ማረጋገጥ |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | ክ/ጊዜ | የመምህር አቀራረብና የማስተማሪያ ዘዴዎች | የመርጃ መሣሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • በየደረጃው የሚታዩትን ለውጦች እንዲከሰቱ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን ይረዳሉ | • የአወላለድ ሂደት የቅድመ ወሊድ ወሳኝ ሁኔታዎች | 3 | - በየደረጃው ስለሚታዩ ለውጦች የቡድን ሥራ መስጠትና የደረጃውን ለውጦች እንዲገነዘቡ ማስረዳት ማወያየት<br>- በየደረጃው ለአደጋ ሊያጋልጡ የሚችሉ ሁኔታዎችን መጠየቅና ማወያየት<br>- የየደረጃው ለውጦች ላይ የቡድን ሥራ መስጠትና ከዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ጋር እንዲያገናዝቡ ማነቃቃት | -የቅድመ ወሊድ ደረጃዎችን የሚያሳዩ ስዕሎች ቻርቶች | -የቅድመ ወሊድ ደረጃዎችን በሙከራ እንዲመልሱ በማድረግ ውጤታቸውን መመልከትና ማረጋገጥ |
| | | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ላይ የሚገኙትን ወሳኝ ሁኔታዎች ይረዳሉ<br>• ትክክለኛውን የዕድገትና መዳበር ሂደት ይገነዘባሉ<br>- | 2.4.2. ድህረ ወሊድ<br>• የጨቅላነት<br>• የሕፃንነት<br>• የልጅነት<br>• የጉርምሳና<br>• የወጣትነት<br>• የጎልማሳነት<br>• የእርጅና ዘመን | 4 | - ሰው ከተወደ በኋላ የሚያፍባቸውን የዕድገት ደረጃዎች መጠየቅና በሕይወት ከሚያዩት ሁኔታ ጋር አያይዘው እንዲናገሩ በጥያቄ ማነቃቃት<br>- የድህረ ወሊድ ደረጃዎችን ማስረዳትና ዋና ዋና ለውጦቻቸውን በቡድን እነዲወያዩባቸውና እንዲያንፀባርቁ ማድረግ | - በተለያዩ ደረጃ ላይ ለውጦችን የሚያሳዩ ስዕሎች | - ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>- በቡድን ሥራ ላይ ተሳትፎአቸውን መመልከትና መረዳታቸውን ማረጋገጥ<br>- ሙከራ መስጠት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | ክ/ጊዜ | የመምህር አቀራረብና የማስተማሪያ ዘዴዎች | የመርጃ መሣሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | የመዳበር ዘርፎች | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• የሕፃናት የመዳበር ደረጃዎችን በቅደም ተከተል ይረዳሉ፡፡<br>• የመዳበር ዘርፎችን የእያንዳንዳቸውን ምንነት መግለፅ ይችላሉ፡፡<br>• ለእያንዳንዱ የመዳበር ዘርፍ በጊዜው ዳብሮ መገኘት ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት ይገልፃሉ፡፡ | 3.1. የመዳበር ዘርፎች<br>• የአካል<br>• የእንቅስቃሴ<br>• የአዕምሮ<br>• የቋንቋ<br>• የስሜት<br>• የማህበራዊ ኑሮ<br>• የክብረ ህሊና (ሞራል) መዳበር | 3 | - ስለ ሰው ልጅ መዳበር ዋና ዋና ደረጃዎች መጠየቅ ማስታወስና መናገር እንዲችሉ ማነቃቃት<br>- የሕፃናት የመዳበር ዘርፎችን እንዲያስታውሱና እንዲናገሩ ማነቃቃት ሁለት ሁለት ሆነው እንዲነጋገሩና እንዲመልሱ መጠየቅ<br>- ሰባቱን የመዳበር ዘርፎችና ምን ላይ እንደሚያተኩሩ ሊዳብሩ የሚችሉባቸውን ተግባራት በጥቅሉ ማስረዳት<br>- የቅድመ መደበኛ ተግባራትን መጠየቅና ማወያየት<br>- የቀረበላቸውን መመሪያ መሠረት በማድረግ ቻርት እንዲሰሩ የቤት ሥራ መስጠት | - ቻርትን (ስለሰባቱ የመዳበር ዘርፎች ምንነት እና ሊደረግ ስለሚገባው እንክብካቤ) | - በቡድን ስለሰሩት በየግላቸው ጥያቄ በማቅረብ መረዳታቸውን ማረጋገጥ<br>- በየግላቸው ያዘጋጁትን ቻርት በማየት ያሉበትን የመረዳት ደረጃ ማረጋገጥ |
| 3.2 | የመዳበር ዘርፎችና እንክብካቤ አቸው | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን ፡-<br>• በህፃናትና በቀዳማይ ልጅነት ዘመን የመዳበር ለውጦች ከየመዳበር ዘርፎች አንፃር መረዳት ይችላሉ<br>• በየመዳበር ዘርፎቹ የሚታዩትን ለውጦች ላይ ሕፃናትን ለማድረስ ሊያደርጉ የሚገባቸውን እንክብካቤ ይገነዛባሉ፡፡ | 3.2.1 የአካል መዳበርና እንክብካቤው<br>• በህፃንነት<br>• በቀዳማይ ልጅነት ዘመን<br>3.2.2 የእንቅስቃሴ መዳበር እንክብካቤው<br>• በህፃንነት<br>• በቀዳማይ ልጅነት ዘመን<br>3.2.3 የአዕምሮ መዳበርና እንክብካቤው<br>• በህፃንነት<br>• በቀዳማይ ልጅነት | 16 | • ቀደም ሲል በጥቅሉ የተዋወቁአቸውን የመዳበር ዘርፎች እንዲያስታውሱ ማድረግ<br>• የመዳበር ዘርፍን ምንነት በዘርፍ የሚታዩትን ለውጦች ሊደረግ የሚገባውን እንክብካቤ ካላቸው አጠቃላይ እውቀት አንፃር እንደወያዩበት ማድረግና ትክክለኛውን አቅጣጫ ማስያዝ<br>• እያንዳንዱን ዘርፍ ወደ ውይይት ከማምጣት በፊት አንብበው እንዲመጡ የቤት ሥራ መስጠት በክፍለ ጊዜው ሐሳባቸውን እንዲገልፁ ጥያቄዎች በመጠየቅ ማሳተፍ | - በቡድን ለሚሠራው ሥራ ናሙና ፎርማት<br>- የየዘርፎቹን መረጃ ለማጠናከር የሚያግዙ ስዕሎች<br>- ነጭ ሰሌዳ ወይም ፍሊፕ ቻርት ማርከሮች | - የተለያዩ ጥያቄዎች በመጠየቅ መመዘን<br>- የቡድን ሥራዎቻቸውን በቡድኑ አባላት ተሳትፎ እንዲያቀርቡ ማድረግና መመዘን |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 3.2.4 የቋንቋ መዳበርና እንክብካቤው<br>•በህፃንነት<br>•በቀዳማይ ልጅነት<br>3.2.5 የማህበራዊ መዳበርና እንክብካቤው<br>• በህፃንነት<br>• በቀዳማይ ልጅነት<br>3.2.6 የስሜት መዳበርና እንክብካቤው<br>•በህፃንነት<br>•በቀዳማይ ልጅነት<br>3.2.7 የክብረ ህሊና (ሞራል)መዳበር እንክብካቤው<br>• በህፃንነት<br>• በቀዳማይ | | • ስባቱንም የመዳበር ዘርፎች ከማወያየት በኋላ ሦስት አባላት ባሉበት ቡድን የተማሩትን በሠንጠረዥ ሠርተው እንዲያቃርቡ እንዴት እንደሚሠራ ፎርማቱን በማሳየት የቡድን ሥራ መስጠት<br>• የሚሰሩትን ሕፃናትን በአካባቢአቸው በመመልከት ፣ እናቶችን፣ አባቶችን በመጠየቅ በተጨባጭ ያለውን በመጨመር እንዲሠሩና እንዲያቀርቡ ማድረግ | | |
| 4 | | በልጅነት ዘመን ጐለተው የሚታዩ ባህርያዊ ክስተቶች | 1. ጨዋታ<br>2. ፍርሐት<br>3. ቁጡነት<br>4. እረፍተቢስነት<br>5. ምቢተኝነት | 5 | - ስለእያንዳንዱ በቡድን ሆነው በመወያየት የሚያውቁትን እንዲያንፀባርቁ ማድረግ<br>- የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴአቸው ከሚታዩ ሁኔታዎች(ምሳሌዎች) ጋር በሚዛመድ ስለ እያንዳንዱ ክስተት ማስረዳትና ማወያየት<br>- የእያንዳንዱን ባህርያዊ ክስተት ጥሩና ጥሩ ያልሆነ ጎን በቡድን እንዲወያዩ ከማድረግ በመልሳቸው ላይ በመደገፍ የባህርያቱን አመጣጥ ሊያደርግ የሚገባውን ነገር እንዲገነዘቡ ማስረዳት<br>- በፕራክቲከም ጊዜ የተጠቀሱትን ባህርያት እንዲከታተሉና ሪፖርት እንዲያቀርቡ ጥያቃዎች መስጠት | - የማስተማሪያ ፅሑፍ የባህሪያት አገላለፅን የሚያሳዩ ስዕሎች | - የተለያዩ ጥያቆዎች በመስጠት ግነዛቤአቸውን ማረጋገጥ<br>- የቡድን ሥራዎችን እንዲያቀርቡ ማድረግና መመዘን |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎች የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5<br><br>6. | የወላጅ ተሳትፎ<br><br>የሕፃናትመብቶች | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን ፡-<br>• የወላጆች ተሳትፎ በሕፃናት መዳበር ሂደት የሚጫወተውን ሚና ይረዳሉ<br>• የወላጆችን ግንዛቤ ማስፋትና እንዴት ግንኙነት መፍጠር እንዳለባቸው ይገነዘባሉ<br><br>.የሕፃናት መብቶችኮንቬንሽንን ይዘት ይረዳሉ ለተግባራዊነቱም መሳተፍ እንዳለባቸው ይገነዘባሉ .ስለ ጥቃትና ችላ መባልያለውን ሁኔታ ይረዳሉ መከላከልይችላሉ | 5.1. የወላጆች ሚና<br>5.2 ወላጅን የማሳተፊያ መንገዶች<br><br>6.1የሕፃናትመብቶች ኮንቬንሽን<br>6.2 የሕፃናት ጥቃትና ችላ መባል | 2<br><br>2 | -በመዳበር ላይ ሚና የሚጫወቱ ወይም አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ነገሮችን በቡድን እንዲያስተውሉ ማድረግ<br>-ስለ ወላጆች ሚና ማወያየት ማስረዳት<br>-የወላጆችን እውቀት ስለማስፋፊያና ግንኙነት ስለመፍጠሪያ መንገዶች ማስረዳት<br>-በፕራክቲከም I ላይ አፀደ ሕፃናት ውስጥ ወላጆች እንዴት እንደሚሳተፉ በመጠየቅ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግና ማወያየት<br>የሕፃናትመብቶችኮንቬንሽን አንብበውእንዲያቀርቡ የቡድን ሥራጥያቄዎች መስጠት፣ስለ ጥቃትናችላ መባል ማወያየት ማስረዳት | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- የወላጆች ተሳትፎን የሚያመለክቱ ለተማሪዎች የተዘጋጁ ጽሑፎች | - የተለያዩ ጥያቃዎች በመጠየቅ ሪፖርታቸውን በማየት ምን ያህል እንደተረዱ ማረጋገጥ |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | ክ/ጊዜ | የማስተማሪያ ዘደዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | የሕፃናትን ዕድገትና መዳበር ግምገማና ምዘና | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• የግምገማና ምዘናን ምንነትና አስፈላጊነት ይገነዘባሉ<br>• ለምዘና ተገቢ የሆኑ መሳሪያዎችን (ዘዴዎችን) መጠቀም ይችላሉ | -የግምገማና ምዘና ትርጉም<br>-የምዘና መሳሪያዎች<br>-የምዘና ቴክኒኮች | 3 | - በምዘና እና ግምገማ ምንነት መጠየቅና ማወያየት<br>- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ስለሚካሄደው ምዘና ዓይነትና ምን እንደሚመዘን ማስረዳት<br>- የምዘና መሳሪያዎችን በቡድን በመስጠት የአጠቃቀም ቴክኒኩን ማስረዳት<br>- እንዲሞክሩ የቤት ሥራ መስጠት | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- ለምዘና የሚሞሉ ፎርሞች ቼክ ሊስቶች | - የምዘና ዘዴዎቹን መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የቤት ሥራቸውን መመልከት |

## 2.የቅድመ መደበኛ ሥነ - ትምህርት

በሳምንት የተፈቀደ ጊዜ 3

አጠቃላይ የኮርሱ ዓላማዎች

ይህን ኮርስ ካጠናቀቁ በኋላ እጩ መምህራን

- የሥነ-ትምህርትን ትርጉምና መሠረታዊ ሐሳቦች ይገነዘባሉ፡፡
- የቅድመ መደበኛ ሥነ- ትምህርትን የጥናት አቅጣጫዎች ይረዳሉ፡፡
- ቀደምት ምሑራን ለቅድመ መደበኛ ትምህርት ያደረጉትን አስተዋጽኦ በመረዳት ጠቃሚ ልምዳቸውን በሥራ ላይ የማዋል ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡
- የቅድመ መደበኛ ትምህርትን ዓላማ፣ የሥራ ይዘትና የማስተማሪያ ዘዴዎች በመገንዘብ ሕፃናትን ያማከለ አሳታፊ ዘዴን መጠቀም ይችላሉ፡፡
- የሕፃናት ትምህርት አሰጣጥ ባህሪን በመገንዘብ ከህፃናት ዕድገት ደረጃ አንፃር ፕሮግራሞችን ማቀድ፣ ማዳራጀትና ሥራቸውን መገምገም ይችላሉ፡፡
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ-ትምህርትን በመገንዘብ ከአባባቢ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር መተግበር ይችላሉ፡፡
- ሕፃናትን ለመደበኛ ትምህርት ቤት የማዘጋጀት ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡ ወላጆችንም ማሳተፍ ይችላሉ፡፡

የኮርሱ ይዘቶች

1. የሥነ- ትምህርት መሠረታዊ ሐሳቦች

   1.1. የሥነ-ትምህርት ትርጉም

   1.2. ዲዳክቲክስ

   1.3. የኢትዮጵያ ትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ

2. የቅድመ መደበኛ ሥነ-ትምህርት

   2.1. የቅድመ መደበኛ ሥነ-ትምህርት ትርጉምና የጥናት አቅጣጫ

   2.2. በቅደመ መደበኛ ትምህርት የቀደምት ምሑራን አመለካከትና አስተዋፅኦ

      2.2.1. የፍሬድሪክ ዊልሀለም ፍሮብል ፍልስፍናና አስተዋፅኦ

      2.2.2. የዶክተር ማሪያ ሞንቴሶሪ ፍልስፍና እና አስተዋጽኦ

      - ፍልስፍና
      - የማስተማሪያ ዘዴና መርሆች
      - የማስተማሪያ መሣሪያዎች

      2.2.3. የቤተሰብ ዓይነቶችና የአስተዳደግ ዘይቤዎች

   2.3. የቅድመ መደበኛ አስተዳደግና ትምህርት ተቋማት

      2.3.1. የቅድመ መደበኛ አስተዳደግና ትምህርት ዓላማና ይዘቶች

      2.3.2. የቅድመ መደበኛ አስተዳደግና ትምህርት መርሆች

      2.3.3. ቤተ - ሕፃናት 1-3 ዓመት

      - ዓላማና የሥራ ይዘቶች
      - 1-3 ዓመት ያሉ ሕፃናት የመዳበር ለውጦችና ፍላጎቶች
      - የመንከባከቢያ ዘዴዎች

      2.3.4. አፀደ ሕፃናት /3-6 ዓመት/

      - የአስተዳደግና ትምህርት ዓላማና ይዘት
      - 3-6 ዓመት ያሉ ሕፃናት የመዳበር ለውጦችና ፍላጎቶች
      - የቤተ ሕፃናትና የአፀደ ሕፃናት ልዩነቶች

2.4. የሕፃናት ችሎታ ደረጃዎችና የማስተማሪያ ዘዴዎች
- የህፃናት ችሎታ ደረጃዎች
- ለየደረጃው ሊደረግ የሚገባው እንክብካቤ
- የማስተማሪያ ዘዴዎች
  - ማሳየት
  - ቃላታዊ
  - ተግባራዊ ዘዴ

3. የቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ትምህርት

3.1. የመርሀ-ትምህርቱ አወቃቀር
3.2. የመርሀ -ትምህርቱ ዓላማና ይዘት
3.3. የመርሀ-ትምህርቱ አጠቃቀም

4. የሕፃናት አስተዳደግና ትምህርት ዕቅድ

4.1. የዕቅድ አስፈላጊነት
4.2. የዕቅድ ዓይነቶች
- የዓመት
- የወር
- የዕለት
- የክፍለ ጊዜ ትምህርት ዝገጅት /ሌሰን ፕላን/

4.3. የትምህርት ዝግጅትና አቀራረብ

5. ሕፃናትን ለመደበኛ ትምህርት ቤት ማዘጋጀት

5.1. የመዘጋጀት ትርጉምና አስፈላጊነት
5.2. የማዘጋጀት አቅጣጫዎች
- አካላዊ
- አዕምሮአዊ
- ማህበራዊ
- ሥነ-ልቦናዊ

5.3. ከህፃናት የሚጠበቁ ክህሎቶች

6. የሕፃናት አስተዳዳግና ትምህርት ምዘናና ግምገማ

6.1. የምዘና አስፈላጊነት
6.2. የምዘና ትኩረት
6.3. የምዘና ዓይነቶች
6.4. የምዘና መሳሪያዎች

## የቅድመ መደበኛ ሥነ-ትምህርት

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎች ና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ ማሣሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሥነ-ትምህርት መሠረታዊ ሐሳቦች | ይህን ርዕስ ካጠናቀቁ በኂላ እጩ መምህራን ፡-<br>• የሥነ-ትምህርትን ትርጉምና ምን እንደሚያጠና መግለፅ ይችላሉ፡፡<br>• የዲዳክቲክስን ምንነትና ኤለመንቶች (ክፍሎች) ይነገዘባሉ፡፡<br>• የኢትዮጰያን ትምህርት ፖሊሲ ዓላማዎች ይረዳሉ<br>• በሙያቸው (ከህፃናት) ጋር ግንኙነት ያላቸውን አንቀፆች ለይተው ማውጣት ይችላሉ፡፡ | 1.1. የሥነ -ትምህርት ትርጉም<br>1.2. ዲዳክቲክስ<br>• የዲዳክቲክስ ኤለመንቶች<br>• የዲዳክቲክ መርሆች<br>1.3. የኢትዮጵያ ትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ | 1<br>2<br>2 | - ሥነ -ትምህርት ምን የሚያጠና ትምህርት እንደሆነ እንዲያስቡ መጠየቅና ማወያየት ሥነ- ትምህርት -ፔዳጉጂ የሚለውን ቃል አመጣጥ በመጠኑ ማስረዳትና ሀሳብ እንዲኖራቸው ማድረግ<br>- የዲዳክቱክስን ምንነት መጠየቅና ማወያየት ስለኢለመንቶቹና መርሆች ማስረዳት ለመማር ማስተማር ያለውን ፋይዳ እነዲገነዘቡ ማድረግ<br>- ቤተ መፃሕፍት በመግባት የትምህርት ፖሊሲን አንብበው አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎቹን እንዲጽፉ ፣ አፀደ ሕፃናትን በሚመለከት የተጠቀሱትን ነጥቦች ለይተው እንዲያወጡ የቤት ሥራ መስጠትና ማወያየት | - የሥነ -ትምህርት መፃሕፍት<br>- የኢትዮጵያ ትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ዶክመንት | - የተለያዩ ጥያቄዎች በመጠየቅ ምን ያህል እንደተረዱ ማረጋገጥ<br>-የቤት ሥራ መስጠት<br>-ሙከራ መስጠትና መገምገም |
| 2 | የቅድመ መደበኛ ሥነ -ትምህርት | ይህን ርዕስ ካጠናቀቁ በኂላ እጩ መምህራን<br>• የቅድመ መደበኛ ሥነ-ትምህርትን ትርጉምና የጥናት አቅጣጫ ይረዳሉ፡፡<br>ከስነ ትምህርት ጋርያገናዝባሉ | 2.1. የቅድመ መደበኛ ሥነ-ትምህርት ትርጉም<br>• የጥናት አቅጣጫ | 2 | - የሥነ -ትምህርትን ምንነት የሚያጠናውን እንዲያስታውሱ በማድረግ የቅድመ መደበኛ ሥነ-ትምህርትን ትርጉምና የጥናት አቅጣጫ ማስረዳት ማወያየት | -የቅድመመደበኛ ሥነ-ትምህርት (Pre-School pedagogy) ጽሑፎች | - በውይይት ሂደት መጀመሪያ ማጠቃለያ ላይ የተለያዩ ጥያቄዎችን |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ ማሣሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን:-<br>የቅድመ መደበኛ ተቋማትንምንነት ይረዳሉ<br><br>• የቅድመ መደበኛ ት/ቤት አስተዳደግና ትምህርት ዓላማና ዋና ዋና ይዘቶችን ይገነዘባሉ<br><br>• የሕፃናት አስተዳዳግና ትምህርት መርሆች<br><br>• የቤተ-ሕፃናትን (Nursery, Day care …) ምንነት ዓላማና የሥራ ይዘት ይረዳሉ፡፡ | 2.5. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት<br><br>2.5.1. የቅድመ መደበኛ ት/ቤት አስተዳደግና ትምህርት ዓላማና ይዘቶች<br>2.5.2. የሕፃናት አስተዳደግና ትምህረት መርሆች<br><br>2.5.3. ቤተ-ሕፃናት<br>- ዓላማና የሥራ ይዘት | 2<br><br>2<br><br>3<br><br>3 | - የሕፃናት እንክብካቤ ስለሚካሄድባቸው ተቋማት የሚያውቋቸውን እንዲናገሩ በማድረግ ማወያየት ማስረዳት<br>-የቅድመ መደበኛ ተቋም ዓላማን ከሳይንሱና በተለምዶ ከሚገመተው አንፃር እንዲናገሩ ማድረግና ትክክለኛውን ዓላማ ማስረዳት<br>-ዓላማውን ከመተግበር አንፃር በቅድመ መደበኛ ተቋማት ምን እንደሚደረግ መጠየቅና ማወያየት ትክክለኛውን ግንዛቤ ማስጨበጥ<br>- የሕፃናት አስተዳዳግና ትምህርት መርሆችን በቅደም ተከተል ማስረዳትና ከዲዳክቲክ መርሆች ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት በመጠየቅ ማወያየት ትክክለኛውን ግንዛቤማስጨበጥ<br><br>-እስከ 3 ዓመት ያሉ ሕፃናት እንክብካቤ የሚደረግባቸውን ቦታዎች አይተው ያውቁ እንደሆነ ምን ተብለው እንደሚጠሩ መጠየቅና ማወያየት ቤተ-ሕፃናት ምን እንደሆኑ ዓላማቸውንና የሥራ ይዞታቸውን ማስረዳት፣ | -መፃህፍት<br>-የተለያዩ የቅ.መደበኛ ተቋማትየሚ ያሳዩ ስዕሎች/ፎቶ ግራፎች/<br>- የቤት-ሕፃናትን አደረጃደት የሚያሳዩ ስዕሎች<br><br>- መጽሐፍት<br><br>- የአፀደ ሕፃናትን ገፅታ የሚያሳዩ ስዕሎች ወይም ፎቶግራፎ ች<br><br>የአፀደ ሕፃናትን የውስጥ አደረጃጀት የሚያሳዩ ስዕሎች | - የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መረዳታቸውን ማረጋገጥ<br>- መርሆችን የያዙ ጽሑፎችን በቡድንበማደል በመርሆቹ ላይ ያላቸውን መረዳት እንዲናገሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና መመዘን<br>- የቡድን ሥራ ሲያቀርቡ መከታተልና ግንዛኤቸውን ማረጋገጥ በ2.5 ማጠናቀቂያ ሙከራ መስጠት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ ማሣሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን፡-<br>• የቀደምት ምሑራንን አመለካከት ይረዳሉ<br>• የፍሬድሪክ ዊልሀለም ፍሮብልንና የዶክተር ሞንቶሶሪን ፍልስፍና ይረዳሉ፡፡<br><br>• የሁለቱንም ምሑራን አመለካከት የማስተማር ዘዴ የመርጃ መሣሪያዎች በመረዳት ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታና ከህፃናት ዕድገተና መዳበር ጋር በማገናዘብ መጠቀም ይችላሉ፡፡<br><br>• የቤተሰብ ዓይነቶችንና የአስተዳደግ ዘይቤዎችን በመረዳት ተገቢውን መንገድ መከተል ይችላሉ፡፡ | 3.2. በቅድመ መደበኛ ትምህርት የቀደምት ምሑራን አመለካከትና አስተዋፅኦ<br>3.2.1. ፍሬድሪክ ዊልሀለም ፍሮብል ፍልስፍናና አስተዋጽኦ<br>3.2.2. የዶክተር ምሪያሞንቴሶሪ ፍልስፍና እና አስተዋፅኦ<br>• ፍልስፍና<br>• ዘዴዎችና መርሆች<br>• የመርጃ መሣሪያዎች የመምህር ሚና<br>3.2.3. የቤተሰብ ዓይነቶችና የአስተዳደግ ዘይቤዎች | 2<br><br>4<br><br>6<br><br>2 | -የቅድመ መደበኛ ሥነ-ትምህርት ጥናትን መጠየቅና ማስረዳት<br>-የቀደምት ምሑራንን አመለካከት ከኖሩበት ዘመን ጋር በማገናዘብ ማስረዳት (ፕላቶ አርስቶትል ኩንቲሊየን፣ ሉክ፣ ሩሶ፣ ፔስታሎሲ ለዘመኑ ባለው ፋይዳ ላይ ማወያየት<br>-የፍሬድሬክ ዊልሀለም ፎሮብልን ማንነት ፍልስፍና፣ ስጦታዎች፣ አስተዋጽኦ ማስረዳት ፣ ማሳየትና ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ለዘመናችን ያለውን ፋይዳ በቡድን እንዲወያዩበትና እንዲያቀርቡማድረግ፣በስጦታዎችማጫወ<br>-የዶክተር ማሪያሞንቴሶሪን ማንነት ፣ፍልስፍና ዘዴዎች የመርጃ መሣሪያዎችን ማሳየት ማስረዳትና ማወያየት<br>-ፕራክቲከም አንድ ላይ ለምልከታ ሲወጡ መሣሪያዎቹን እንዲያዩ ፣ ምን ያህል እንደሚጠቀሙበት በማስተዋልና በመጠየቅ ሪፖርት እነዲያቀርቡ ማድረግ<br><br>አስተዳደግ ላይ ያተኮሩ አባባሎችን በመጠየቅ ማወያየት ስለ ቤተሰብ ዓይነቶችና ዘይቤዎች ማስረዳትና ተገቢውን ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ | -የቅድመ መደበኛ ሥነ-ትምህርት መድሐፍት (ሞጁውል)<br><br>-የፍሮብል ስጦታዎች (መጫወቻዎች)<br><br>-የማርያሞንቶሶሪ ማስተማሪያ መሣሪያዎች<br><br>የማስተማሪያ ፅሁፍ | በመጠየቅ ግንዛቤአቸውን መመዘን<br>- የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ መረዳታቸውን ማረጋገጥ<br>- በመሣሪያዎቹ ሲጫወቱ በማየት ምን ያህል የአቀርረብ ዘዴቻቸውንእን እንደተረዱ ማየትና ማረጋገጥ<br>- የቡድን ሥራ ውጤታቸውን መገምገም |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ ማሣሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • 1-3 ዓመት ያሉ ሕፃናትን የመዳበር ለውጦች፣ ፍላጎቶችና ዘዴዎች በመረዳት መንከባከብ ይችላሉ፡፡<br>1-3 ዓመት ያሉ ሕፃናትን ለመንከባከብ የሚጠበቅባቸውን የስብዕና ባህሪ ይገነዘባሉ፡፡<br><br>• የአፀደ ሕፃናትን ምንነት ይገነባሉ፡፡<br>• 3-6 ዓመት ያሉ ሕፃናትን የመዳበር ለውጦችና ፍላጎቶች ለይተው ያውቃሉ፡፡<br>• ቤተ - ሕፃናትና አፀደ ሕፃናት የሚለዩባቸውን ነገሮች ይረዳሉ፡፡ | - -1-3 ዓመት ያሉ ሕፃናት የመዳበር ለውጦችና ፍላጎቶች<br>- የአቀራረብ ዘዴዎች ከአሳዳጊዎች የሚጠበቅ የስብዕና ባህሪ<br><br>2.5.4. አፀደ ሕፃናት<br>• ምንነት<br>• የአስተዳደግና ትምህርት ዓላማና ይዘት<br>• 3-6 ዓመት ያሉ ሕፃናት የመዳበር ለውጦችና ፍላጎቶች | <br><br>5 | -1-3 ዓመት ያሉ ሕፃናት የመዳበር ለውጦችና ፍላጎቶችን በየዕድሜው ለይተው እንዲጽፉና እንዲያቀርቡ የቤት ሥራ መስጠት<br>-1-3 ዓመት ካሉ ሕፃናት ጋር ሊኖር የሚገባው አቀራረብ የመንከባከቢያ ቦታው አደረጃጀት ምን መምሰል እንዳለበት ማስረዳትና ማወያየት<br>-ከአሳዳጊ (መምህራን) ምን እንደሚጠበቅ በቡድን በመወያየት እንዲሰሩና እንዲያቀርቡ በማድረግ ግንዛቤ ማስጨበጥ<br>-አፀደ ሕፃናት ምን ዓይነት ተቋም እንደሆነ ከስንት እስከ ስንት ዓመት ያሉ ሕፃናትን እንደሚንከባከብ መጠየቅና ማወያየት፣<br>-የአፀደ ሕፃናትን ዓላማና የሥራ ይዘት በመጠየቅ ፕራክቲከም I ላይ ያዩትን እንዲናገሩ ማድረግና ማወያየት ስለ ዓላማው የቀለም ትምህርት ላይ ማተኮር ሳይሆን ቅድሚያ የሚሰጠው መዳበራቸው እንደሆነ ማስረዳት<br>-ከዓላማው አንፃር ምን ሊሰራ ይገባል ብለው እንደሚያስቡ መጠየቅና ማወያየት ፕራክቲከም አንድ ላይ ምን ሲሠራ እንዳዩ እንዲናገሩ ማድረግና ማወያየት | - | - በክፍል ትምህርት ሂደት የሚጠየቁ ጥያቄዎች<br>የቡድን ሥራ ይዘቶች አቀራረብ በማየትመገምገ ም |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴምና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ ማሣሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • የሕፃናት ችሎታ ደረጃዎችን ና ሊደረግላቸ ው የሚገባውን እንክብካቤ ይገነዘባሉ | • የቤተ-ሕፃናትና የአፀደ ሕፃናት ልዩነት<br><br>2.6. የሕፃናት ችሎታ ደረጃዎችና የማስተማሪያ ዘዴዎች<br><br>• የሕፃናት ችሎታ ደረጃዎች<br><br>• ለየደረጃው ሊደረግ የሚገባው እንክብካቤ<br><br>• የማስተማሪያ ዘዴዎች<br>-ማሳየት<br>-ቃላታዊ ዘዴ<br>-ተግባራዊ ዘዴ | 5 | - 3-6 ስላሉ ሕፃናት የመዳበር ለውጦችና ፍላጎቶች በየዕድሜው የሚታዩትን ጽፈው እንደመጡ የቤት ሥራ መስጠት<br>-ስለ አፀደ ሕፃናትአደረጃጀት መጠየቅና ማወያየት ከቤተ-ሕፃናት ይለይ እንደሆነ የሚለይበትን በቡድን ተወያይተው እንዲያንፀባርቁ ማድረግና ስለአደረጃጀት ልዩነት ለምን እንደሆነ ተገቢውን ግንዛቤ ማስጨበጥ<br>- ስለችሎታ መጠየቅና ማወያየት<br>-የሕጎሣት ችሎታ ደረጃዎች (የአቀባበል ደረጃዎች) ማስረዳትና ማወያየት በተለይ በሁለተኛውና በሦስተኛው ደረጃ ላይ የመገናኘት ምክንያቶችን ማስረዳትና ማወያየት<br>-በየደረጃው ላሉት ሊደረግ የሚገባውን እንከብካቤ መጠየቅ፣ ማወያየትና ማስረዳት<br>-ሕፃናትን እንዴት እንደሚማሩ መጠየቅና በአካባቢአቸው ያሉ ሕፃናት ምን ሲያደርጉ እንደተመለከቱ በመጠየቅ ማወያየት<br>-የሕፃናት መዳበር ከአዋቂ ሰዎች እንደሚለይ በማስታወስ ከሕፃናት ጋር ሲሰሩ ሊጠቀሙበት የሚገባው ዘዴ ሕፃን ተኮር መሆን እንዳለበትና | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br><br>- የተለያዩየመርጃ መሣሪያዎች | - ጥያቄዎች በመጠየቅ መረዳታቸውን ማረጋገጥ<br><br>- ናሙና ትምህርት እንዲያሳዩ ማድረግ<br><br>- ሙከራ መስጠት |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ ማሣሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ምን ማለት እንደሆነ ማስረዳት<br>- ሕፃናትን ስለማስተማሪያ ዘዴዎች እያንዳንዱን ዘዴ በቅደም ተከተል ማስረዳተና ለምን እንዴት እንደሚጠቀሙበት ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ<br>- የማስተማሪያ ዘዴዎችን እንዴት እንደሚጠቀሙባቸው በማስተማር ማሳየት | | |
| 3. | የቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ትምህርት | ከዚህ ትምህርት በኂላ እጩ መምህራን ፡-<br>• የቅድመ መደበኛ መርሃ-ትምህርትን አወቃቀር ይገነዘባሉ፡፡<br>• የመርሀ-ትምህርቱን ዓላማና ይዘት ቅንጅታቸውንም ይረዳሉ፡፡<br>• የመርሀ- ትምህርቱን አጠቃቀም በመረዳት በተግባር ላይ ማዋል ይችላሉ፡፡ | 3.1. የመርሀ-ትምህርቱ አወቃቀር<br>3.2. የመርሀ - ትምህርቱ ዓላማና ይዘት<br>3.3 የመርሀ ትምህርቱ አጠቃቀም | 4 | - መርሀ-ትምህርት ምን እንደሆነ መጠየቅና ማወያየት ምን እንደሆነ በማስረዳት ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ<br>- መርሀ-ትምህርቱን እንዲያድ በማድረግ ጥያቄዎች መስጠተና ከመግቢያው ጀምሮ በማንበብ በቡድን በራሳቸው ዓላማና ይዘቶቹን እንዲፈትሹና እንዲናገረ ማድረግ፡፡<br>- መርሀ-ትምህርቱን በመጠቀም ዓላማና ይዘቱን ማሳየት፣ ማስረዳተና ማወያየት<br>- የመርሀ-ትምህርቱን አጠቃቀም ከአወቃቀሩ ጋር በማዛመድ ማስረዳትና ለተቀመጡት ብቃቶች ርዕስ እንዲያዘጋጁላቸው የቤት ሥራ መስጠት፡- | - የቅድመ መደበኛ መርሀ -ትምህርት (በጊዜው በሥራ ላይ ያለው)<br>-ስለአወቃቀሩና አጠቃቀሙ የተዘጋጀ ጽሑፍ | - ርዕስ ለማውጣት ያደረጉትን ጥረት መመልከት<br>- ሙከራ መስጠት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴምና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ ማሣሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | የሕፃናት አስተዳደግና ትምህርት እቅድ | ከዚህ ትምህርትበኋላ እጩ መምህራን :-<br>• የእቅድን ምንነት እና አስፈላጊነት ይረዳሉ<br>• የእቅድ ዓይነቶችንና እረስበርስ ያላቸውን ግንኙነት ይገነዘባሉ። ማቀድና መተግባር ይለማመዳሉ ።<br>• የትምህርቶችን ዝግጅትና አቀራረብ ይረዳሉ። በተግባር ላይ ያውላሉ ። | 4.1 የእቅድ አስፈላጊነት<br>4.2 የእቅድ ዓይነቶች<br>- የዓመት<br>- የወር<br>- የዕለት እና ሌሰንፕላን<br>4.3 የትምህርቶች ዝግጅትና አቀራረብ | 5<br>4 | - ለዕለት ተዕለት ኑሮአቸው እቅድ በፅሑፍ አዘጋጅተው ያውቁ እንደሆነ መጠየቅና የእቅድ አስፈላጊነትን ማስረዳት<br>- የእቅድ ዓይነቶችን በቅደም ተከተል ማስረዳተና የእያንዳንዱን አዘገጃጀት ናሙና በማሳየት ማስረዳት እርስ በርስ ያላቸውን ግንኙነት ማስረዳት እንዲሞክሩ የቤት ሥራ መስጠትናበየግላቸው ናሙና እነዲሠሩ ማድረግ<br>- የትምህርት ዝግጅትና አቀራረብ ላይ ሊያወ የሚገባቸውን ነጥቦች ማስረዳተና እንዲሠሩ ማድረግ | - የእቅድ ናሙናዎች<br>- ስለዕቅድ የተዘጋጁ ጽሑፎች | -ጥያቄዎች መጠየቅ<br>-ሙከራ መስጠት<br>-ያዘጋጁትን የዓመት ፣ የወር፣ የዕለት፣ ደሌሰን ፕላን ናሙና መመልከት |
| 5. | የሕፃናትን ለመዳበኛ ትምህርት ቤት ማዘጋጀት | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• ለመደበኛ ትምህርት ቤት መዘጋጀትማለት ምን ማለት እንደሆነ ያውቃሉ<br>• የማዘጋጀትን አስፈላጊነት ይገነዘባሉ<br>• ለመደበኛ ት/ቤት የማዘጋጀት አቅጣጫዎችንና እርስ በርስ ያላቸውን ግንኙነት በመገንዘብ በማቀናጀት የመሥራት | 5.1 ለመደበኛ ትምህርት ቤት የመዘጋጀት ትርጉምና አስፈላጊነት<br>5.2 የማዘጋጀት አቅጣጫዎች<br>-አካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ<br>5.3 ከህፃናት የሚጠበቁ ክህሎቶች | 4 | - ለመደበኛ ትምህርት ቤት መዘጋጀት ማለት ምን እንደሆነ ወላጅ ምን እንደሚያስብ በመጠየቅ እንዲወያዩበት ማድረግ<br>- የመዘጋጀትን ትርጉም ማስረዳተና በተለምዶ ስለመዘጋጀት ክማባለው ጋር እንዲያወዳድሩ በማድረግ ማወያየት<br>- የማዘጋጀት አቅጣጫዎችን አካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ማህበራዊ ፣ስሜታዊ ዝግጅነትን እያንዳንዱን አቅጣጫ በማወያየት እንዲረዱና | -የማስተማራያ ጽሑፎች<br>-በርዕሱ ላይ የተዘጋጁ ጽሑፎች<br>-አፀደ ሕፃናት ውስጥና በመደበኛ ት/ቤት አንደኛ ክፍል ያሉ ልጆች ሲማሩ የሚያሳይ ቪዲዮ (ከተቻለ) | - በውይይት ሂደት ጥቅቄዎችን ማቅረብ<br>- የቡድን መልሶቻቸውን በየግል እነዲመልሱ ማድረግ ውጤታቸውን ማየት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ ማሣሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡<br>• ለመደበኛ ትምህርት ቤት ተዘጋጁ ከሚባሉ ሕፃናት ምን እንደሚጠበቅ በመረዳት ለሚፈለግባቸው ነገር የማዘጋጀት ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡ | | | እንዴት ከተባለው አቅጣጫ አንፃር ሊዘጋጅ እንደሚችሉ እንዲገነዘቡ ማድረግ<br>-በማዘጋጀት ሂደት ስለሚካፈሉ ባለ ድርሻ አካላትም ማስረዳት<br>-ተዘጋጀ ከሚባል ሕፃን የሚጠበቁ ነገሮችምን ምን ምንደሆኑ መጠየቅና በቡድን ተወያይተው እንዲመልሱ ማድረግ<br>-ትክክለኛውን የሚጠበቅ ነገር እንዲገነዘቡ ማድረግና ገንዛቤአቸውንተገቢ አቅጣጫ ማስያዝ፡፡ | | |
| 6 | የሕፃናት አስተዳደግና ትምህርት ምዘናና ግምገማ | ከዚህ ትምህርት በኋላ መምህራን፡-<br>• የምዘናን አስፈላጊነት ይረዳሉ፡፡<br>• የምዘና ትኩረቶች ነጥቦችን ያውቃሉ፡፡<br>• የምዘና ዓይነቶችን ይረዳሉ መሣሪያዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡ | 6.1. የምዘና አስፈላጊነት<br>6.2. የምዘና ትኩረቶች<br>6.3. የምዘና ዓይነቶች<br>6.4. የምዘና መሳሪያዎች | 2 | - ስለምዘና ምንነትና አስፈላጊነት መጠየቅ ማወያየት<br>- በቅድመ መደበኛ አስተዳደግና ትምህርት ምን እንደሚመዘን ትኩረቱ ምን ላይ እንደሆነ ማስረዳት<br>- ምን ምን ዓይነት ምዘናዎችን መጠየም እንደሚቻል የምዘና ዓይነቶችን መጠየቅና ማወያየት፣ ማስረዳት<br>- የምዘና መሳሪያዎችን ማሳየት በቡድን እንዲመለከቱ ማድረግ እንዴት እንደሚሞላ ማሳየት<br>- ለምዘና የምልከታን አስፈላጊነት ማስረዳት በፐራክቲከም I ስለ ምዘና ያዩትን እንዲናገሩ መጠየቅናተገቢውን ሐሳብ እንዲጨብጡ ማገዝ | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- የምዘና መሳሪያ ዎች<br>• ቅፆች /የተከታይ ምዘና መሙያዎች ወዘተ | -ጥያቄዎችመ ጠየቅና ማወያየት<br>- ሙከራ መስጠት |

## 3.የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት አደረጃጀትና አመራር

ለኮርሱ የተፈቀደው ጊዜ በሳምንት -3

የኮርሱ አጠቃላይ ዓላማዎች

ይህንን ኮርስ ካጠናቀቁ በኁላ እጩ መምህራን፦

- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶችን ዕድገት አጭር ታሪክ ይገነዘባሉ፡፡
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች አደረጃጀትና አመራር በመረዳት የግቢ፣ የክፍሎች አካባቢን ማደራጀትና መጠቀም ይችላሉ፡፡
- የሰው ኃይል አደረጃጀትን ፣ አመራረጥን፣ ተበርና ኃላፊነቶችን በመረዳት የማደራጀት ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡
- የመዛግብትን አስፈላጊነት ፣ አደረጃጀት በመገንዘብ በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ይችላሉ፡፡
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት እቅድን የማዘጋጀት ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡
- ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ተገቢውን ግንኙነት የማድረግ ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡

የኮርሱ ይዘቶች

1. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ዕድገት አጭር ታሪክ
   1.1. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ዕድገት
   1.2. የቅደመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ዕድገት በኢትዮጵያ
      - ፖሊሲ
      - መመሪያዎች
      - ሥርዓተ-ትምህርት
2. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት አደረጃጀት
   2.1. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ዓላማ
   2.2. የማቋቋሚያ አካባቢ ምርጫ
   2.3. የግቢ አደረጃጀት
   2.4. የመገልገያ ክፍሎች አደረጃጀት
   2.5. የቁሳቁስ ምርጫና አደረጃጀት
   2.6. የሰው ኃይል አደረጃጀት
3. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ዕቅድ
4. የመዛግብት አያያዝ
5. ከባለ ድርሻ አካላት ጋር የሚደረግ ግንኙነት
   5.1. አስፈላጊነት
   5.2. መንግስታዊ ና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር
   5.3. ከወላጆች ጋር

## የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት
## አደረጃጀትና አመራር

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህሩ አቀራረብ | የመረጃ ማሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ዕድገት አጭር ታሪክ | ከዚህ ትምህርት በኂላ እጩ መምህራን፡-<br>• በአጠቃላይ ስለ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ዕድገት ሐሳብ ይኖራቸዋል፡፡<br>• በኢትዮጵያ ስለ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ዕድገት ይረዳሉ፡፡<br>• በኢትዮጵያ ቀደም ሲል ስለነበሩ እና አሁን በሥራ ላይ ስላሉት መመሪያዎች ፣ ፖሊሲ ሥርዓተ ትምህርት ግነዛቤ ይኖራቸዋል፡፡<br>• ቀደም ሲል ከነበረውና አሆን ካለው የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ተሞክሮዎችን በመውሰድ ሥራ ላይ ያውላሉ፡፡ | 1.1. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ዕድገት<br><br>1.2. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ዕድገት በኢትዮጵያ | 2<br><br>3 | - በቅድመ መደበኛ ፕሮግራም ዕድገት ስመጥር የሆኑ ምሑራንን ያውቁ እንደሆነ መጠየቅ፡-<br>- የዘመኑ ስለነበረ የሕፃናት አያያዝና አስተዳደግ ታሪክ ባጭሩ ማስረዳት<br>- በኢትዮጵያ መቼ የሕፃናት ትምህርት እንደተጀመረ እነርሱ ከየት ጀምረው መማር እንደቻሉ በአካባቢአቸው ስላለው ሁኔታ እንዲናገሩ ማነቃቃት<br>- በኢትዮጵያ ከፊደል ትምህርት ቤቶች የጀመረው የሕፃናት ትምህርት ዕድገትና መስፋፋት ምን እንደሚመስል በይዘቱ | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ዶክመንት<br>- መመሪያዎች<br>- ሥርዓተ ትምህርት | - የተለያዩ ጥያቄዎች በመጠየቅ ግንዛቤአቸውን ማረጋገጥ<br>- ሙከራ መስጠት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህሩ አቀራረብ | የመርጃ ማሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | • ፖሊሲ መመሪያዎች ሥርዓተ ትምህርት<br>• የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን | 2 | ላይ እንደተቀመጠው የነበረውንና አሁን ያለውን ሁኔታ መመርያ ፣ ፖሊሲ ፣ ሥርዓተ ትምህርት፣ኮንቬንሽን በማሳየት ማስረዳትና ማወያየት<br>- አሁን ያለውን ቀደም ሲል ከነበረው ጋር እንዲያገናዝቡ በማድረግ ስላገኙት ተሞክሮ እንዲናገሩ ማድረግ | | |
| 2 | የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት አደረጃጀት | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን፡-<br>• የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤትን ዓላማ ይገነዘባሉ፡፡ | 2.1. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ዓላማ | 3 | - ስለ ቅድመ መደበኛ ት/ቤት ዓላማ የሚያውቁትን እንዲናገሩ መጠየቅ ማወያየት ዓላማውን ለመተግበር ምን ዓይነት አካባቢ እንደሚያስፈልግ በመጠየቅ ማወያየት | -የማስተማሪያ ጽሑፍ | |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህሩ አቀራረብ | የመርጃ ማሣሪየ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ስማሚቋቋምበት አካባቢ ምርጫ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡ | 1.2. የአካባቢ ምርጫ<br>• የአካባቢ ምርጫ መስፈርቶች | 3 | - የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስለሚቋቋምበት አካባቢ ምርጫ ያላቸውን ሐሳብ እንዲናገሩ መጠየቅ፣<br>- በቡድን የአካባቢ ምርጫ መስፈርቶችን እንዲያወጡ ማድረግና መስፈርቶቻቸው ላይ መወያየት<br>- ተገቢውን አቅጣጫ እንደይዙ ማድረግና ግንዛቤ ማስጨበጥ | - የማስተማሪያ ጽሑፍ (ሞጅውል) | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- የቡድን ሥራ አቅርቦታቸውን ማዳመጥ<br>- ከፕራክቲከም] ያዩትን ሲናገሩ ምን ያህል መረዳት፣ ማገናዘብ እንደቻሉ መመልከት |
| | | | 2.3 የግቢ አደረጃጀት<br>• ግቢ ምን ሊመስል ይገባል?<br>• የግቢ ጥቅም<br>• የግቢ አደረጃጀት | 3 | - የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ግቢ ምን ሊመስል እንደሚገባ ፕራክቲከም ላይ ያዩትን መጠየቅና | - ግቢን የሚያሳይ ስዕል ወይም ፎቶ ግራፍ | |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህሩ አቀራረብ | የመርጃ ማሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የግቢ ስፋት በነፍስ ወከፍ ስንት ሊሆን እንደሚገባ ማስረዳት<br>-የግቢ ገፅታን የሚያሳዩ ስዕሎች ወይም ፎቶ ግራፎች ማሳየትና ተገቢው ገፅታ ምን መምሰል እንደለበት በመጠየቅ ማወያየት ተገቢውን የግቢ ገፅታ ማስረዳት<br>-የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ግቢ ለምን እንደሚጠቅም መጠየቅ ማወያየት ጥቅሙን ማስረዳት<br>-ስለግቢ አደረጃጀት ማስረዳት ማወያየት ተገቢውን ሀሳብ እንዲጨብጡ ማድረግ | | |
| | | ከዚህ ትምህርት በኂላ እጩ መምህራን፡-<br>-በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ሊኖሩ የሚገባቸውን የመገልገያ ክፍሎች ያውቃሉ | 1.3. የመገልገያ ክፍሎች ዓይነትና አደረጃጀት<br>• የመገልገያ ክፍሎች ዓየነትና መጠን<br>1.4. የቁሳቁስ ምርጫና አደረጃጀት | 4<br><br><br><br><br>4 | - ፕራክቲከምአንድ ላይ ስለአዩአቸው የመገልገያ ክፍሎች መጠየቅና መወያየት<br>- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ሊኖረ ስለሚገባቸው የመገልገያ ክፍሎችና ዓይነትና መጠን በልጅ ማስረዳት<br>- በየመገልገያ ክፍሎች በተለይ በመማሪያ ክፍል ሊኖሩ የሚገባቸውን ቁሳቁሶች በቡድን መወያየት ሰርተው እንዲያቀርቡ ማድረግና ተገቢውን የክፍሎች አደረጃጀት እንዲረዱ ማድረግ | | |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህሩ አቀራረብ | የመርጃ ማሣሪየ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • ለቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ይረዳሉ<br>• የሰው ኃይል መምረጫ መስፈርቶችና ተግባርና ኃላፊነቶችን ይገነዘባሉ፡፡ | 2.6 የሰው ኃይል አደረጃጀት<br>• የሰው ኃይል ዓይነትና ብዛት<br>• የመምረጫ መስፈርት<br>• ተግባርና ኃላፊነቶች | 5 | - በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ሊሰሩ የሚገባቸው ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆኑ እንዲናገሩ መጠየቅ<br>- የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ዓይነትና የመምረጨ መስፈርቶችን ማስረዳት ከመስፈርቶቹ አንፃር ራሳቸውን እንዲያስተውሉ ማድረግና ማወያየት<br>- የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ውስጥ የሚሰሩ ሰዎች ራሳቸውን እንዴት ሊያሻሽሉ እንደሚችሉ መጠየቅና ማወያየት<br>- በሰው ኃይል ስር የተጠቀሱትን ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነቶች ማስረዳት | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መመሪያ (1985, 1997, 2001..)<br>- በአፀደ ህፃናት ሊኖሩ የሚገባቸው ቁሳቁሶች ናሙና<br>- የመምህራንና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ተግባርና ኃላፊነቶች የሚያሳዩ ጽሑፎች | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- የቡድን ሥራዎችን መመልከት |
| 2. | የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ዕቅድ | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• የድርጅት ዕቅድ አስፈላጊነትና ይዘቱን ይረዳሉ | - የዕቅድ አስፈላጊነት<br>- የአስተቃቀድ ሂደት | 5 | -የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት እንደድርጅት ዕቅድ እንዳለው ናሙና በማሳየት ማስረዳት ይዘቱንና እንዴት እንደ ታቀደ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- የዕቅድ ናሙና | - ጥያቃዎች መጠየቅና ምን ያህል እንደተረዱ ማረጋገጥ<br>- የቡድን ሥራቸውን ማረም |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህሩ አቀራረብ | የመርጃ ማሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | -የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ዕቅድ ማቀድን በቡድን እንዲሞክሩ ማድረግ | | |
| 3. | የመዝገብ አያያዝ | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን:-<br>• መዝገብን በጥንቃቄ የመያዝን ጥቅም ይገነዘባሉ፡፡<br>• በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ሊያዙ የሚገባቸውን መዛግብት (በተለይ የክፍላቸውን) ይለያሉ፡፡ | • የመዝገብ አያያዝ<br>-አስፈላጊነት<br>- ሊያዙ የሚገባቸው መዛግብት | 3 | -በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ምን ምን ዓይነት መዛግብት ሊቀሩ እንደሚችሉ መጠየቅና ማወያየት<br>-መዛግብትን የመጠበቅን አስፈላጊነት ማስረዳት<br>-መዛግብት እንዴት መያዝና መጠበቅ እንዳለባቸው ማስረዳት<br>-በፕራክቲከም አንድ አፀደ ሕፃናት ሲሄዱ ያዩአቸውን የመዛግብት ዓይነትና እንዴት ተይዘው እንዳሉ ተመልክተው ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- የመዛግብት ናሙና | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- ሪፖርታቸውን ማረም |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህሩ አቀራረብ | የመርጃ ማሣሪየ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ከባለ ድርሻ አካላትና ከወላጅ ጋር የሚደረግ ግንኙነት | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• ግንኙነት የማድረግን አስፈላጊነት ይረዳሉ፡፡<br>• ግንኙነት የማድረግ ትኩረት ነጥቦችን ይገነዘባሉ<br>• ግንኙነት ስለማድረጊያ ዚዴዎች ይረዳሉ፡፡ | 5.1. አስፈላጊነት<br>5.2. መንግሥታ ዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር<br>5.3. ከወላጆች ጋር<br>• የትኩረት ነጥቦች<br>• የመገናኛ ዘዴዎች | 3 | - ከባለ ድርሻ አካላት ጋር የሚደረግ ግንኙነት ለምን እንዳስፈለገን መጠየቅና ማወያየት አስፈላጊነትን ማስረዳት<br>- መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ከምን አኳያ ግንኙነት ማድረግ እንደሚያስፈልግ መጠየቅና ማወያየት<br>- ከወላጅ ጋር ግንኙነት ለመፍጠር በሚያስፈልጉ ትኩረት በሚሰጣቸው ነጥቦች ላይ ማወያየት<br>- ከወላጅ ጋር ግንኙነት መፍጠሪያ መንገዶችን ማስረዳትና ማወያየት<br>- ከወላጅ ጋር ግንኙነትን በተመለከተ አጭር ድራማ እንዲያቀርቡ ማድረግ | -የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>-የመምህርና የወላጅን ግንኙነት የሚያሳዩ ፎቶግራፎች | - ጥያቄዎች መጠቅና ምን ያህል እንደተረዱ ማረጋገጥ<br>- ወላጅና መምህር ሆነው በመነጋገር ድራማ እንዲያዘጋጅ ማነቃቃት መከታተል፡፡ |

## 4.ጤናና ሥርዓተ -ምግብ

በሳምንት የተፈቀደ ጊዜ -2

የኮርሱ አጠቃላይ ዓላማዎች

ይህንን ኮርስ ካጠናቀቁ በኋላ እጩ መምህራን

- የጤናን ትርጉምና አስፈላጊነት ይገነዘባሉ፣
- የምግብንና የሥርዓተ ምግብን ምንነት ከጤና ጋር ያላቸውን ግንኙነት ይረዳሉ፡፡
- አልሚ ምግብ የሚገኝባቸውን የምግብ ክፍሎችና ለምግብ ሊደረግ የሚገባውን ጥንያቄ በማወቅ በተግባር ላይ ያውላሉ፡፡
- የታወቁ የሕፃናት በሽታዎችን መነሻ የምግብ እጥረትንና የሚያስከትለውን ችግር ለይተው ይገነዘባሉ፡፡
- ስለቤተሰብ ምጣኔ ምንነት አስፈላጊነትና ዘዴ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡
- ስለመጀመሪያ ህክምና ርዳታ መሠረታዊ እውቀት ይኖራቸዋል፡፡

**የኮርሱ ይዘቶች**

1. ጤና

    1.1. የጤና ትርጉምና አስፈላጊነት

2. ምግብ

    2.1. መሠረታዊ የምግብ ክፍሎችና መገኛቸው

    2.2. የተመጣጠነ ምግብ ትርጉምና አስፈላጊነት

3. ሥርዓተ- ምግብ

    3.1. የሥርዓተ ምግብ ትርጉም

    3.2. የንጥረ ምግቦች ትርጉምና የምግብ (ሐይጅን) አጠባበቅ

    3.3. የሕፃናት አመጋገብ

        3.3.1. የታመመ ሕፃን አመጋገብና እንክብካቤ

        3.3.2. የንጥረ ምግብ እጥረት የሚያስከትለው ተፅእኖ እና የመከላከያ ዘዴው

4. በሽታ

    4.1. የበሽታ ትርጉም

    4.2. የኤድስና የአባላዘር በሽታዎች

        4.2.1. የበሽታው ምንነት

4.2.2. መተላለፊያው

4.2.3. ለበሽታዉ የሚደረግ ጥንቃቄና የመከላከያ ዘዴዎች

4.3. የተለመዱ የሕፃናት በሽታዎች

4.4. ለታመሙ ሕፃናት የሚደረግ ጥንቃቄ

4.5.በሽታን የመከላከያ መንገዶች

4.5.1. የግል የቤትና የአካባቢ ንፅህና

4.5.2. የተመጣጠነ ምግብ

4.5.3. ክትባት

5. የሕፃናት ጤና አጠባበቅ

5.1.በቅድመ ወሊድ

5.2.በድህረ ወሊድ

6. የቤተሰብ ምጣኔ

6.1.የቤተሰብ ምጣኔ አስፈላጊነት

6.2.ቤተሰብን መመጠኛ ዘዴ

7. የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ

7.1.የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ምንነት

7.2.የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ዓላማና ደንቦች

7.3.በአፀደ ሕፃናት ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎች

7.4.ለተለያዩ አደጋዎች እርዳታ አሰጣጥ

## ጤናና ሥርዓተ ምግብ ትምህርት

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጤና | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• የጤናን ትርጉም ይረዳሉ አስፈላጊነቱን ይገነዘባሉ፡፡ | 1.1 የጤና ትርጉምና አስፈላጊነት | 2 | - የጤናን ትርጉም መጠየቅ ማወያየት ማስረዳት | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- የታመመና ጤነኛ ሰው ምስል | - የምዘና ጥያቄዎች |
| 2 | ምግብ | • የምግብን ትርጉም ያውቃሉ<br>• መሠረታዊ የምግብ ክፍሎችና መገኛቸውን ይገነዘባሉ<br>• የተመጣጠነ ምግብን ትርጉምና አስፈላጊነት ይረዳሉ፡፡ | 2.1. የምግብ ትርጉም መሠረታዊ የምግብ ክፍሎችና መገኛቸው<br>2.2. የተመጣጠነ ምግብ ትርጉምና አስፈላጉነት | 4 | - ስለ ምግብ ምንነት መጠየቅ ማወያየትና ማስረዳት<br>- የሚመገቧቸውን ምግቦችና መገኛቸውን እንዲጽፉና እንዲናገሩ ማድረግና ማስረዳት<br>- የተመጣጠነ ምግብ የሚባለው ምን የያዘ (ዓይነት) እንደሆነ መጠየቅ ማወያየትና ማስረዳት | - የምግብ ዓይነቶችን የሚያሳዩ ስዕል<br>- የተመጣጠኑ የምግብ ዓይነቶችን የሚያሳይ ስዕል | - ጥያቄዎች<br>- 1 እና 2 ላይ ሙከራ መስጠት |
| 3 | ሥርዓተ ምግብ | • የሥርዓተ ምግብን ምንነት ይገነዘባሉ፡፡<br>• የንጥረ ምግቦችን ትርጉም ይረዳሉ<br>• የምግብ አጠባበቅ ይረዳሉ በተግባር የመተርጐም ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡ | 3.1. የሥርዓተ ምግብ ትርጉም<br>3.2 የንጥረ ምግቦች ትርጉምና አጠባበቅ | 4 | ስለ ስርዓተ ምግብ ምንነት መጠየቅ ማወያየት ማስረዳት<br>የንጥረ ምግቦችን ትርጉምና አጠባበቅ ማስረዳት ማወያየት<br>ስለ ምግብ አጠባበቅ በቡድን እንዲወያዩና በተለምዶ በሳይንሳዊ መንገድ ለይተው እንዲጽፉ ማድረግ | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- ከርዕሱ ጋር የተዛመዱ ስዕሎች | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- የቡድን ሥራ ውጤታቸውን ማየት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • ስለ ሕፃናት አመጋገብ ይረዳሉ መመገብ ይችላሉ<br>• የታመመ ህፃን አመጋገብና እንክብካቤን ይረዳሉ | 6.5. የሕፃናት አመጋገብ<br>6.5.1. የታመመ ህፃን አመጋገብና እንክብካቤ<br>6.5.2. የንጥረ ምግቦች እጥረት የሚያስከት ለው ተፅዕኖና መከላከያ ዘዴው | 4 | - ከልምዱ (ከተሞክሮ) ስለ ሕፃናት አመጋገብ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማድረግና ማወያየት<br>- ስለታመመ ህፃን አመጋገብ ማወያየት ማስረዳት<br>- የንጥረ ምግቦች እጥረት ያጋጠመው ሕፃን አይተው ያውቁ እንደሆነ በመጠየቅ ስለ ተፅዕኖው ና የመከላከያ ዘዴ ማስረዳት | - የንጥረ ምግቦች እጥረት ያጋጠመውና ያላጋጠመው ሕፃን ስዕል | - ጥያቄዎች መጠየቅ |
| 4 | በሽታ | ከዚህ ትምህርት በኍላ እጩ መምህራን<br>• የበሽታ ምንነትን ይረዳሉ<br>• የተለመዱ የሕፃናት በሽታዎችን ይለያሉ<br>• የኤድስና የአባለዘር በሽታዎችን ይለያሉ የመተላለፊያ መንገዶችን ያውቃሉ ለበሽታው የሚደረገውን ጥንቃቄ ይገነዘባሉ፡፡ | 3.1. የበሽታ ትርጉም<br>3.2. ኤድስና የአባለዘር በሽታዎች ን<br>3.2.1. የበሽታ ው ምንነትና መተላለ ፊያው<br>3.2.2. ለበሽታ ው ሊደረግ የሚገባው ጥንቃቄና መከላከያ | 4 | - ስለ በሽታ ምንነት መጠየቅ ማወያየት ማስረዳት<br>- ስለኤድስና የአባላዘር በሽታዎች የሚያውቁትን እንዲናገሩ በማድረግ ማወያየት ማስረዳት<br>- ስለ ማተላለፊያ መንገዶች ማወያየት ማስረዳት<br>- ለበሽታው ሊደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ መጠየቅ ማወያየት ማስረዳት<br>- የመከላከያ ዘዴዎቹን ማስረዳት | - የማስተማ ሪያ ጽሑፍ<br>- በሽታው የያዘውን ሰው የሚያሳዩ ስዕሎች | - ጥቃቃዎችን መጠየቅና መልሳቸውን በማዳመጥ ምን ያህል እንደተረዱ ማረጋገጥ |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • በሽታን የመካላከያ መንገዶችን ይረዳሉ<br>• የግል የቤትና የአካባቢ ንፅህናን ይጠብቃሉ | 4.5 በሽታን የመከላከያ መንገዶች<br>4.5.1 የግል ፣ የቤትና የአካባቢ ንፅህና<br>4.5.2. የተመጣጠነ ምግብ<br>4.5.3 ክትባት | 4 | - በሽታን ስለመከላከያ መንገዶች በቡድን ተወያይተው እንዲያቀርቡ ማድረግ<br>- በሽታን የመከላከያ መንገዶችን ማስረዳትና ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ<br>- ንፅህና የተመጣጠነ ምግብና ክትባት በወላጆች ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባና ከወላጆች ጋር መስራት እንደሚገባቸው ማስረዳትና ወላጆችን የማስተማሪያ መንገዶችን እንዲገነዘቡ ማድረግ | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- ከርዕሱ ጋር የተያያዙ ስዕሎች | - ጥቃቃዎች መጠየቅ<br>- የቡድን ሥራቸውን መመልከት<br>- ሙከራ መስጠት |
| 5 | የሕፃናት ጤና አጠባበቅ | ከዚህ ትምህርት በኂላ እጩ መምህራን<br>• በቅድመ ወሊድ ሊደረግ ስለሚገባው ጤና አጠባበቅ ይገነዘባሉ<br>• በድህረ ወሊድ ለሕፃናት ሊደረግ ስለሚገባው ጤና አጠባበቅ ይረዳሉ፡፡ | ➢ በቅድመ ወሊድ<br>➢ በድህረ ወሊድ | 6 | - በተለምዶአዊና ባህላዊ ጤና አጠባበቆች ላይ ከተሞክሮአቸው እንዲወያዩ ማድረግ ተገቢውን የጥንቃቄ ሂደት ማስረዳት<br>- ሊደረግ በሚገባው ጥንቃቄ ላይ በቡድን እንዲወያዩና እንዲያንፀባርቁ ማድረግ | - የማስተማሪያ ጽሑፎች<br>- ስዕሎች | - የቡድን ሥራ ፅብረቃቸውን መከታተል<br>- የተለያዩ ጥቃቄዎች መጠየቅ |
| 6 | የቤተሰብ ምጣኔ | ከዚህ ትምህርት በኍላ እጩ መምህራን<br>• የቤተሰብ ምጣነ አስፈላጊነትን ይገነዘባሉ | 6.1. የቤተሰብ ምጣኔ አስፈላጊነት<br>6.2. የቤተሰብ | 3 | - በተለምዶ የሚታወቀውን መጠየቅና ማወያየት<br>- በቤተሰብ ምጣኔ አስፈላጊነት ላይ ማወያየት ማስረዳት | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- ስዕሎች<br>- ሉፕ የወሊድ | - ጥያቃዎች መጠየቅ<br>- የቡድን ውይይት<br>- |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • የቤተሰብ ምጣኔን ማከናወኛ ዘዴዎችን ይረዳሉ፡፡ | ምጣኔንማከናወኛ ዘዴዎች | 3 | - በቡድን በመመጠኛ ዘዴዎች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ የተወያዩበትን እንዲያንፀባርቁ ማድረግ መሳሪያና ስዕሎችን በማሳየት ተገቢውን የበተሰብ ምጣኔ ማከናወኛ ዘዴዎችን ማስረዳት ለጥያቃዎች መልስ መስጠት | መከላከያ እንክብሎች እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔን የሚደግፍ መሳሪያዎች ቻርቶች | ውጤታቸውን ማየት |
| 7 | የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ምንነትን ይገነዘባሉ፡፡<br>• ዓላማዎቹንና ደንቦቹን ይረዳሉ፡፡<br>• በአፀደ ሕፃናት ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን ለይተው ያውቃሉ፡፡<br>• የመጀመሪያ ዕርዳታ አሰጣጥ ዘዴዎችን ይረዳሉ፡፡ ዕርዳታ የሚደረግ እውቀት (መረጃ) ይኖራቸዋል፡፡ | 7.1 የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ምንነት<br>7.2 የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ዓላማና ደንቦች<br>7.3 በአፀደ ሕፃናት ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎች<br>7.4. ለተለያዩ አደጋዎች ዕርዳታ አሰጣጥ ዘዴዎች | 6 | - ስለመጀመሪያ ዕርዳታ አሰጣጥ ምንነት መጠየቅ ፣ ዕርዳታ ተደርጎላቸው የሚያውቁ ከሆነ ተሞክሮአቸውን እንዲናገሩ ማድረግ ምንነቱን ማስረዳት<br>- ዓላማዎችና ደንቦቹን በቡድን አዲያነቡና እንዲወያዩባቸው ግልፅ አይደለም የሚሉትን በቡድን መጠየቅ እንዲችሉ ማድረግና ማስረዳት<br>- በቅድመ መደበኛ ት/ቤት (በአፀደ ሕፃናት) እየተው ወይም አጋጥሞአቸው የሚያውቅ አደጋ ካለ ምን እንደሆነ ምን ዕርዳታ እንደተደረገ እንዲናገሩ ማድረግ አደጋዎቹን ማስረዳት | - የመጀመሪያ ዕርዳታ መስጫ ሳጥን ከነ መሣሪያዎች<br>- የተጐዳ ክፍልን ማሰሪያ በተገቢው መንገድ የተቀረጡ አቡጀዲ ጨርቆች<br>- ስዕሎች | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- በተግባር ሲያሳዩ መመልከትና መመዘን<br>- የቡድን ሥራ ውጤታቸውን ሲያቀርቡ መመልከት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህርር አቀራረብ | የመርጃ መሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | - ለተለያዩ አደጋዎች እንዴት የመጀመሪያ ዕርዳታ እንደሚሰጥ በስዕል ማሳየት በተግባርም ተማሪዎችን በመጠቀም ማሳየት<br>- ያዩትን እርስ በዕርሳቸው እንዲሞክሩ ማድረግ (መቋጠርያ ወይም ማሰሪያ ጨርቆቹን እንዴት እንደሚቆረጡ ጭምር ማሳየትና ማለማመድ ይገባል) | | |

## 5.የልዩ ፍላጎት ትምህርት

**ለኮርሱ የተፈቀደዉ ጊዜ በሳምንት- 2 ፔሬድ**

**አጠቃላይ ዓላማዎች**

ይህን ኮርስ ካጠናቀቁ በኃላ እጩ መምህራን

- የልዩ ፍላጎት ትምህርትን ምንነትና ትርጉም ይረዳሉ
- የልዩ ፍላጎት ፅንሰ ሀሳብን ይገነዘባሉ ልዩ ፍላጎት ያላቸዉን ሕፃናት በመለየት እገዛ ሊያደርጉ ይችላሉ
- ልዩ ፍላጎት ያላቸዉን ህፃናት ኣይነትና አመዳደብ መግለፅ ይችላሉ

የኮርሱ ይዘቶች

1. የልዩ ትምህርት ፅንሰ ሐሳቦች
    1.1. የልዩ ፍላጎት ትምህርት ምንነትና ትርጉም
    1.2. የልዩ ፍላጎት ትምህርት አስፈላጊነትና ጠቀሜታ
    1.3. በልዩ ፍላጎት ዙርያ የሚነሱ መሰረታዊ ደንቦችና ህጎች
2. የማየት ጉድለት ያለባቸዉ ህፃናት
    2.1. የማየት መሳን መንስኤዎችና መለያ መንገዶች
    2.2. የማየት መሳን ላለባቸዉ የሚደረግ ትምህርታዊና ማህበራዊ እገዛ
    2.3. የማየት መሳን ላለባቸዉ  የሚደረግ የህይወት ኪሒሎች ሙያዊ እገዛ
3. የአእምሮ ዉስንነት ችግር ያለባቸው ህፃናት
    3.1. የአእምሮ ዉስንነት ችግር መንስኤዎችና መለያ መንገዶች
    3.2. የአእምሮ ዉስንነት ችግር ላለባቸዉ የሚሰጥ ትምህርታዊና ማህበራዊ እገዛ
    3.3. የአእምሮ ዉስንነት ችግር ላለባቸዉ የሚደረግ የህይወት ኪሒሎች ሙያዊ እገዛ
4. አካላዊ እክልና የጤንነት ጉድለት ያለባቸዉ ሕፃናት
    4.1. አካላዊ እክልና የጤንነት ችግር መንስኤዎችና ለይቶ ማወቂያ መንገዶች
    4.2. አካላዊ እክልና የጤንነት ችግር ላለባቸዉ የሚደረግ ትምህርታዊና ማህበራዊ እገዛ
    4.3. አካላዊ እክልና የጤንነት ችግር ላለባቸዉ የሚደረግ የህይወት ኪሒሎች ሙያዊ እገዛ
5. የመግባባት ችግር ያለባቸዉ ህፃናት
    5.1. የመግባባት ችግር መንስኤዎችና ለይቶ ማወቂያ መንገዶች
    5.2. የመግባባት ችግር ላለባቸዉ የሚደረግ ትምህርታዊና ማህበራዊ እገዛ
    5.3. የመግባባት ችግር ላለባቸዉ የሚደረግ የህይወት ክህሎት ሙያዊ እገዛ
6. የባህሪ ችግር ያለባቸዉ ህፃናት
    6.1. የባህሪ ችግር መንስኤዎችና ለይቶ ማወቂያ መንገዶች

6.2. የባህሪ ችግር ላለባቸዉ የሚደረግ ትምህርታዊና ማህበራዊ እገዛ

6.3. የባህሪ ችግር ላለባቸዉ የሚደረግ የህይወት ኪሒሎች ሙያዊ እገዛ

7. የመማር ችግር ያለባቸዉ ህፃናት

7.1. የመማር ችግር መንስኤዎች

7.2. የመማር ችግር ላለባቸዉ የሚደረግ ትምህርታዊና ማህበራዊ እገዛ

7.3. የመማር ችግር ላለባቸዉ የሚደረግ የህይወት ክህሎት ሙያዊ እገዛ

8. ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ ያላቸዎ ህፃናት

8.1. ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ ያላቸዉ ህፃናት ባህሪያት

8.1.1. አዎንታዊ

8.1.2. አሉታዊ

9. ከወላጅ ጋር መስራት

9.1ከወላጅ ጋር የመስራት አስፈላጊነትና መንገዶች

# የልዩ ፍላጎት ትምህርት

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣርያ | ግምገማና ምዘና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የልዩ ትምህርት ፅንሰሃሳብ | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን፦<br>• የልዩ ፍላጎት ትምህርት ምንነትና ትርጉም ይረዳሉ<br>• የልዩ ፍላጎት ትምህርት አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ይረዳሉ<br>• በልዩ ፍላጎት ዙርያ የሚነሱ መሠረታዊ ደንቦችና ህጎችን ይገነዘባሉ | 1.1. የልዩ ፍላጎት ትምህርት ምንነትና ትርጉም<br>1.2 የልዩ ፍላጎት ትምህርት አስፈላጊነትና ጠቀሜታ<br>1.3 በልዩ ፍላጎት ዙርያ የሚነሱ መሠረታዊ ደንቦችና ህጎች | -ልዩ ችግር ያለበት ሕፃን ምን ዓይነት እንደሆነ መጠየቅና ማወያየት ማስረዳት<br>-የልዩ ፍላጎት ትምህርት ለምን እንደሚያስፈልግ መጠየቅና ማወያት አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ማስረዳት<br>-ደንቦችና ህጎችን ማስረዳትስለተፈፃሚነታቸው በቡድን ተወያይተው እንዲናገሩ ማድረግና አቅጣጫ ማስያዝ | የማስተማርያ ፅሁፍ<br>ልዩ ችግር ያለባቸው ሕፃናትን የሚያሳይ ፎቶ<br>የማስተማርያ ፅሁፍ<br>ማስተማርያ ፅሁፍ<br>የመመርያዎች | ጥያቄዎች መጠየቅና ምን ያህልእንደተገነዘቡ ማረጋገጥ<br>የቡድን ሥራዎችን ማዳመጥና መገምገም |
| 2. | የማየት ጉድለት ጉድለት ያለባቸው ሕፃናት | • የማየት መሣን ምንነትና መንስዔዎችን ይረዳሉ<br>• የማየት መሣን ላለበቸው ስለሚደረግ ትምህርታዊና ማህበራዊ ዕገዛ ይረዳሉ<br>• የማየት መሣን ላለበቸው ስለሚደረግ የሕይወት ክህሎት ዕገዛ ይረዳሉ ዕገዛ ማድረግም ይችላሉ | 2.1የማየት መሣን ምንነትና መንስዔዎች መለያ መንገዶች<br>2.2 የማየት መሣን ላለበቸው ስለሚደረግ ትምህርታዊና ማህበራዊ ዕገዛ<br>2.3 የማየት መሣን ላለበቸው ስለሚደረግ የሕይወት ክህሎት ሙያዊ ዕገዛ | -የማየት መሣን ምንነት ምን እንደሆነ መጠየቅና ማወያየት<br>-መንስዔዎቹን መጠየቅና ማወያየት ማስረዳት እንዴት መለየት እንደሚቻል በመጠየቅ ማወያየትና ማስረዳት<br>-በሕብረተሰብ በተለምዶ የሚደረገውን እገዛ መጠየቅና ማወያት ሊደረግላቸው እንደሚገባ ማስረዳት<br>-የሕይወት ኪሂል ማለት ምን እንደሆነ መጠየቅና በቡድን ተወያይተው እንዲያቀርቡ ማድረግ ማየት ለተሳናቸው ስለሚያስፈልጉ ክሂሎች መጠየቅና ማወያየት ሙያዊ ዕገዛውን ማስረዳት | ማስተማርያ ፅሁፍ<br>ማስተማርያ ፅሁፍ<br>የሕይወት ክህሎችን የሚያሳዩ ሥዕሎች | ጥያቄዎች መጠየቅ የመወያያ ጥያቄዎቻቸውን ማዳመጥና መረዳታቸውን ማረጋገጥ<br>የቡድና ውይይታቸውን በማዳመጥ ተጨማሪ ጥያቄዎች መጠየቅና መረዳታቸውን ማረጋገጥ |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣርያ | ግምገማና ምዘና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | የአዕምሮ ውስንነት ችግር ያለባቸው ሕፃናት | ከዚህ ትምህርት በኂላ እጩ መምህራን፡-<br>• የአዕምሮ ውስንነት ችግር ምንነትና መንስዔዎች ይገነዘባሉ<br>የአዕምሮ ውስንነት ይለያሉ<br>• የአዕምሮ ውስንነት ላለባቸው ስለሚደረግ ትምህርታዊና ማህበራዊ ዕገዛ | 3.1 የአዕምሮ ውስንነት ችግር ምንነት መንስዔዎችና መለያ መንገዶች<br>3.2 የአዕምሮ ውስንነት ላለባቸውየሚሰጥ ትምህርታዊና ማህበራዊ ዕገዛ<br>3.3 የአዕምሮ ውስንነት ላለባቸውየሚደረግ የህይወት ክህሎት ሙያዊ እገዛ | -የአዕምሮ ውስንነት ችግር ምን እንደሆነ እንዴት እንደሚገለፅ መንስኤዎችን መጠየቅና ማወያየት መንስኤዎቹንና መለያ መንገዶችን በማስረዳት ተገቢ አቅጣጫ ማስያዝ<br>-በተለምዶ የአዕምሮ ውስንነት ላለባቸው የሚደረግ እገዛ አለወይ<br>በህብረተሰቡ ውስጥ ያላቸው ተቀባይነት ምንያህል ነው በማለት መጠየቅና ማወያየት ሊደረግላቸው የሚገባውን ማህበራዊና ትምህርታዊ ዕገዛ ማስረዳት<br>-የአዕምሮ ውስንነት ላለባቸው ያስፈልጋሉ ተብሎ የሚገመቱ የህይወት ክህሎቶች ምን እንደሆኑ መጠየቅና ማወያየት ሊደረግላቸው ስለሚገባ ዕገዛ ማስረዳት | የማስተማርያ ፅሁፍ<br>የማስተማርያ ፅሁፍ<br>የማስተማርያ ፅሁፍ | ጥያቄዎች መጠየቅና ሙከራ መስጠት<br>ጥያቄዎች መጠየቅና የውይይታቸውን ምላሽ በማዳመጥ ምን ያህል እንደተረዱ ማረጋገጥ<br>ጥያቄዎች መጠየቅና ምን ያህል እንደተረዱ ማረጋገጥ<br>ሙከራ መስጠት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣርያ | ግምገማና ምዘና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | አካላዊ ዕክልና የጤንነት ጉድለት ያለባቸው ሐፃናት | • አካላዊ ዕክልና የጤንነት ጉድለት ያለባቸውን መለየት ይችላሉ መንስዔዎቻቸውን ይረዳሉ<br>• የአካላዊ ዕክልና የጤንነት ችግር ላለባቸው ስለሚደረግ ማህበራዊና ትምህርታዊ ዕገዛ ግንዛቤ ይኖራቸዋል<br>• የአካላዊ ዕክልና የጤንነት ችግር ላለባቸው ስለሚደረግ የሕይወት ክህሎቶች ዕገዛ እውቀት ይኖራቸዋል ማገዝም ይችላሉ | 4.1 የአካላዊ ዕክልና የጤንነት ችግር መንስኤዎችና መለያ መንገዶች<br>4.2 የአካላዊ ዕክልና የጤንነት ችግር ላለባቸው የሚደረግ ማህበራዊና ትምህርታዊ ዕገዛ<br>4.3 የአካላዊ ዕክልና የጤንነት ችግር ላለባቸው ስለሚደረግ የሕይወት ክህሎቶች ዕገዛ | -አካላዊ ዕክልና የጤንነት ችግር መንስኤዎችን መጤቅና ማወያት እንዴት መለየት እንደሚቻል እንዲወያዩ ማድረግና በማስረዳት ተገቢውን አቅጣጫ እነዲይዙ ማድረግ<br>-በርዕሱ ላይ ጥያቄ ማቅረብና ማወያየት ሊደረግ ስለሚገባው ትምህርታዊና ማህበራዊ ዕገዛ ማስረዳት<br>-በርዕሱ ላይ ለተተቀሱት ምን አይነት ክህሎቶች ያስፈልጋሉ?<br>ብሎ በመጠየቅ ማወያየት ክህሎቶቹን በቡድን ጽፈው እንዲያቀርቡ ማድረግና ማስረዳት | የማስተማርያ ፅሁፍ<br>የማስተማርያ ፅሁፍ<br>የማስተማርያ ፅሁፍ | ጥያቄዎች መጠየቅና ምን ያህል እንደተረዱ ማረጋገጥ<br>ጥያቄዎች በመጠየቅ<br>ሙከራ መስጠት |
| 5. | የመግባባት ችግር ያለባቸው ሕፃናት | • የመግባባት ችግር ያለባቸውን ሕፃናት ለይተው ያውቃሉ መንስኤዎቻቸውንም ይረዳሉ | 5.1የመግባባት ችግርመንስኤዎችን ለይቶ ማወቅያ መንገዶች | -መግባባት ምን እንደሆነ መጠየቅና ማወያየት ትክክለኛውን በማስረዳት አቅጣጫ ማስያዝ<br>-የመግባባት ችግርመንስኤዎችን መጠየቅ ማወያየትና ማስረዳት<br>-የመግባባት ችግር ያለባቸውን ሕፃናት ለይቶ ማወቅያ መንገዶችን ማስረዳት | የማስተማርያ ፅሁፍ<br>የማስተማርያ ፅሁፍ | ጥያቄዎች መጠየቅ<br>ጥያቄዎች መጠየቅ |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣርያ | ግምገማና ምዘና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • ሊደረግ የሚገባውን ትምህርታዊና ማህበራዊ ዕገዛ ይረዳሉ<br>• የመግባባት ችግር ላለባቸው የሚደረግ የሕይወት ክህሎት እገዛን ይረዳሉ | 5.2 ሊደረግ የሚገባውን ትምህርታዊና ማህበራዊ ዕገዛ<br>5.3 የመግባባት ችግር ላለባቸው የሚደረግ የሕይወት ክህሎት ሙያዊ እገዛ | -ሊደረግ የሚገባውን ትምህርታዊና ማህበራዊ ዕገዛ ማስረዳት<br>-የመግባባት ችግር ያለባቸው ሕፃናት በሕይወት ክህሎት ላይ ምን ችግር እንዳለባቸው መጠየቅና እንዲናገሩ ማድረግ ሊደረግላቸው የሚገባውን ዕገዛ ማስረዳት | የማስተማርያ ፅሁፍ<br>የማስተማርያ ፅሁፍ | ሙከራ መስጠት<br>የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅና መረዳታቸውን ማረጋገጥ |
| 6. | የባህሪይ ችግር ያለባቸው ሕፃናት | • የባህሪይ ችግር ያለባቸው ሕፃናት ለይቶ ማወቅያ መንገዶችንና መንስኤዎችን ይረዳሉ<br>• የባህሪ ችግር ላለባቸው የሚደረግ ትምህርታዊና ማህበራዊ | 6.1የባህርይ ችግር መንስኤዎች ለይቶ ማወቅያ መንገዶች<br>6.2 የባህሪ ችግር ላለባቸው የሚደረግ ትምህርታዊና ማህበራዊ እገዛ<br>6.3 የባህሪ ችግር ላለባቸዉ ህፃናት የሚደረግ የህይወት ክህሎት ዕገዛ | በሕፃናት ላይ ሊታዩ የሚችሉ የባሕርይ ችግሮች ምን ምን ዓይነት እንደሆኑ መጠየቅና ማወያየት ማስረዳት የባህሪይ ችግር ያለባቸውን ሕፃናት ማወቅያ (መለያ) መንገዶችን ማስረዳት<br>-የባህሪ ችግር ላለባቸው ህፃናት በተለምዶ ሚደረገውን መጠቅና ማወያየት ሊደረግ የሚገባውን ትምህርታዊና ማህበራዊ እገዛ ማስረዳት እንደወያዩ ማድረግ<br>-የባህሪ ችግር ያለባቸዉን ህፃናት ሲጫወቱ ሊፈጥሩ የሚችሉትን ሁኔታ | የማስተማርያ መጽሐፍ<br>-ሕፃናት በተለያየ መልኩ ሲጫወቱ የሚያሳይ ስዕል<br>የማስተማርያ ፅሁፍ<br>ስዕል ወይም የባህሪ ችግር ያለባቸዉ ሲጫወቱ የሚያሳይ ፎቶግራፍ | የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>ሙከራ መስጠት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣርያ | ግምገማና ምዘና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 7. | የመማር ችግር ያለባቸዉ ህፃናት | • የመማር ችግር መንስኤዎችን ይረዳሉ<br><br>• የመማር ችግር ላለባቸዉ ስለሚደረግ ትምርታዊና ማህበራዊ እገዛ ይረዳሉ | 7.1 የመማር ችግር መንስኤዎች<br><br>7.2 የመማር ችግር ላለባቸዉ የሚደረግ ትምህርታዊና ማህበራዊ እገዛ<br><br>7.3 የመማር ችግር ላለባቸዉ የሚደረግ የህይወት ክህሎት ሙያዊ እገዛ | - መማር ማለት ምን ማለት እንደሆነ መጠየቅና መወያየት<br><br>- የመማር ችግር መንስኤዎችን መጠየቅ ማወያየት በቡድን ተወያይተዉ መንስኤዎችን እንዲያቀርቡ ማድረግና ማዳመጥ ተገቢዉን አቅጣጫ ማስያዝ<br><br>- የመማር ችግር ላለባቸዉ ስለሚደረግ ትምርታዊና ማህበራዊ እገዛ በቡድን እንዲወያዩና እንዲያቀርቡ ማድረግ ማስረዳት<br><br>- የመማር ችግር ያለባቸዉ ምን አይነት የህይወት ክህሎቶች እገዛ እንደሚያስፈልጋቸዉ መጠየቅና ማወያየት ማስረዳት | የማስተማርያ ፅሁፍ<br><br>የማስተማርያ ፅሁፍ<br><br>የማስተማርያ ፅሁፍ | የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅና መረዳታቸውን ማረጋገጠ<br><br>ጥያቄዎችን መጠየቅ<br><br>የቡድን ውይይት ፅብረቃቸዎን ማዳመጥ መገምገም<br><br>ሙከራ መስጠት |
| 8. | ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ ያላቸዎ ህፃናት | • ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ ስላላቸዉ ህፃናት ባህሪያት ይረዳሉ | 8.1 ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ ያላቸዉ ህፃናት ባህሪያት<br>✓ አዎንታዊ<br>✓ አሉታዊ | - ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ ያላቸዉ ህፃናት ላይ ሊታዩ ስለሚችሉ ባህሪያት መጠየቅና ማወያየት ማስረዳት<br><br>- አዎንታዊና አሉታዊ ባህሪያትን ዝርዝር ደባልቆ መስጠትና ተወያይተዉ ለይተዉ እንዲያቀርቡ ማድረግ ማስረዳት | የማስተማርያ ፅሁፍ | ጥያቄዎችን መጠየቅ |
| 9 | ከወላጅ ጋር መስራት | • ችግር ካለባቸዉ ሕፃናት ወላጆች ጋር መስራትና ህፃናትን መርዳት ይችላሉ | 9.1 ከወላጅ ጋር የመስራት ስፈላጊነትና መንገዶች | ከወላጅ ጋር የመስራትን አስፈላጊነትን መጠየቅና ማወያየት ማስረዳት<br><br>ከወላጅ ጋር የመስራት መንገዶችን ማስረዳት ተግዳሮቶችን በቡድን እንዲሰራ ማድረግ | የማስተማርያ ፅሁፍ | ጥያቄዎችን መጠየቅ<br><br>የቡድን ስራ ዉጤታቸዉን ማየት |

## *II. በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤትከሚከናወኑ ተግባራት ጋርየተያያዙ ትምህርቶች*

### 7.ጨዋታ

(Play)

ለኮርሱ የተፈቀደ ጊዜ 2

የኮርሱ አጠቃላይ ዓለማዎች

ይህንን ኮርስ ካጠናቀቁ በኋላ እጩ መምህራን

- የጨዋታን ምንነት ይረዳሉ ፣ ጨዋታ ለሕፃናት ዕድገትና መዳበር የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ይገነዘባሉ፡፡
- የጨዋታን ዕድገት ደረጃዎች ይረዳሉ ሕፃናትን እንደየደረጃቸው እንዲጫወቱ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ ጨዋታን ማገዝ ይችላሉ ፡፡
- የጨዋታ ዓይነቶችንና ባህሪአቸውን ይረዳሉ በተገቢው መንገድ ማደራጀትና መምራት ይችላሉ፡፡
- በተለያዩ የሕፃናት ጨዋታዎች የመሳተፍ ፍላጎትን ያዳብራሉ፡፡
- ጨዋታ ሕፃናትን የማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን ተረድተው በሕፃናት አስተዳደግና ትምህርት አሰጣጥ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡
- ጨዋታ በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ ያለውን ቦታ ይገነዘባሉ ጥቅም ላይ ማዋልም ይችላሉ፡፡
- የመጫወቻ ዓይነቶችንና አመራረጣቸውን ይረዳሉ በአካባቢ ከሚገኝ ጥሬ ዕቃ መጫወቻዎችን የመሥራት ዕውቀትን ያዳብራሉ፡፡

የኮርሱ ይዘቶች

1. የጨዋታ ትርጉምና ጥቅሞች
   1.1. የጨዋታ ትርጉም
   1.2. የጨዋታ ጥቅሞች
2. የጨዋታ ዕድገት ደረጃዎች
3. የጨዋታ ዓይነቶችና አመራር
   3.1. የጨዋታ ምንጮች (መነሻዎች)
   3.2. የመስሎ መጫወት ጨዋታ
   3.3. ትምህርታዊ ጨዋታዎች
   3.4. የመገንባት ጨዋታ
   3.5. እንቅስቃሴአዊ (ስፖርታዊ) ጨዋታዎች
   3.6. ጨዋታ ድራማ
4. ጨዋታ በቅድመ መደበኛ ሥርዓተ-ትምህርት
   4.1. ጨዋታ እንደማስተማሪያ ዘዴ
   4.2. ጨዋታ በሥርዓተ -ትምህርቱ ውስጥ ያለው ቦታ
5. መጫወቻዎች
   5.1. የመጫወቻ ዓይነቶች
   5.2. የመጫወቻዎች አመራረጥ

## ጨዋታ

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | ክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የጨዋታ ትርጉምና ጥቅሞች | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን ፡-<br>• የጨዋታን ትርጉም ያውቃሉ<br>• ጨዋታ ለሕፃናት ዕድገት ያለውን ጥቅም ይገነዘባሉ፡፡ | 1.1. የጨዋታ ትርጉም<br>1.2. የጨዋታ ጥቅሞች | 2<br>2 | -የጨዋታን ምንነት መጠየቅ ጨዋታ አዋቂዎችም ይጫወታሉ ምን ልዩነት አለው ብሎ በመጠየቅ እነዲወያዩበት ማድረግ የሕፃናት ጨዋታን ትርጉም ማስረዳት<br>-ሕፃናት ለምን ጨዋታን እንደሚወዱ መጠየቅ ማወያየት ማስረዳት<br>-ጨዋታ ለሕፃናት የሚሰጠውን ጥቅም መጠየቅና ማወያየት የሚሰጠውን ጥቅም ከሁለንተናዊ መዳበር አንፃር በዝርዝር ማስረዳት በየአካባቢአቸው ሲጫወቱ ከሚያዩአቸው ሕፃናት ጋር የተረዱትን እንዲገናዘቡ ማድረግ | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- መጫወቻዎች | - ጥያቄዎች መጠየቅና ምን ያህል እንደተረዱ ማረጋገጥ |
| 2 | የጨዋታ ዕድገት ደረጃዎች | • የጨዋታ ዕድገት ደረጃዎችን ይረዳሉ<br>• በየደረጃው ሕፃናት ምን ዓይነት ሁኔታ ሊታይባቸው እንደሚችል በመገንዘብ ሕፃናትን ያጫውታሉ | የጨዋታዕድገት ደረጃዎች<br>• ሕፃኑ የማይጫወትበት ደረጃ<br>• ለብቻ የሚጫወትበት ደረጃ | | - በአካባቢአቸው ያሉ ሕፃናት ሲጫወቱ አይተው እንደሆነ መጠየቅ በተለያየ ዕድሜ ደረጃ ያሉ ሕፃናት እንዴት እንደሚጫወቱ ባዩት ላይ ማወያየት ማስረዳት ደረጃዎቹን መጫወቻ በመጠቀም ማሳየት | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>-መጫወቻዎች (ደረጃዎቹን ለማሳየት) | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- በቡድን ጨዋታን ሲያሳዩ ደረጃውን በትክክል |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | ክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • የመስሎ መጫወት ጨዋታን ይለያሉ በመስሎ መጫወት ስር የሚመደቡትን ጨዋታዎች ያውቃሉ<br>• ለመስሎ መጫወት ጨዋታ የጨዋታ ቦታ ማደራጀትን ይረዳሉ፡፡<br>• የመምህርን ሚና በመገንዘብ ይሠራሉ<br>• ጨዋታዎችን በተግባር ያሳያሉ | የጨዋታ ዓይነቶች<br>3.2 መስሎ መጫወት ጨዋታ ምንነት ጠቀሜታ<br>• የመስሎ መጫወት ጨዋታዎች<br>• ለጨዋታው ክፍልን ማደራጀት<br>• የመምህር ሚና<br>• ተግባራዊ ሥራዎች | 4 | -የመስሎ መጫወት ጨዋታን ምንነት መጠየቅና ጥቅሙንም ማወያየት የመስሎ መጫወት ጨዋታ ዓይነቶችን ማስረዳት በልጅነት ከተጫወቷቸው ጨዋታዎች ለናሙና እንዲያሳዩ ማድረግ<br>-በጨዋታው የመምህር ሚና ምን እንደሆነ መጠየቅ<br>-የመምህርን ሚና ማስረዳት<br>-የተመረጡ ጨዋታዎችን ለየቡድኑ መስጠትና ተዘጋጅተው እንዲጫወቱ ማድረግ<br>-በጨዋታ ሂደት አንድ ተማሪ እንደ አፀደ ሕፃናት መምህር ሆኖ እንዲመራ በማድረግ ማስገምገም፡፡ | የማስተማሪያ ጽሑፍ ለመስሎ መጫወት የሚያስፈልጉ መጫወቻዎች | - ጥያቄዎች መጠየቅና ምን ያህል እንደተረዱ መመዘን<br>- ሲጫወቱ መመልከት<br>- የመምህር ሚና የያዘውን ሰው ሲገመግሙ ማዳመጥና ምን ያህል እንደተረዱ መመዘን |
| | | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• የትምህርታዊ ጨዋታን ምንነትና ጥቅም ይረዳሉ | 3.3. ትምህርታዊ ጨዋታዎች<br>• የጨዋታው ምንነትና ጠቀሜታ<br>• የጨዋታው አደረጃጀት | 3 | - ከትምህርታዊ ጨዋታዎች መካከል ጥቂቶቹን ማጫወት ለምሳሌ ፡- እንቆቅልሽ ፣ የጠፋውን ፍልጋ፣ ፐዝል፣ መገጣጠም የማዛመድ ጨዋታዎች ወዘተ | -በአፀደ ሕፃናት ትምህርታዊ ጨዋታዎችን ሲጫወቱ የሚያሳዩ | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- የቡድን ጨዋታዎቻቸውን መመልከትና |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | ክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • በተለያየ የጨዋታ ደረጃ ላይ ያሉትንሕፃናት ማገዝ ይችላሉ | • ከሌሎች ሕፃናት አጠገብ የሚጫወትበት ደረጃ<br>• ከሌሎች ህፃናት ጋር አብሮ የሚጫወትበት ደረጃ | | -በተለያዩ ደረጃዎችን በቡድን መስጠትና ጨዋታውን እንዲያንፀባርቁ ማድረግ | | ማንፀባረቃቸ ውን ማየት |
| 3 | የጨዋታ ዓይነቶችና አመራራቸው | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• የሕፃናት ጨዋታዎችን ማስፋፋት ይችላሉ<br>• የሕፃናት ጨዋታ ምንጮችን በመገንዘብ ሕፃናትን መርዳት ይችላሉ | 3.1 የጨዋታ ምንጮች ወይም ማነሻዎች<br>• የዕለት ተዕለት ኑሮ<br>• አካባቢ<br>• ሙዚቃና ሥነ-ጥበብ<br>• የሕፃናት መፃህፍት ጉብኝት | 2 | - በልጅነት ምን እንደሚወዱ መጠየቅና ጨዋታዎችን እንዴት ይጫወቱ እንደነበር እንዲናገሩ በማድረግ የሕፃናት ጨዋታ መነሻዎችን በማስረዳት ማወያየትና የእነርሱ ጨዋታ በልጅነታቸው መነሻው ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ<br>- ከልጅነት ጨዋታዎቻቸው መካከል መርጠው በቡድን ለመጫወት ለክፍሉ እንዲያሳዩ ማድረግና ምንጩን በመጠየቅ እንዲናገሩ ማድረግ | -የተለያዩ የሕፃናት መፃህፍት<br>-የሥነ-ጥበብ ውጤቶች | - በጥያቄዎች ማሳተፍና መመዘን<br>- የቡድን ጨዋታዎችን መመልከት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • የጨዋታውን አደረጃጀት ይረዳሉ በማደራጀት ሕፃናትን የማጫወት ችሎታ ይኖራቸዋል። <br> • የመምህራን ሚና ይገነዘባሉ <br> • ጨዋታውን በመጫወት ሕፃናትን የማጫወት አቅማቸው ይዳብራል። | • የመምህር ሚና <br> • ተግባራዊ ሥራ | 4 | -ከተጫወቱአቸው መካከል - የተወሰኑትን ጥቅም አስበው እንዲናገሩ ማድረግ <br> - ትምህርታዊ ጨዋታዎች በተለያየ ቦታ ቢከናወኑም በክፍል ውስጥ ለማጫወት ምን መደረግ እንዳለበት ማስረዳት <br> - በትምህርታዊ ጨዋታዎች የመምህርን ሚና መጠየቅና ማወያየት ማስረዳት <br> - ትምህርታዊ ጨዋታዎችን በቡድን እንዲጫወቱ የቤት ሥራ መስጠትና ጨዋታዎችን በማቅረብ እንዲለማመዱ ማድረግ ያቀረቡአቸው ጨዋታዎች እያንዳንዳቸው የሚሰጡትን ጥቅም እንዲናገሩ ማድረግ <br> - እያንዳንዱ እጩ መምህር የተጫወተውን ጨዋታ | ፎቶዎች <br> - ለትምህርታዊ ጨዋታዎች የሚያስፈልጉ መጫወቻዎች | - ጥያቄዎች መጠየቅ <br> - የቡድን ጨዋታዎቻቸውን መመልከትና መመዘን |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ሂደት ጥቅሙን በዝርዝር ጽፎ እንዲያቀርብ ማድረግ | | |
| | | ከዚህ ትምህርት በኂላ እጩ መምህራን<br>• የመገንባት ጨዋታ ምንነትና ባህሪውን ይገነዘባሉ<br>• የጨዋታውን አደረጃጀት ያውቃሉ<br>• የመምህርን ሚና በመገንዘብ በተገቢው ደረጃ መምራት ይችላሉ፡፡<br>• የመገንባት ጨዋታዎችን በመጫወት ይለማመዳሉ፡፡ | 3.4. የመገንባት ጨዋታዎች<br>• ምንነትና ባህሪ<br>• የጨዋታው አደረጃጀት<br>• የመምህር ሚና<br>• የተግባር ሥራዎች | 4 | - የመገንባት ጨዋታ ምን ዓይነት ጨዋታ እንደሆነ ከሌሎች የጨዋታ ዓይነቶች በምን እንደሚለይ መጠየቅ ማወያየት ምንነቱንና ባህሪውን ማስረዳት<br>- ለናሙና ጥቃት የግንባታ ጨዋታዎችን እንዲጫወቱ መጫወቻዎች ማቅረብ መከታተል<br>- አደረጃጀቱንና የመምህር ሚናን ማስረዳት<br>- የመገንባት ጨዋታዎችን በመጫወት እንዲለማመዱ ማድረግናጨዋታዎቹለምን እንደሚጠቅሙ ሕፃናቱን ከምን አኳያ ሊያዳብሩ እንደሚችሉ እንዲጽፉ ማድረግ | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- የመገንባት ጨታ መጫወቻዎች | - የቡድን ጨዋታዎቻቸውን ማየትና መገምገም |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 3.5. እንቅስቃሴአዊ (ስፖርታዊ) ጨዋታዎች<br>• የጨዋታው ባህሪ<br>• አደረጃጀት<br>• የመምህር ሚና<br>• የተግባር | 4 | - ከእንቅስቃሴአዊ ጨዋትዎች መሀረቤን ፣ ሮዚና ፣ ሰብለወንጌል ፣ አረንጓዴ ፣ ሌባና ፖሊስ ወዘተ የተመረጡትን ማጫወተና እንቅስቃደአዊ ጨዋታዎች እንዲሆኑ ባህሪአቸውን ማስረዳት<br>- ለእንቅስቃሴአዊ ጨዋታዎች አካባቢን ያማደራጀትን ሂደት ማስረዳት የመምህር ሚና ምን እንደሆነ በቡድን ተወያይተው እንዲናገሩ ማድረግ<br>- በራሳቸው ምርጫ በቡድን እንቅስቃሴአዊ ጨዋታዎችን እንዲጫወቱና ሕፃናት የሚሰጡትን ጥቅም እንዲጽፉ ማድረግ | ጽሑፍ ለእንቅስቃሴአዊ ጨዋታዎች የሚያስፈልጉ መጫወቻዎች | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- የቡድን ሥራ ውጤታቸውን (ጨዋታውን) መመልከት መገምገም |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• የጨዋታ ድራማን ምንነት፣ ባህሪ በመረዳት ማደራጀትና ማጫወት ይችላሉ፡፡<br>• የመምህር ሚናን በመረዳት ጨዋታ ድራማን መምራት ይችላሉ<br>• ጨዋታ ድራማን በመጫወት ይለማመዳሉ | 3.6 ጨዋታ ድራማ<br>• ምንነትና ባህሪ<br>• መነሻ<br>• አደረጃጀት<br>• የመምህር ሚና<br>• ተግባራዊ ሥራዎች | 4 | - ስለጨዋታ ድራማ ምንነትና ባህሪ መጠየቅና ማወያየት ማስረዳት<br>- የጨዋታ ድራማ መነሻን ማስረዳት አንድ አጭር ተረት መተረክና ወደ ድራማ ለመቀየር የባለ ታሪኮቹን ሚና በማከፋፈል ማሰራት<br>- በጨዋታ ድራማ አደረጃጀት የመምህር ሚናን በቡድን በመወያየት እንዲጽፉ ማድረግና ማወያየት<br>- ተረት መርጠው ጨዋታ ድራማን በቡድን አዘጋጅተው እንደጫወቱ ማድረግ | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- ጨዋታ ድራማን ለማጫወት የሚያስፈልጉ አልባባት መጫወቻዎች | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- የቡድን ሥራ ውጤታቸውን መከታተልና መመዘን |
| 4 | ጨዋታ በቅድመ መደበኛ ሥርዓተ ትምህር ት | • ጨዋታ ዋና ሕፃናትን ማሳደጊያና ማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን ይረዳሉ፡፡<br>• ሥርዓተ ትምህርቱን በመፈተሽ የጨዋታ ቦታን ይረዳሉ፡፡ | 4.1. ጨዋታ እንደማስተማሪያ ዘዴ<br>4.2. ጨዋታ በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ | 4 | - ጨዋታ ዋና ሕፃናትን ማስተማሪያና ማሳደጊያ መንገድ መሆኑ ማወያየትና ማስረዳት<br>- በሥርዓተ -ትምህርቱ ውስጥ ጨዋታ በየፕሮግራሞቹ ውስጥ ያለውን ቦታ እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ ፈትሸው እንዲያወጡ ማድረግና ማስረዳት | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- ሥርዓተ ትምህርት | - ጥያቄዎች<br>- ሥርዓተ ትምህርቱን በመፈተሽ ያገኙትን መመልከት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክ/ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሣሪያ | የምዘና ዘዴዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | መጫወቻዎች | • የመጫወቻዎችን ዓይነቶች ይረዳሉ። <br> • ለጫወታ መጫወቻዎችን መምረጥ ይችላሉ። <br> • በአካባቢ ከሚገኝ ነገሮች መጫወቻዎችን መስራት ይችላሉ። | 5.1. የሕፃናት መጫወቻ ዓይነቶች <br> 5.2. የመጫወቻዎች አመራረጥ | 4 | - የመጫወቻዎችንና የጨዋታ ግንኙነት በመጠየቅ ማወያየት አስፈላጊነታቸውን ማስረዳት <br> - የመጫወቻዎችን አመራረጥ መጠየቅና ማወያየት የመጫወቻዎችን አመራረጥ መስፈርቶች ማስረዳት <br> - መጫወቻዎችን እንዲሰሩ የቤት ሥራ መስጠት | - የማስተማሪያ ጽሑፍ <br> - የተለየ ዕድሜን የሚመጥኑ የመጫወቻ ዓይነቶች | - ጥያቄዎት <br> - የሠሩትን የመጫወቻ ዓይነቶች መመልከት |

## 8. የአካባቢ ትምህርት

የተፈቀደ ጊዜ በሳምንት- 2

የኮርሱ አጠቃላይ ዓላማዎች

ይህንን ኮርስ ካጠናቀቁ በኂላ እጩ መምህራን፦

- የአካባቢ ትምህርትን ትርጉምና አስፈላጊነት ይገነዘባሉ
- ዓላማና ይዘት ይገነዘባሉ፣ በተግባር ላይ ማዋል ይችላሉ፡፡
- ሕጻናትን ከቅርብ አካባቢአቸው ጋር ለማስተዋወቅ ሊጠቀሙ የሚገባቸውን ዘዴዎች ይረዳሉ መጠቀምም ይችላሉ
- ስለ ሕይወት ክህሎቶች አስፈላጊነት ግንዛቤ ይኖራቸዋል ሕጻናት ሊለምዱአቸው የሚያስፈልጉ የሕይወት ክህሎቶችን ይረዳሉ ማለማመድም ይችላሉ
- የአካባቢ ትምህርትን የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን አጠቃቀም ይረዳሉ

**የኮርሱ ይዘቶች**

1. የአካባቢ ትምህርት

    1.1. የአካባቢ ትምህርት ትርጉምና አስፈላጊነት

    1.2. የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሐብቶች

      1.2.1. እንስሳት

      1.2.2. እጽዋት

    1.3. ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች

2. የአካባቢ ትምህርት በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት

    2.1. የአካባቢ ትምህርት ትቅሞች

    2.2. የአካባቢ ትምህርት ዓላማዎች

    2.3. የአካባቢ ትምህርት ይዘቶች

      2.3.1. ከህብረተሰብ ጋር ማስተዋወቅ

      2.3.2. ከህብረተሰብ የሥራ ውጤቶች ጋር ማስተዋወቅ

      2.3.3. ከተፈጥሮአዊ ነገሮች ጋር ማስተዋወቅ

      2.3.4. ከወቅቶች ጋር ማስተዋወቅ

      2.3.5. ከበዓላት ጋር ማስተዋወቅ

        - የልደት በማለትየሕዝብ በዓላት

    2.4. አካባቢን የማስተዋወቂያ መንገዶች

      2.4.1. የማስተዋወቂያ መንገዶ

2.4.2. የማደራጃ መንገዶች

3. የሕይወት ክህሎቶች

3.1. ራስን መጠበቅ

3.2. አካባቢን መጠበቅ

3.3. ማህበራዊ ኑሮን ማዳበር

4. የአካባቢ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

4.1. የመርጃ መሳሪያዎች ዝግጅት
4.2. የመርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | ክፍለ ጊዜ | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • ሕጻናትን የአካባቢ ትምህርት የማስተማር ዓላማዎችን ይረዳሉ<br>• ዓላማዎቹን መግለጽ ይችላሉ | 2.1. የአካባቢ ትምህርት ዓላማዎች | 4 | - በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ከሚሰጡ ይዘቶች ውስጥ አካባቢን የሚመለከቱ እንዳሉበት ማስታወስና ለምን ለሕጻናት መሰጠት እንዳለበት ዓላማውን እንዲናገሩ መጠየቅ ማወያየትና በእያንዳንዱ ዓላማ ላይ በቡድን ተወያይተው መለወጥ ያለበት ካለ እንዲናገሩ በማድረግ ግንዛቤአቸውን ማስፋት | - የማስተማሪያ መጽሐፍ<br>- ዓላማዎቹን የያዙ ለቡድን የሚታደሉ ጽሑፎች | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- የቡድን ውይይታቸውን ውጤት መከታተል |
| | | • ከማህበረሰብ ጋር በማስተዋወቅ ስር የተቀመጡትን ይዘቶች ይለያሉ<br>• ከህብረተሰብ የሥራ ውጤቶች ጋር ማስተዋወቅ በሚለው ክፍል የታቀፉትን ይዘቶች ይለያሉ<br>• ተፈጥሮአዊ ነገሮችን ማስተዋወቅ በሚለው ስር የታቀፉትን ይዘቶች ይለያሉ<br>• ከይዘቱየተቀመጡትን ከዕድሜ ጋር በማገናዘብ አንጻር ትምህርቶችን ማዘጋጀት ይችላሉ | 2.3. የአካባቢ ትምህርት ይዘቶች<br>2.3.1. ከህብረተሰብ ጋር ማስተዋወቅ<br>2.3.2. ከህብረተሰብ የሥራ ውጤቶች ጋር ማስተዋወቅ<br>2.3.3. ከተፈጥሮአዊ ነገሮች ጋር ማስተዋወቅ<br>• እጽዋት<br>• እንስሳት<br>• ሕይወት የሌላቸው ተፈጥሮአዊ ነገሮች<br>2.3.4. ከወቅቶች ጋር ማስተዋወቅ | 10<br>12 | - ሕጻናት ስለአካባቢ ምን ሊያውቁ ይገባል ብ መጠየቅና ማወያየት በቡድን በመወያየት ከሶስቱ አቅጣጫዎች አንጻር ምን መማር እንዳለባቸው እንዲጽፍና እንዲያቀርቡ በማድረግ ማወያየት፡፡<br>- በአራቱም ይዘቶች ስር ስለታቀፉት ንዑስ ይዘቶችና ዓላማ በየቅደም ተከተሉ ማስረዳትና ከአካባቢአቸው ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር እንዲወያዩባቸው ማድረግ<br>- በቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ትምህርት ላይ ይዘቶቹ በየዕድሜው የትና እንዴት እንደተቀመጡ በቡድን እንዲፈጽሙ ማድረግ<br>- ለእያንዳንዱ ይዘት ትምህርት አዘጋጅተው እንዲቀርቡና እንዲለማመዱ ማድረግ<br>- ወቅቶች ላይ በሰው ፣ በእንስሳት ለእጽዋቶች የሚታየውን ለውጥ ቻርት እንዲያዘጋጁ ማድረግ | - በዋናዎቹ ይዘቶች ስር በየዕድሜው ሊቀመጡ የሚገባቸውን ንዑስ ይዘቶች የሚያሳይ ቻርት<br>- ከወቅቶች ጋር በማስተዋወቅ ስር ወቅቶች የሚያሳዩትን ለውጥ በሰዎች፣ በእንስሶች በእጽዋቶች ይይወት በሌላቸው ነገሮች የሚታየውን ለውጥ የሚያሳይ ቻርት | - በውይይት ወቅት ጥያቄዎች መጠየቅና ምን ያህል እንደተረዱ መመዘን<br>- የቡድን ሥራዎቻቸውን ማየት<br>- ትምህርት አዘጋጅተው ሲያቀርቡ መገምገም<br>- የአየር ጸባይ ማሳያ ካላንደር |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | ክፍለ ጊዜ | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2.3.5. ከበዓላት ጋር ማስተዋወቅ<br>- ልደት<br>- የሕዝብ በዓላት | 5 | በአካባቢያቸው የሚከበሩ በዓላትን እንዲያስታወሱ በማድረግ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤትሊከበሩ በሚገባቸው በዓላት ላይ ማወያየትና በዓላትን ለምንና እንዴት ማክበር እንዳለባቸው ማስረዳትበልደትና በጠወሰኑ የሕዝብ በዓላት ላይየቤት ስራ መስጠት | - የአካባቢ እጽዋቶች እንስሳት | |
| | | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን፦<br>• አካባቢን ለሕጻናት ሲያስተዋውቁ ሊጠቀሙባቸው የሚገቡ ዘዴዎችን ይረዳሉ መጠቀምም ይችላሉ<br>• የአካባቢ ትምህርትን በምን አይነት ቦታ ሕጻናትን አደራጅተው ማስተማር እንደሚገባቸው ይረዳሉ፣ በተግባር ላይ ማዋልም ይችላሉ፡ | 2.4. አካባቢን የማስተዋወቂያ መንገዶች<br>2.4.1. ዘዴዎች<br>• ማተኮር<br>• ሙከራ<br>• የሥራ ጨዋታ<br>2.4.2. የማደራጃ መንገዶች<br>• ሽርሽር<br>• በክፍል ውስጥ በተለመደ ሁኔታ<br>• በክፍል ውስጥ የአትክልት ማዕዘን (በግቢም) | 3 | - የአካባቢ ትምህርት ከሌሎች ፕሮግራች ይለያል? ምን ባህሪ አለው? በማለት መጠየቅና ማወያየት ለማስተማር ሊጠቀሙባቸው የሚችሉትን ዘዴዎች በቅደም ተከተል ማስረዳት<br>- ከእያንዳንዱ ዘዴ ውይይት በኋላ ዘዴውን ተጠቅመው ትምህርት እንዲያዘጋጅ እና እንዲለማመዱ ማድረግ<br>- ማንኛውንም ዘዴ በተገኘው ቦታ መጠቀም ይችላል ወፍ? በማለት መጠየቅና ማወያየት የማደራጃ መንገዶችን ማስረዳት እያንዳንዱን መንገድ ተጠቅመው ሊሰሩ የሚሉትን በመጠየቅ ማወያየት | - ርዕስን ሊደግፉ የሚችሉ ስዕሎች<br>- የማስተማሪያ ጽሑፎች | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- የትምህርት አቀራረብና ይዘታቸውን ማየትና መገምገም |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | ክፍለ ጊዜ | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | የሕይወት ክህሎቶች | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን፡-<br>• ስለ ሕይወት ክህሎቶች ይገነዘባሉ<br>• ሕጻናት ራሳቸውን አካባቢአቸውን፣ መጠበቅን እንዲለማመዱ ማድረግ ይችላሉ፡ | 3.1. ራስን መጠበቅ<br>3.2. አካባቢን መጠበቅ<br>3.3. ማህበራዊ ኑሮ መዳበር | 5 | - በሕይወት ክህሎቶች ላይ ማወያየትና ከለጋ ሕጻንነት ዕድሜ ጀምሮ መገንባት እንዳለበት ማስረዳት<br>- ራስን ከመጠበቅ ጀምሮ አካባቢን መጠበቅን፣ ከሰዎች ጋር ያላቸውን ማህበራዊ ግንኙነቶች እንዲያዳብሩ ምን መጠቀም እንዳለባቸው በማስረዳት በየ<br>ዕለት ተግባራት ላይ ትምህርት በማዘጋጀት እንዲያቀርቡ ማድረግ | - የሕይወት ክህሎቶች ወይም የዕለት ተግባር መለማመጃ የቁልፍና የዚፕ የጫማ ፍሬም<br>• ሳሙና<br>• ውሃ<br>• እጅ ውስጥ የሚገባ አቧራ ማንሻ<br>• መጥረጊያ | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- የትምህርት አቀራረባቸውን ከእድሜ አንጻር መስራታቸውን መመልከትና መገምገም |
| 4 | አካባቢን ማስተዋወቂያ መሳሪያ ዎች | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን፡- | 4.1. የመርጃ መሳሪያዎች ዝግጅት<br>4.2. የመርጃ መሳሪያዎች አጠቃቀም | 2 | - የአካባቢ ትምህርትን ለማቅረብ የሚያስፈልጉ መርጃ መሳሪያዎችን በዝርዝር እንዲያቀርቡ የክፍል ሥራ መስጠትና ማወያየት<br>- ከምን እንዴት ሊሰሩ እንደሚሉ ማወያየትና በማቴሪያል ዝግጅት ክፍላቸው እንዲሰሩ የቤት ሥራ መስጠት<br>- የሰሩአቸውን መሳሪያዎች አጠቃቀም በተግባር እንዲያሳዩ ማድረግና ማወያየት | - የአካባቢ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ናሙና<br>- እጩ መምህራን ያዘጋጁአቸው መሳሪያዎች | - የተለያዩ ጥያቄዎች መጠየቅና መገምገም<br>- ያዘጋጁአቸውን መሳሪያዎች አጠቃቀም ሲያሳዩ መከታተልና መገምገም |

## 9.የሕጻናት ቋንቋ መዳበር

ለኮርሱ የተፈቀደ ጊዜ በሳምንት - 2

የኮርሱ አጠቃላይ ዓላማዎች

ከዚህ ኮርስ በኋላ እጩ መምህራን፡-

- እስከ 6 ዓመት ዕድሜ ያሉ ሕጻናትን የቋንቋ መዳበርና የአቀባበል ችሎታ ይረዳሉ
- የሕጻናት ቋንቋ መዳበር ደረጃዎችን በመረዳት እንደየዕድሜ ደረጃው ማስተማር ይችላሉ

ስለ አራቱ የቋንቋ ክህሎቶች ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ ግንዛቤን ይኖራቸዋል ሕጻናት ልምድን እንዲያዳብሩ ማገዝ ይችላሉ

- ቋንቋ ከጨዋታ ጋር ያለውን  ግንኙነት ይረዳሉ ጨዋታን ተጠቅመው ማስተማር ይችላሉ
- የቅድመ መደበኛ መርሀ ትምህርት ለየዕድሜው ያስቀመጣቸውን ብቃቶች ሊማሩ  የሚገባቸውን ይዘቶች ተረድተው መርሀ ትምህርት መጠቀም ይችላሉ፡፡

**<u>የኮርሱ ይዘቶች</u>**

1. የሕጻናት ቋንቋ መዳበር
   1.1. የቋንቋ ትርጉም
   1.2. ቋንቋ በሰው እድገት ላይ  የሚጫወተው ሚና
   1.3. ለቋንቋ መዳበር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ነገሮች
      1.2.6- ዘር

      1.3.2.- አካባቢ

   1.4. የቋንቋ መዳበር
      1.4.1. ከልደት እስከ ስድስት ዓመት
      1.4.2. ከአራት ዓመት እስከ ስድስት ዓመት
2. በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት የቋንቋ ክህሎቶች መዳበር
   2.1. የማዳመጥ ክህሎት
      - ማዳመጥን የማዳበርያ ዘዴዎች
   2.2. የንግግር ክህሎት
      - ንግግርን ማዳበርያ ዘዴዎች
   2.3. የማንበብ ክህሎት
      - ንባብን የማዳበሪያ ዘዴዎች
   2.4. የመጻፍ ክህሎት
      - መጻፍን ማዳበሪያ መንገዶች
   2.5. የቋንቋ ክህሎቶች መዳበርና ለመደበኛ ትምህርት ቤት መዘጋጀት
3. የሕጻናት ተረት
   3.1. የሕጻናት ተረት ምንነት፣ ጥቅሞና አመራረጥ
   3.2. ተረትን የማስተማር ዘዴ
   3.3. ሥዕልን መመልከትና መናገር
4. ፊደላት
   4.1. በየዕድሜው ፊደላትን የማስተዋወቅ ደረጃዎች

4.2. ፊደላትን የማስተማሪያ ዘዴዎች

5. ቃላት

5.1. ቃላትን የማስተማሪያ ዘዴዎች

6. ጨዋታና ቋንቋ

6.1. ጨዋታ ለቋንቋ መዳበር የሚጫወተው ሚና

7. የቅድመ መደበኛ መርሀ ትምህርት

7.1. በቅድመ መደበኛ መርሀ ትምህርት ቋንቋ ዓላማዎችች ይዘቶች፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችና መርጃ መሳሪያዎች፡-

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 1 | የሕጻናት ቋንቋ መዳበር | ከዚህ ትምህርት በኋላ<br>• የቋንቋን ትርጉም ይረዳሉ<br>• ቋንቋ ከተለያዩ የዕድገት ዘርፎች መዳበር አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ይረዳሉ፡፡<br>• ለቋንቋ መዳበር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ነገሮችን ይገነዘባሉ | 1.1 የቋንቋ ትርጉም<br>1.2 ቋንቋ በሰው እድገት ላይ የሚጫወተው ሚና<br>1.3. ለቋንቋ መዳበር አስተዋጽኦ የሚያደርጉት ነገሮች<br>1.3.1. ዘር<br>1.3.2. አካባቢ | | - ቋንቋ ምን እንደሆነና ምን ተግባራት እንዳሉት መጠየቅና ማወያየት ማስረዳትና ተገቢውን አቅጣጫ ማስያዝ፡፡<br>- ቋንቋ ለአካል ለአእምሮ ለማህበራዊ ኑሮ ለስሜት መዳበር የሚጫወተውን ሚና ማስረዳትና ተማሪዎች እንዲወያዩበት ማድረግ<br>- ቋንቋን የመቀበል አቅም ከዘር ሊወረስ እንደሚችል በልዩ ልዩ ምሳሌዎች ማስረዳት ከልምዳቸው እንዲናገሩ ማነቃቃት<br>- የሚጫወቱበት አካባቢና ግንኙነታቸው በቋንቋ መዳበር አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ማስረዳትና ማወያየት | - የማስተማሪያ ጽሑፎች | - ጥያቄዎች መጠየቅ ምን ያህል እንደዘዴ ማረጋገጥ<br>ሙከራ መስጠት |
| | | • የሕጻናት ቋንቋ የመዳበር ሂደትን በየዕድሜው ደረጃ ይገነዘባሉ | 1.4. የቋንቋ መዳበር<br>1.4.1. ከልደት እስከ አራት ዓመት<br>1.4.2. ከአራት ዓመት እስከ ስድስት ዓመት | | - በዕድሜ በገፉ ሰዎችና በሕጻናት ቋንቋ መካከል ምን ልዩነት እንዳለ መጠየቅና ማወያየት እስከ አራት ዓመት በመቀጠልም እስከ አራት እስከ ስድስት ዓመት ያለውን የሕጻናት ቋንቋ ማዳበር ማስረዳት ማወያየት፡- በአካባቢአቸው ከሚያዩት የሕጻናት ቋንቋ መዳበር ጋር እንዲያገናዝቡ ማድረግ | - የማስተማሪያ ጽሑፎች | ልዩ ልዩ ጥያቄዎች መጠየቅ<br>ሙከራ መስጠት |
| 2 | በቅድመ መደበኛ ትምህርት | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን | 2.1. ማዳመጥ<br>• ማዳመጥን የማዳበሪያ | | - ክህሎቶች ምን ማለት እንደሆነ መጠየቅና የቋንቋ ክህሎቶችን ማስረዳት የእያንዳንዱን ክህሎት | - የማስተማሪያ ጽሑፍ | - ጥያቄዎች መጠየቅ |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቤት የቋንቋ ክህሎቶች መዳበር | • የቋንቋ ክህሎቶችን ያውቃሉ<br>• እያንዳንዱን የቋንቋ ክህሎት ማዳበሪያ መንገዶችን ይረዳሉ<br>• የቋንቋ ክህሎቶችን የማዳበሪያ መንገዶችን ተረድተው በተግባር ላይ ማዋል ይችላሉ<br>• የእያንዳንዱን ክህሎት መዳበር አስፈላጊነት ይረዳሉ<br><br>• የቋንቋ ክህሎቶች መዳበርና ለመደበኛ ትምህርት ቤት መዘጋጀት ያለውን ግንኙነት ይረዳሉ | ዘዴዎች<br><br>2.2. ንግግር<br><br>• ንግግርን ማዳበሪያ ዘዴዎች<br>2.3. ማንበብ<br><br>ንባብን የማዳበሪያ ዘዴዎች<br><br>2.4. መጻፍ<br><br>• መጻፍን የማዳበሪያ ዘዴዎች<br><br>2.5. የቋንቋ ክህሎቶች መዳበርና ለመደበኛ ትምህርት ቤት መዘጋጀት | | መዳበር አስፈላጊነት እንዲናገሩ ማድረግ<br>- እያንዳንዱን ክህሎት በቅደም ተከተል ማስረዳትና የማዳበሪያ ዘዴዎችንም እንዲገነዘቡ ማድረግ<br>- በእያንዳንዱ ክህሎት ዘዴዎችን በመጠቀም ትምህርት እንዲያዘጋጁ እና እንዲያቀርቡ የቡድን ሥራ መስጠትና የመገምገሚያ መስፈርት አብሮ በማውጣት በቡድን የሚቀርበውን ትምህርት እንዲገመግሙ ማድረግና ተገቢውን የማሻሻያ ሀሳብ መስጠት<br><br>- ለመደበኛ ትምህርት ቤት መዘጋጀት ማለት ምን እንደሆነና መደበኛ ትምህርት ቤት የሚገባ ልጅ ምን እንደሚጠበቅበት መጠየቅ ማስረዳትና ከእያንዳንዱ የቋንቋ ክህሎት ጋር ያለውን ግንኙነት በመጠየቅ ማወያየት | - የቋንቋ ክህሎቶችን የማስተማሪያ መሳሪያዎች<br><br>- የማስተማሪያ ጽሑፍ ቋንቋን የማስተማር መርጃ መሳሪያዎች | የትምህርት አቀራረብን መመልከትና መገምገም በአራቱ ክህሎቶች ላይ ሙከራ መስጠት<br><br>በጠየቀው መልሳቸውን ከተማሩት ጋር በማገናዘብ መረዳታቸውን ማረጋገጥ |
| 3 | የሕጻናት ተረት | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br><br>• የተረትን ምንነትና አመራረጥ ይረዳሉ<br>• ተረት ለሕጻናት የማስተማር ዘዴን በመገንዘብ ተረትን መርጠው የማስተማር | 3.1. የተረት ምንነትና ተረትን አመራረጥ<br><br>3.2. ለሕጻናት ተረትን የማስተማር ዘዴ<br><br>3.3. ሥዕልን መመልከትና መናገር | | - አንድ አጭር ተረት መተረክና ስለተረት ምንነት ማስረዳት፣ ጥቅሙን መጠየቅ ማስረዳት<br>- ተረቶች ብዙ አይነት እንደሆኑና ለየእድሜ የሚመጥነውን ተረት እንዲመረጡ በቡድን የተረት መጽሐፍት መስጠት የመረጡትን ተረት እንዴት ሊመርጡት እንደቻሉ መጠየቅና ማወያየት | - የተረት መጽሐፍ<br>- የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- የተረት አቀራረብ ሊደግፉ የሚችሉ አሻንጉሊቶች | ተረትን ሲያቀርቡ መከታተልና መገምገም<br><br>የተለያዩ ጥያቄዎች |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ችሎታ ይኖራቸዋል | | | - ተረትን የመምረጫ መስፈርቶችን ማስረዳት<br>- ለሕጻናት ተረት እንዴት እንደሚተረክ ተርኮ ማሳየት ተረትን ለሕጻናት የማቅረቢያ ዘዴዎችን ማስረዳት የዕድሜ ክልል ለይቶ መስጠትና ተረቶችን በትንንሽ ቡድኖ መርጠው በማዘጋጀት እንዲያቀርቡ ማድረግና መገምገም<br>- ለሕጻናት የሚያስ ፈልጉ የሥዕል አይነቶችን ማስረዳትና ሥዕልን የመመልከትና የመናገር ተግባር የሚሰጠውን ጠቀሜታ እንዲገነዘቡ ማድረግ<br>- አንድ ናሙና ትምህርት ሥዕልን በመመልከት ላይ ማሳየትና ሥዕሎችን መርጠው ትምህርት አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ማድረግ | - ሥዕልን ለመመልከት ትምህርት የሚያገለግሉ የተለያዩ ሥዕሎች | መጠየቅ<br>የቡድን ሥራቸውን መገምገም<br>ትምህርት ሲያቀርቡ ማየትና መገምገም<br>ሙከራ መስጠት |
| 4 | ፊደላት | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን፦<br>• ፊደላትን ለሕጻናት የማስተማር ደረጃዎችንና ዘዴዎችን ይረዳሉ | 4.1.በየዕድሜው ፊደላትን የማስተዋወቅ ደረጃዎች<br>4.2. ፊደላትን | | - ፊደላትን ለማስተዋወቅ በየዕድሜው ሊተኮርበት የሚገባውን ማስረዳትና ማወያየት<br>- ፊደላትን የማስተማሪያ ዘዴዎችን በቅደም ተከተል ማስረዳት<br>- ናሙና ትምህርቶችን ለየዕድሜው ማሳየትና ለየዕድሜው ትምህርት | - የፊደል ሰሌዳ<br>- የፊደል ቻርቶች<br>- የፊደል ፓዝሎ<br>- ፍሬዎች ቆርኪዎች<br>- በፊደል | - ጥያቄዎች መጠየቅና መረዳታቸውን ማረጋገጥ<br>- ትምህርት ሲያቀርቡ |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የማስተማሪያ ዘዴዎች<br>• መዘመር<br>• ተረት<br>• ሶስት ደረጃ የማስተማር ዘዴ | | አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ የቤት ስራ መስጠትና መገምገም<br>- በየዕድሜው ፊደልን ለማስተዋወቅ የሚተኮርባቸውን ይዘቶች በሰንጠረዥ እንዲያዘጋጁ ማድረግ | ብሎኮች<br>-ፊደል የተጻፈባቸው ክዩቦች<br>ናሙናየየዕድሜው ፊደል ይዘቶችበሰንጠረ በሰንጠረዥ | መከታተል ና መገምገም |
| 5 | ቃላት | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን፡-<br>• ቃላትን የማስተማሪያ ዘዴዎች ይረዳሉ | 5.1. ቃላትን የማስተማሪያ ዘዴዎች<br>• ሥዕል<br>• ጉብኝት<br>• ሶስት ደረጃ የማስተማሪያ ዘዴ<br>• መዝሙር<br>• ተረቶች | | - በፊደላት ቃላትን እንዴት መመስረት እንደሚቻል ምን መጠቀም እንደሚያስፈልግ መጠየቅና ማወያየት<br>- ቃላትን የማስተማሪያ ዘዴዎችን በቅደም ተከተል ማስረዳትና እያንዳንዱን ዘዴ በመጠቀም ትምህርት እንዲያዘጋጁ ማድረግ በርስ በርስ መማር እንዲያቀርቡት ማድረግ | - ቋንቋ ሰቃቢ ፊደሎች የፊደል ብሎኮች<br>- በክብሪት ቤት ላይ የተለጠፉ ፊደሎች ወዘተ. | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- ትምህርት አዘጋጅተ ው ሲያቀርቡ መከታተል መገምገም<br>ሙከራ መስጠት |
| 6 | ጨዋታና ቋንቋ | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን፡-<br>• ጨዋታና የቋንቋ መዳበር ያላቸውን ግንኙነቶች ይገነዘባሉ<br>• ጨዋታ ለቋንቋ መዳበር የሚጫወተውን ሚና ይረዳሉ ጨዋታን እንደማስተማሪያ ዘዴ | 6.1. ጨዋታ ለቋንቋ መዳበር የሚጫወተው ሚና<br>• የጨዋታና የቋንቋ ግንኙነት<br>• ጨዋታ ቋንቋን እንደማዳበሪያ ዘዴ | | - ጨዋታና ቋንቋ በሕጻናት ያላቸውን ግንኙነት መጠየቅና ማስረዳት<br>- አንድ የሕጻናት ጨዋታን እንዲጫወቱ በማድረግ ለቋንቋ መዳበር የሚሰጠውን ጠቀሜታ መጠየቅና ማወያየት የሕጻናት<br>- ጨዋታ ቋንቋን ላበር የሚጫወተውን ሚና ማስረዳት በራሳቸው የፈለጉትን ጨዋታ መርጠው እንደሚጫወቱ ሁኔታዎችን በማመቻቸት እንዴት | - መጫወቻ መሣሪያዎች<br>- የማስተማሪያ ጽሑፎች | - ጥያቄዎች<br>- ጨዋታ ሲቻወቱ መመልከት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መጠቀም ይችላሉ፡፡ | | | ቋንቋና ማስተማሪያ ዘዴ ሊሆን እንደሚችል ማስረዳት<br>- የተለያዩ ጨዋታዎችን በቡድን በመጫወት ለቋንቋ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ማስጨበጥ<br>- | | |
| 7 | የቅድመ መደበኛ መርሀ ትምህርት | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን፡-<br>• ቋንቋ ትምህርት በቅድመ መደበኛ ትምህርት ሲለበስ ያለውን ቦታ (የይዘት ቅንጅትን) ይረዳሉ መርሀ ትምህሩን መጠቀም ይችላሉ | 7.1. በቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ - ትምህርት የቋንቋ ዓላማዎች፣ ይዘቶች የማስተማሪያ ዘዴዎችና መርጃ መሳሪያዎች | | - መርሀ ትምህርቶችን ከቡድን እንዲመለከቱ ማድረግ ቋንቋን በተመለከተ ያለውን፣ ዓላማ በየዕድሜው ይዘኀቹን የማስተማሪያ ዘዴዎችን እና መርጃ መሣሪያዎችን በማውጣት እንዲተቹበትና እንዲወያዩበት ማድረግ<br>- አጠቃቀሙን ማሳየትና ናሙና ትምህርት እንዲያዘጋጁ ማድረግ | - የቅድመ መደበኛ መርሀ ትምህርት<br>- የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- ትምህርት ሲያቀርቡ መመልከት |

## 10.የሥነ- ስእልና ቅርፃ ቅርፅ ትምህርት

ለኮርሱ የተመደበው ጊዜ በሳምንት -2

የኮርሱ አጠቃላይ አላማዎች

ይህንን ኮርስ ካጠናቀቁ በኋላ እጩ መምህራን

- ስለ ስነ- ስእልና ቅርፃ ቅርረፅ መሠረታዊ እውቀት ይኖራቸዋል
- የስነ-ስእልና ቅርፃ ቅርፅን ትርጉምና አስፈላጊነት ይገነዘባሉ
- የስን ስእልና ቅርፃ ቅርፅ በሕፃናት ሁለንተናዊ እድገትና መዳበር ላይ የሚዳብር ከተውን አስተዋጽኦ ይረዳሉ
- የስን- ስእልና ቅርፃ ቅርፅ ትምህርትን በማቅረብ የሕፃናት ትናናንሽየእጅ ጡንቻዎች እንዲዳብሩ እገዛ ማድረግ ይችላሉ፡፡
- የስነ ስእልና ቅርፃ ቅርፅ ትምህርትን ለሕፃናት እንዴት ማቅረብ እንዳለባቸው ተረድተው በተግባር መተረጎም ይችላሉ፡፡
- በትምህርት ሚኒስቴር የዘጋጀውን መርሀ-ትምህርት ይረዳሉ መጠቀምም ይችላሉ፡፡

**የኮርሱ ይዘቶች**

1. በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት የስነ-ስእልና ቅርጻ ቅርፅ ትምህርት
   1.1. የስነ-ስእልና ቅርፃ ቅርፅ ትምህርት
   1.2. የስነ-ስእልና ቅርርፃ ቅርፅ ትምህርት አላማና ይዘት
   1.3. የዲዛይን መሠረቶች
      - መስመር
      - ቴክስቼር
      - ፎርም
      - ቅርፅ
   1.4 የቀለም አይነቶች
   1.5 የሕፃናት የፈጠራ ስራ አጀማመርና እድገት
      - መሞነጫጨር
      - ምልክት ሰጪ
      - የተፈጥሮ ግንዛቤ
2. የሕፃናት የፈጠራ ስራ ይዘቶች
   2.1. የቅብ ስራ
      - የቡርሽ ቅብ
      - የስፖንጅ ቅብ
      - የሲባጎ ቅብ
      - የጣት ቅብ

- በመርጨት መቀባት
- የተግባር ስራ

2.2. ስእል መሳል

- ስእል የመሳል ደረጃዎች

2.3. የእጅ ስራ

2.3.1. መበጫጨቅ

2.3.2. በመቀስ መቁረጥ

2.3.3. መቆራረጥና መለጣጠፍ (collage &Mosaic)

- ወረቀት
- ቅጥላ ቅጠሎችን መጠቀም
- የተግባር ስራ

2.3.4. የጭቃ ስራና ፔፐር ማሼ

2.4. ህትመት

2.4.1. የተለያዩ የህትመት አይነቶች

- የሲባጎ
- የጣትና የእጅ ህትመት
- የድንች ህትመት
- የቅጠል ህተመት
- የእግር ህትመት
- የተግባር ስራ

2.5. ሽመናና ስፌት

- የወረቀት ሽመና
- የክር ሽመና
- የወረቀት ስፌት
- የተግባር ስራ

3. ስነ-ስእልና ቅርፃ ቅርፅን የማስተማር ዘዴ

3.1. የክፍል አደረጃጀት

3.2. የማስተማሪያ መሳሪያዎች

3.3. የማስተማሪያ ዘዴዎች

4. የቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ትምህርት

4.1. የስነ-ስእልና ቅርፃ ቅርፅ ይዘቶች በመርሃ ትምህርት

## የስነ- ስእልና ቅርፃ ቅርፅ ትምህርት

| ተ.ቁ | ርእስ | ዓላማ | ይዘት | ክፍል ጊዜ ብዛት | የማስተካከያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመረጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት የስነ-ስእልና ቅርፃ ቅርፅ ትምህርት | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• የስነ-ሥዕልና ቅርጻ ቅርጽ ትምህርት አስፈላጊነትን ይረዳሉ<br>• የስነ ስእልና ቅርጻ ቅርፅ ትምህርትን አላማና ይዘቶች ይገነዘበሉ<br>• የዲዛይን መሰረቶች ይለያሉ በተግባር ስራ ላይም ይጠቀምባቸዋል፡፡ | 1.1 የስነ-ስእልና ቅርፃ ቅርጻ ቅርፅ ትምህርት ትርጉምና አስፈላጊነት<br>1.2 የስነ-ስእልና ቅርጻ ቅርፅ ትምህርት አላማና ይዘት<br>1.3 የዲዛይን መሠረቶች<br>• መስመር<br>• ቴክስቸር<br>• ፍግም<br>• ቅርፅ<br>1.4 የቀለም አይነቶች<br>1.5 የህፃናት የፈጠራ ስራ | | - የስነ ስእልና ቅርጻ ቅርፅ ትምህርትን ምንነት መጠየቅ እንደነገሩ ማነቃቃት ማስረዳት<br>- ከሕፃናት እድገትና መዳበር የስነ ስእልና ቅርጻ ቅርጽን አስፈላጊት መጠየቅ፣ማወያየት ማስረዳት<br>- ስነ-ስእልና ቅርጻ ቅርፅን ለምን ማስተማር አስፈለገ? ምን ምን የሚማሩ የመስላችሁዋል? በማለት መጠየቅና መወያየት አላማውንና ይዘቱን በቅደም ተከተል ማስረዳት<br>- ስለዲዛይን መሠረቶች ማስረዳት ናሙናዎችን በማሳየት ማወያየትና ከእለት ተእለት ሁኔታዎች ጋር በማያያዝ በምሳሌ በመንገር እንዲረዱ ማድረግ መስመርና ቅርፃቸውን ማስራት<br>- የቀለም አይነቶችን በናሙና ማሳየትና የቱ ቀለም ከየቱ ጋር ቢደባለቅ ምን ሊሰጥ እንደሚችል በተግባር እንዲሞክሩ ማድረግ፣<br>- የህፃናት የፈጠራ ስራ አጀማመር እድገትን ማስረዳትና እያንዳንዱን የእድገት ደረጃ በስእል ደብተራቸው እንዲሰሩ ማድረግ<br>በሕፃናት የተሰሩ ስራዎችን ማሳየት | - የማስተማሪያ ጽሁፍ<br>- የማስተማሪያ ጽሐፍ<br>- የተዘጋጁ የዲዛይን መሠረቶች ናሙና<br>- የውሃ ቀለም አይነቶች<br>- የእርሳስ ከለር<br>- የስእል ደብተር<br>- እርሳስ የውሃ ቀለም<br>- ቡርሽ<br>- የሕፃናት ስራ | - ጥያቄዎች መጠየቅ |

| ተ.ቁ | ርእስ | ዓላማ | ይዘት | ክፍል ጊዜ ብዛት | የማስተካከያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመረጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አጀማመርና እድገት<br>• መሞነጫጨርና<br>• ምልክት ሰጪ<br>• የፈጥሮ ግንዛቤ | | | | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- በተግባር የሰሩትን ማየት ሙኩራ መስጠት |
| 2 | የሕፃናት የፈጠራ ስራ ይዘቶች | ከዚህ ትምህርት በኂላ እጩ መምህራን<br>▪ የቅብ ስራን ምንነትና የተለያዩ የቅርብ ስራ ይዘቶችን ይለያሉ<br>▪ የቅብ ስራ አይነቶችን በተግባር ይሞክራሊ<br>▪ ስእል የመሳል ደረጃዎችን ይረዳሉ<br>▪ ስእል መሳልን በመለማመድ ለሕፃናት ለማስተማር ተነሳሽነት ይኖራቸዋል<br>▪ በእጅ ስራ ስር የታቀፈቱን ስራዎች ይለያሉ<br>▪ መቦጫጨቅና መቁረጥን በተግባር ይሠራሉ | 2.1 የቅብ ስራ<br>▪ የቡርሽ ቅብ<br>▪ የሲባጎ ቅብ<br>▪ የስፖንጅ ቅብ<br>▪ የጣት ቅብ<br>▪ በመርጨት መቀባት<br>▪ የተግባር ስራ<br>2.2 ስእል መሳል<br>▪ ስእል የመሳል ደረጃዎች<br>2.3 የእጅ ስራ<br>2.3.1 መቦጫጨቅ<br>2.3.2 በመቀስ መቁረጥ | | - የቅብ ስራን ምንነት ያወቁ እንደሆን መጠየቅ ማወያየት እያንዳንዱን የቅብ ስራ ይዘት ናሙና በማሳየት ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ<br>- እያንዳንዱን የቅብ ይዘት በልሙጥ ወረቀት ላይ እንዲሞክሩ ማድረግ<br>- ስእልን በማሳየት ስለሚያዩት ስእል የተሰማቸውን እንዲናገሩ ማድረግ ስእል የመሳል ደረጃዎችን ማስረዳት<br>- ለናሙና ስእሎችን ማሳየት<br>- እያንዳንዳቸው ስእል መሳልን እንዲሞክሩ ማድረግ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ስእል መሳል ምን እንደሆነ እንዴት ህፃናት እንደሚሳሉ ቀደም ሲል ሕፃናት የተማሩትን በማስታወስ እንዲሰሩ ማድረግ ዘዴውን ማስረዳት<br>- በእጅ ስራ ስራ ስለሚከናወኑት | ▪ ቡርሾች<br>▪ ስፖንጅ<br>▪ ሲባጎ<br>▪ ልሙጥ ወረቀት/የስእል ደብተር/<br>▪ የቅብ ስራ ናሙናዎች የውሃ ቀለሞች<br>▪ የተሳሉ ስእሎች<br>▪ ልሙጥ ወረቀት<br>▪ እርሳስ<br>▪ ከለሮች | ▪ ጥያቄዎች መጠየቅ<br>▪ በተግባር የሠሩትን ማየትና መገምገም<br>▪ ጥያቄዎች መጠየቅና ማወያየት<br>▪ የሰሩትን ናሙና መመልከት<br>▪ ሙከራ መስጠት |

| ተ.ቁ | ርእስ | ዓላማ | ይዘት | ክፍል ጊዜ ብዛት | የማስተካከያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመረጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ንዑስ ይዘቶች ማስረዳትና ማሳየት መቦጫጨቅንና በመቀስ መቁረጥን እንዲሞክሩ በማድረግ ለህፃናት እንዴት እንደሚያቀርቡ ማስረዳት ማሳየት | | |
| 3 | | ▪ የመቆራረጥና የመለጣጠፍ ተግባርን ይረዳሉ<br>▪ መቆራረጥና መለጣጠፍን በተግባር ይሞክራሉ | 2.3.3 መቆራረጥና መለጣጠፍ<br>▪ ወረቀት<br>▪ ቅጠላ ቅጠሎችን መጠቀም<br>▪ የተግባር ስራ | | - የመቆራረጥና መለጣጠፍን ምንነት ናሙና ሥራ በማሳየት ማስረዳት እንዴት እንደሚሰራ ማሳየት<br>- ወረቀትንና ቅጠላ ቅጠሉን በመጠቀም እንዲለጣጥፍ አስፈላጊውን ማቴሪያል ማቅረብና በተግባር እንዲሞክሩ ማድረግ | - ወረቀት<br>- ቅጠሎች ኮላ | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- የሥራ ውጤቻውን ማየት<br>- |
| | | ▪ የጭቃ ሥራንና ፔፐር ማሴን ይረዳሉ በተግባር ይሰራሉ | 2.3.4. የጭቃ ሥራና ፔፐርማሼ | | - የጭቃ ሥራን ምንነት ማስረዳትና ከጭቃ የተሰሩ ናሙናዎችን ማሳየት ጭቃ እንዴት እንደሚቦካ ደረጃዎችን ማሳየት እንዲያቦኩ ማድረግ የተቦካው በሚደርስበት ጊዜ ሕጻናት እንዴት እንደሚጠቀሙበት ማሳየትና እንዲሰሩ ማድረግ<br>- ፔፐር ማሼንም እንደጭቃስራው ማስረዳትና በተግባር ማሳየት ናሙናዎችን ማሳየትና እንዲሰሩ ማድረግ | - ቀይ አፈር<br>- የላስቲክ ባሊ<br>- ላስቲክ<br>- መዘፍዘፊያ የተቆራረጡ ወረቀቶች ኮላ (ሙቅ)<br>- የፔፐር ማሺ ስራ ናሙና | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- የተሰሩ ሥራዎችን ማየት |
| | | ▪ የህትመት ሥራ ምንነትን ይገነዘባሉ<br>▪ ህትመትን በተግባር መስራት ይችላሉ | 2.4. ህትመት<br>2.4.1 የለያዩ የህትመት አይነቶች<br>▪ የሲባጎ<br>▪ የጣትና የእጅ ህትመት<br>▪ የድንች ህትመት<br>▪ የቅጠል ህትመት<br>▪ የእግር ህትመት | | - ህትመት በቅደመ መደበኛ ትምህርት ቤት አንዱ ተግባር እንደሆነ ማስረዳት<br>- የተዘጋጁ ናሙናዎችን በማሳየት የሕህተመት አይነቶችን እንዲረዱ ማድረግ<br>- ሁሉንም አይነት ህትመት እንዲሰሩ ማድረግና ግንዛቤአቸውን ማስፋት<br>- ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት | - ድንች<br>- ከተር<br>- ቅጠል<br>- ቀለሞች<br>- ለህትመት ሥራ የሚያስፈልጉ ሌሎች ነገሮች<br>- የሽመና ናሙና ስራዎች<br>- ወረቀት | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- በተግባር የመረዳትን ማየት |

| ተ.ቁ | ርእስ | ዓላማ | ይዘት | ክፍል ጊዜ ብዛት | የማስተካከያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመረጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ▪ ሽመናና ስፌት ሥራን እንዴት እንደሚያከናው ይረዳሉ<br>▪ በተግባር ይሰራሉ | የተግባር ስራ<br>2.5. ሽመናና ስፌት<br>▪ የወረቀት ሽመና<br>▪ የክር ሽመና<br>▪ የወረቀት ስፌት<br>▪ የተግባር ሥራ | | እንዴት መስራት እንዳለባቸው ማስረዳት<br>- የሽመናና ስፌት ሥራ ውጤቶችን በማሳየት ማስረዳት ናሙናዎችን አገላብጠው እንዲያዩ በማድረግ እንዴትና ከምን እንደተሰራ ማስረዳት<br>- የሽመና አይነቶችን በተረዱት መሰረት እንዲሰሩ አስፈላጊ ማቴሪያሎችን ማቅረብና በተግባር እንዲሰሩ ማድረግ<br>- የወረቀት ስፌትን ቀዳዳ በዲዛይን በማውጣት መስጠትና እንዲሰፉ ማድረግ ያለ ዱልዱም መርፌ የወረቀት ስፌት ለሕጻናት እንደማዋካናውንም ማስረዳት | - ክር<br>- ክላሰር<br>- ዱልዱም መርፌ | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- የሥራ ውጤቶቻቸ ውን ማየት |
| 3 | በስነሥዕል ና ቅርጻ ቅርጽ ትምህርት ን የማስተማ ር ዘዴ | ▪ የስነ ሥዕልና ቅርፃቅርስ ክፍል አደረጃጀትን ይረዳሉ<br>▪ የስነ ሥዕልና ቅርፃቅርስ ማስተማሪያመሳሪያ ዎችንና የማስተማሪያ ዘዴዎችን ይለያሉ | 3.1. የክፍል አደረጃጀት<br>3.2 የማስተማሪያ መሳሪያዎች<br>3.3. የማስተማሪያ ዘዴዎች | | - ስነ ሥዕልና ቅርጻ ቅርጽ ይዘቶችን ለማስተማር የክፍል አደረጃጀትን በተግባር ማሳየት<br>- ከስነ ሥዕልና ትርጻ ቅርጽ የሚያስፈልጉ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ማሳየትና አደረጃጀታቸውን ማስረዳት<br>- ለአንድ ክፍለ ጊዜ የሌሰን ፐላን አዘገጃጀትና የማስተማሪያ ዘዴ ማስረዳት | - ለስነ ሥዕልና ቅርጻ ቅርጽ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች | - ክፍል እንዲያደራጁ በማድረግ ማየት<br>- የተዘጋጀውን ሌሰን ፐላን ሲያስተምሩ በት ማየትና መገምገም |
| 4 | የቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ትምህርት | ▪ በቅድመ መደበኛ ስርዓተ ትምህርትየስነ-ስዕልና ቅርፃቅርፅ ይዘቶችን ይረዳሉ | 4.1. በመርሀ ትምህርቱ የስነ ሥዕልና ቅርጻ ቅርጽ ይዘቶች | | - መርሀ ትምህርቱን እንዲፈትሹና ከስነ ሥዕል ጋር የተያያዙ ይዘቶችን በማውጣት በሰንጠረዥ እንዲያስቀምጡ በማድረግ መርሀ ትምህርቱ እንዲመረምሩ ማድረግ | | - |

## 11.ቅድመ ሂሳብ

ለኮርሱ የተፈቀደው ጊዜ በሳምንት 2 ፔሬድ

የኮርሱ አጠቃላይ ዓላማዎች

ይህን ኮርስ ካጠናቀቁ በኂላ እጩ መምህራን፡-

- የሂሳብ ትምህርትን አስፈላጊነት ይረዳሉ
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ሊከናወኑ የሚገባቸውን የሂሳብ ትምህርት ዓላማዎችና ይዘቶች ለይተው ያውቃሉ፡፡

ቅድመ ሂሳብን ማቀድና መተባበር የሚያስችል ችሎታ ይኖራቸዋል

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ሲለበስ ላይ ሂሳብ ያውን ቦታ ይገነዘባሉ መርሀ ትምህርቱን ተጠቅመው የመስራት ችሎታም ይኖራቸዋል፡፡

**የኮርሱ ይዘቶች**

1. ቅድመ ሂሳብ ለሕጻናት ሁለንተናዊ መዳበር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ፣
    1.1. የሂሳብ ትምህርት አስተዋጽኦ
2. በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት የቅድመ ሂሳብ ትምህርት ዓላማዎች
    2.1. የሂሳብ ትምህርት ዓላማዎች
3. በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት የቅድመ ሂሳብ ትምህርት ይዘቶች
    3.1. በዓይት መመደብ፣ በስርዓት መደርደር
    3.2. ቁሳቁሶችን ማወዳደር፣ ማዛመድ
    3.3. የቅርጸ ቅርጽ ጽንሰ ሀሳብ
    3.4. የመጠን ጽንሰ ሀሳብ
    3.5. የመለካ ጽንሰ ሀሳብ
    3.6. የጊዜ ጽንሰ ሀሳብ
    3.7. የቁጥርና አሀዝ ጽንሰ ሀሳብ
4. የቅድመ መሂሳብ ትምህርት እቅድ
    4.1. የእቅድ አስፈላጊነት አስታቀጽ
    4.2. ማቀድና ማስተማር
5. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መርሀ ትምህርት
    5.1. በቅድመ መደበኛ መርሀ ትምህርት የቅድመ ሂሳብ ዓላማዎች
    5.2. በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት የቅድመ ሂሳብ ትምህርት ይዘቶች

# የቅድመ ሂሳብ ትምህርት

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የቅድመ ሂሳብ ትምህርት ለሕጻናት መዳበር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን፡-<br>• የሂሳብ ትምህርት ለሕጻናት መዳበር የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ይገነዘባሉ፡፡ | 1.1. የሂሳብ ትምህርት አስተዋጽኦ በሕጻናት ሁለንተናዊ ዕድገት | | - ስለሕፃናት መዳበር ዘርፎች መጠየቅና ለመዳበራቸው ምን ምን ነገሮች አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ መጠየቅ ማወያየት<br>- የሂሳብ ትምህርት ከሕጻናት የአእምሮ መዳበር ጋር ያለውን ግንኙነትና የሚበረክተውን አስተዋጽኦ እንዲገነዘቡ ማድረግ | - የማስተማሪያ መጽሐፍ | - ጥያቄዎች መየጠየቅ |
| 2 | በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት የሂሳብ ትምህርት ዓላማዎች | • ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት የሂሳብ ትምህርት ዓላማዎችን ይገነዘባሉ | 2.1. የሂሳብ ትምህርት ዓላማዎች | | - የሂሳብን ጥቅም መጠየቅና ማወዳየት፡፡ የሂሳብ ትምህርት ዓላማዎችን በቅድም ተከተል ማቅረብና ማወያየት ማስረዳት<br>- እያንዳንዱን ዓላማ ከሕጻናት መዳበር ጋር እንዲያገናኙና እንዲወያዩ በቡድን የክፍል ሥራ መስጠትና አቅጣጫ ማስያዝ | - የማስተማሪያ ጽሑፍ | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- የቡድን ሥራቸውን ሲያቀርቡ መገምገም<br>- ሙከራ መስጠት |
| 3 | የቅድመ ሂሳብ ትምህርት ይዘቶች | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• የሂሳብ ትምህርት ይዘቶችን ይለያሉ<br>• የሂሳብ ትምህርት ይዘቶችን ከየእድሜው ጋር ማገናዘብ ይችላሉ<br>• የቦታ ጽንሰ ሀሳብን ይገነዘባሉ<br>• ሕጻናትን ከቦታ ጋር ማስተዋወቅ ይችላሉ<br>• የቅርጸ ቅርጽ መጠን | 3.1. ቁሳቁሶችን በአይነት መመደብ በስርዓት መመደብ<br>• ስብስብ<br>3.2. ቁሳቁሶችን ማወዳደርና ማዛመድ<br>• በስብስብ<br>• አንድላንድ በማዛመድ<br>3.3. የቦታ ጽንሰ ሀሳብ<br>- ላይ-ታች<br>- ውስጥ- ውጪ | | - ስለእያንዳንዱ ይዘት የሚያውቁትን መጠየቅና ማወያየት ማስረዳት<br>- እያንዳንዱን ይዘት ከተረዱ በኋላ የተግባር ስራ እንዲሰሩ በማድረግ መረዳታቸውን ማጠናከር<br>- እያንዳንዱን ይዘት በማስተዋወቅ ጊዜ ከዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር እንዲያያይዙ መጠየቅና ማወያየት<br>- የእያንዳንዱን ይዘት ንዑስ ይዘቶች ከዕድሜ ጋር እንዲያያይዙ መጠየቅና | - የማሪያሞንቴ ሶሪ የሂሳብ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች<br>- አሸዋ<br>- ፍሬዎች<br>- ቆርኪዎች<br>- የሚሰፈሩ ጠጣር ነገሮች<br>- ውሃ<br>- የመለኪያ ጥብጣቦች | |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| | | ጽንሰ ሀሳብን ይለያሉ<br>• ቅርጽና መጠንን በየደረጃው ለሕጻናት ማስተማር ይችላሉ<br><br>• የመለካትን ጽንሰ ሀሳብ ይረዳሉ<br>• ሕጻናትን መለካትን ማለማመድ ይችላሉ | - ፊት- ኋላ<br>- ግራ -ቀኝ<br>- ጎን ፣አጠገብ<br>- እሩቅ -ቅርብ<br>3.4. ቅርጸ ቅርጽ<br>- ጎነ- ሶስት<br>- ጎነ -አራት<br>- ካሬ<br>- ክብ<br>- ሞላላ<br>- ጎነ-አምስት<br>3.5 መጠን<br>- ብዙ -ጥቂት<br>- ትልቅ ትንሽ<br>- ረዥም- አጭር<br>- ቀጭን - ወፍራም<br>- ሰፊ - ጠባብ<br>- ቀላል- ከባድ<br>3.6. መለካት<br>• ርዝመት<br>• ፈሳሽን<br>• ጠጠር ነገሮች መስራትና<br>• የተግባር ስራ<br>3.7. ጊዜ<br>• ዛሬ - ነገ<br>• ቀን - ሌሊት<br>• የሳምንቱ ቀናት<br>• የዓመቱ ወራት<br>• አሁን- በኋላ<br>• የቁርስ፣ ምትክ፣ የምሳ ሰዓት | | ማስረዳት<br>- ለእያንዳንዱ ይዘት አስፈላጊ የሆኑትን መርጃ መሳሪያዎች ዝርዝር ማሳወቅ<br><br>- ለይዘቶቹ የሚያስፈልጉትን መርጃ መሳሪያዎች በመርጃ መሳሪያዎች ማምረቻ ክፍለ ጊዜ እንዲያመርቁ መጠቆም<br>- በአጠቃላይ የመርጃ መሳሪያዎቹን አጠቃቀም ማስረዳት | - የመለኪያ ገመድ<br>- ተንቀሳቃሽ ቁጥሮች<br>- የቁጥር ፑዝሎት<br>- የውሀ መያዣ ዕቃ ክዳኖች<br><br>- የክብሪት ቤት ቁጥሮች<br>- መጠንና ቁጥርን የማዛመድ ፑዝል | |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍል ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • የጊዜ ጽንሰ ሀሳብን ይለያሉ<br>• ሕጻናትን ደረጃቸው በሚፈቅደው ከጊዜ ጋር ማስተዋወቅ ይችላሉ<br>• የቁጥርና የአሃዝን ልዩነትና ጠቀሜታ ይረዳሉ<br>• መቁጠርን፣ ቁጥርና መጠን የማገናኘትን ሂደት ይረዳሉ ሕጻናትን የማሰራት ችሎታ ይኖራቸዋል | • የተግባር ሥራ<br><br>3.8. ቁጥርና አሀዝ<br><br>• መቁጠር<br>• ከስብስብ ጋር<br>• በተለያየ አቅጣጫ መቁጠር<br>• የተቆጣሪ ነገሮችን መጠን ማገናዘብ<br>• መጠንና አሀዝ ማዛመድ<br>• የቁጥር አመሰራረት<br>• ቁጥሮችና አሀዝን<br>• መደመር መቀነስ<br>• የተግባር ስራ | | | | |
| 4 | ቅድመ ሂሳብን ማቀድና ማስተማር | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br><br>• የእቅድን አስፈላጊነት ይረዳሉ አስተቃቀድ ሂደቱን ይገነዘባሉ<br>• ማቀድ፣ ማስተማርና መገምገም ይችላሉ፡፡ | 4.1. የሂሳብ ትምህርት እቅድ አስፈላጊነትና አስተቃቀድ<br><br>4.2. ማቀድና ማስተማር | | - የእቅድ አስፈላጊነት መጠየቅና ማወያየት ማስረዳት<br>- የክፍለ ጊዜ ትምህርት እቅድ (Lesson Plan) ፎርማትን ማሳየትና እንዴት እንደሚታቀድ ማሳየት<br>- በቡድን ማደራጀትና ከእያንዳንዱ ይዘት ርዕስ በመምረጥ እንዲያቅዱና ትምህርት በክፍል ውስጥ በእረስ በርስ መማማር እንዲያቀርቡ ማድረግና መገምገም፡፡ | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- የእቅድ ፎርማት<br>- የቅድመ ሂሳብ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች | - ጥያቄዎች መተየቅ<br>- የቡድን ሥራቸውን መከታተል<br>- የትምህርት አዘገጃጀት ና አቀራረባቸ ውን በማየት መገምገም<br>- ሙከራ መስጠት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መርሀ ትምህርት | • በቅድመ መደበኛ ትምሀርት መርሀ-ትምሀርት የቅድመ ሂሳብ ይዘቶች ይረዳሉ | 5.1. በቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ትምህርት የቅድመ ሂሳብ ትምህርት አላማዎች<br>5.2. በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት የቅድመ ሂሳብ ትምህርት ዓላማዎች | | - በቅድመ መደበኛ መርሀ-ትምሀርት በየእድሜው ለቅድመ ሂሳብ የተቀመጡትን ዓላማዎችና ይዘቶች በመመርመር ለየይዘቶቹ የተቀመጡትን ከዕድሜ አንጻር አውጥተው እንዲያስቀምጡ ማድረግና በተመረጡ ይዘቶች ላይ ትምህርት እንዲያዘጋጁ በማድረግ ማስተዋወቅ | - የቅድመ መደበኛ ትምሀርት መርሀ ትምሀርት | -በመርሀ ትምሀርት ላይ የተሰጣቸውን ሥራ እንዴት እንደሰሩት ማየትና መገምገም |

## 12.የሙዚቃ ትምህርት

ለኮርሱ የተፈቀደው ጊዜ በሳምንት 2 ፔሬድ

አጠቃላይ ዓላማዎች

ይህን ኮርስ ካጠናቀቁ በኂላ እጩ መምህራን፡-

- የሙዚቃን ጽንሰ ሀሳብ ይረዳሉ
- የሙዚቃ ትምህርት አስፈላጊነትትን ይገነዘባሉ
- ከልደት እስከ ስድስት ኣመት እድሜ የሙዚቃ ስሜት መዳበር ሂደትን ይረዳሉ
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤትሙዚቃ ትምህርት ይዘቶችን ይገነዘባሉ
- መዝሙርን የማዘጋጀት ደረጃዎችን ይረዳሉ ለሕጻናት የሚሆኑ መዝሙሮችን መምረጥና ማቅረብ ይችላሉ።

<u>**የኮርሱ አይነቶች**</u>

1. የሙዚቃ ምንነትና አስፈላጊነት
   1.1 ሙዚቃ ምንድነው?
   1.2 የሙዚቃ አስፈላጊነት

   1.3 የድምፅ ዓይነቶችና ሙዚቃን የሚፈጥሩ ነገሮች
2. የሙዚቃ ንድፈ ሀሳቦች
   2.1 ሶልፌጅ የሙዚቃአፃፃፍና አነባበብ
   2.2 የሙዚቃ አዘማመርና አጻጻፍ
   2.3 መሰረታዊ ምቶች
3. የሙዚቃ መሳሪያዎች
   3.1 ዘመናዊ (ዓለም አቀፋዊ)
   3.2 ባህላዊ

4. የሙዚቃ ትምህርት በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት
   4.1 ሙዚቃ ስሜት መዳበር ከልደት እስከ ስድስት ዓመት

   4.2 በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ሙዚቃን የማስተማር ኣላማዎች

   4.3 የሙዚቃ ትምህርት ዋና ዋና ይዘቶች

   - ማዳመጥ
   - መዘመር
   - ሙዚቃዊ እንቅስቃሴ
   - የሙዚቃ መሳሪያዎችን ማስተዋወቅ

   4.3 የሕፃናት መዝሙሮች

   4.3.1መዝሙሮችን መዘመር

   4.3.1 የሕፃናት መዝሙሮችን ማዘጋጀት
   4.3.2 መዝሙሮችን የማስጠናትና የማዘመር ዘዴ
   4.3.3 የቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ትምህርት
5. የሙዚቃ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

5.1 የሙዚቃ መርጃ መሳሪያዎች፡-

# የሙዚቃ ትምህርት

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የሙዚቃ ምንነትና አስፈላጊነት | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• የሙዚቃን ምንነት ይረዳሉ<br>• የሙዚቃን አስፈላጊነት በሕብረተሰብ ውስጥ ያለውን ሚና ይረዳሉ | 1.1ሙዚቃ ምንድነው?<br>1.2. የሙዚቃ አስፈላጊነት<br>1.3. የድምጽ አይነቶችና ሙዚቃን የሚፈጥሩ ነገርች | 3 | - ሙዚቃ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ ከልምዳቸው እንዲመለሱ ማድረግና በሙዚቃ ምንነት ላይ ማወያየት ማስረዳት<br>- ለሰው ልጅ ሙዚቃ ስለሚሰጠው ጥቅም በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ በህብረተሰብ ሙዚቃ ያለውን ቦታና አስፈላጊነት ማስረዳት<br>- የተለያዩ ድምጽ የሚሰጡ ነገሮችን በማቅረብ ድምጽ እንዲያዳምጡ ማድረግ ሙዚቃዊ ድምጽን ሊፈጥሩ ስለሚችሉ ነገሮች መጠየቅ ማወያየትና ማስረዳት | - የሙዚቃ የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- የሙዚቃ መሳሪያ ባህላዊ (ክራር ከበሮ…)<br>- የሙዚቃ መሳሪያዎች ድምጽ የሚሰጡ የተለያዩ ነገሮች | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- ጥያቄዎች መተየቅ<br>- የቡድን ስራ ውጤታቸ ውን መከታተል<br>- ጥያቄዎች መጠየቅ ሙከራ መስጠት |
| 2 | የሙዚቃ ንድፈ ሀሳብ | • የሙዚቃ አዘማመርና አጻጻፍን ይረዳሉ<br>• መሰረታዊ ምቶችን ይገነዘባሉ | 2.1. ሰልፌጅየሙዚቃ አፃፃፍና አነባበብ<br>2.2 የሙዚቃ አዘማመርና አጻጻፍ<br>2. 3 መሰረታዊ ምቶች | 5 | - ስለሙዚቃ ንድፈ ሀሳብ ማስረዳት፣ መጠየቅ ማወያየት ስለሙዚቃ ሰሌዳ ማጻፊያ ማስረዳት<br>- ስለምቶች መጠየቅ ማወያየትና መሰረታዊ የሚባሉት ምቶች ምን ምን እንደሆኑ በተግባር ማሳየትና በምቱ ያለውን ልዩነት እንዲናገሩ ማበረታታት፡፡ | - የሙዚቃ መሳሪያ<br>- የምት ዱላ | - በተግባር የምቶችን ልዩነት እንዲያሳዩ ማድረግ |
| 3 | የሙዚቃ መሳሪያዎች | • ዓለም አቀፋዊና ባህላዊ የኢትዮጵያ የሙዚቃ | 3.1. ዘመናዊ (ዓለም አቀፋዊ) | 2 | - የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ማሳየትና ስማቸውን ያወቁ እንደሆነ | - የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎች | - ጥያቄዎች መጠየቅ በ2 እ በ3 ላይ |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍል ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መሳሪያዎችን ይለያሉ | 3.2. ባህላዊ | | መጠየቅ ዘመናዊ (ዓለም አቀፋዊ) እና ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ለማሳየት በሁት አይነቶች መካከል ያለውን ልዩነት ማስረዳት | - ኪቦርድ<br>- ክራር<br>- ወዘተ | ሙከራ መስጠት |
| 4 | የሙዚቃ ትምህርት በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን፡-<br>• የሕጻናት የሙዚቃ ስሜት እድገት ይረዳሉ<br><br>• ሙዚቃን ሕጻናት ለምን እንደሚማሩ ይረዳሉ<br><br>• በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ለሕጻናት ሊቀርቡ የሚችሉ የሙዚቃ ትምህርትይዘቶችን ይረዳሉ | 4.1 የሙዚቃ ስሜት ዕድገት ከልደት እስከ ስድስት ዓመት<br><br>4.2.ሙዚቃን የማስተማር ዓላማዎች<br><br>4.3. የሙዚቃ ትምህርት ዋና ዋና ይዘቶች<br>• ማዳመጥ<br>• መዘመር<br>• ሙዚቃዊ | 3<br><br>2<br><br>10 | - ሕጻናት ሙዚቃዊ ድምጽን መቼ ነው መስማት የሚሰምሩት? ብሎ በመጠየቅ መወያየት<br>- ስለሙዚቃ ስሜት መዳበር ማስረዳትና በዕለት ተዕለት ሕጻናት ላይ ከሚያዩት ጋር በማወዳደር እንዲወያዩ በቡድን የክፍል ሥራ መስጥትና ማዳመጥ ማስረዳትና አቅጣጫ ማስያዝ<br>- የሙዚቃ ትምህርት ዓላማዎችን ማስረዳት ማወያየትና ስለተፈጻሚነታቸው ከልምዳቸው እንዲናገሩ ማድረግ<br>- ከዓላዎች አንጻር ምን አይነት ይዘቶች ሊኖሩ ይገባቸዋል? በማት መጠየቅና ከዓላማዎች አንጻር ይዘቶቹን ሊያስቀምጡ እንዲችሉ በቡድን እንዲወያዩ ዕድሉን መስጠት<br>- ስለእያንዳንዱ ይዘት በቅደም ተከተል ከዓላዎች ጋር በማገናዘብ ማስረዳት<br>- እያንዳንዱን ይዘት ከዕድሜ ጋር በማገናዘብ እንዲረዱ ማድረግና የማስተማር ዘዴዎችን ማስረዳት | - የማስተማሪያ ጽሑፍ<br><br>- የሙዚቃ መሳሪያዎች<br><br>- የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>- ኪቦርድ<br><br>- የሙዚቃ መሳሪያዎች<br><br>- የማስተማሪያ ጽሑፍ | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br><br>- የቡድን ሥራቸውን መከታተልና መገምገም<br>-<br>-<br>-<br>- በተፈጻሚነታቸው ላይ የሚያቀርቡትን ሀሳብ በማዳመጥ መገምገም<br>- ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- የቡድን ስራ መከታተል ሙከራ መስጠት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • ለሕጻናት ይዘቶቹን የማቅረብ ችሎታም ይኖራቸዋል፡፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ<br><br>• የሕጻናት መዝሙሮችን ይለማመዳሉ መዘመርም ይችላሉ<br>• የመዝሙር ግጥሞችን ማዘጋጀትና ከዜማ ጋር ማቀናጀትን ይለማመዳሉ<br>• መዝሙሮችን ለሕጻናት ማስጠናትና ማዘመር ይችላሉ፡- | እንቅስቃሴ<br>• የሙዚቃ መሳሪያዎችን ማስተዋወቅ<br><br>4.4. የሕጻናት መዝሙሮች<br><br>4.4.1 መዝሙሮችን መዘመር<br><br>4.4.2. የሕጻናት መዝሙሮችን ማዘጋጀት<br><br>4.4.3. መዝሙሮችን የማስጠናት የማዘመር ዘዴዎች<br><br>4.4.4. የቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ትምህርት | 10<br><br>2 | - የሕጻናት መዝሙሮችን በቡድን መርጠው በማዘጋጀት እንዲያቀርቡ ማድረግ መገምገም<br>- መዝሙሮችን ማዘመር ማለማመድ ከሕጻናት ጋር የሚዘምሯቸውን እንዲያውቁ ማድረግ<br>- መዝሙሮችን ማዘመር ማለማመድ ከሕጻናት ጋር የሚዘምሯቸውን እንዲያውቁ ማድረግ<br>- ሕጻናትን መዝሙሮችን የማስጠናት የማዘመር ዘዴዎችን ማስረዳትና ማወያየት<br>- በመርሀ ትምህርቱ ያሉትን መዝሙሮች መርጠው በዕርስ በርስ መማማር ትምህርት አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ማድረግና መገምገም | - የመዝሙር ኦዲዮ ሪከርደር<br><br>- ኦዲዮ ሪከርደር<br>- መዝሙሮቹን ሊያጅቡ የሚችሉ መርጃ መሳሪያዎች<br>• ማጨብጨብ<br>• ከበሮ<br>• ኪቦርድ<br>• ሪትምስቲክ<br>• ጸናጽል (ማራካሽ)<br>• ደውሎች | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- የቡድን ሥራ ውጤታቸውን መከታተል |
| 5 | የሙዚቃ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች | • ለሙዚቃ ትምህርት የሚያስፈልጉ መርጃ መሳሪያዎችን ያውቃሉ | 5.1.መርጃ መሳሪያዎች<br><br>• ከበሮ<br>• ማራካሻ<br>• ጽናጽል<br>• የድምጽ ሳጥን | 3 | - ለሙዚቃ ትምህርት የሚያገለግሉ መርጃ መሳሪያዎችን ማሳየት<br>- ከቀረቡት ውስጥ አንድ መርጠው በቡድን መዝሙር እንዲያቀርቡ በማድረግ መሳሪያዎችን ማስተዋወቅ፡፡ | - የሙዚቃ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች | - በመርሀ ትምህርት ላይ የተሰጣቸውን ሥራ እንዴት እንደሰሩት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | • የምት ዱባ<br>• ትሪያንግል<br>• ማጨብጨቢያ<br>• የመዘመሪያ ሥዕሎት<br>• ትንሽ ትንሽ ወፎች፣ ተረት፣ ተረት | | | | ማየትና መገምገም |

## 13.የሰውነትማጎልመሻ ትምህርት

ለኮርሱ የተፈቀደው ጊዜ በሳምንት 2

የኮርሱ አጠቃላይ ዓላማዎች

ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን

- ስለሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ትርጉምና አስፈላጊነት ይረዳሉ
- ከ3 - 6 ዓመት ያሉ ሕጻናትን የአካል መዳበር ባህርይ ይገነዘባሉ
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ያለውን ዓላማ ይገነዘባሉ
- የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርትን ይዘቶች ያውቃሉ አቅደው ማስተማር ይችላሉ
- የሰውነት ማጎልመሻ እንቅስቃሴዎችን በመለማመድ ሕጻናትን ለማስተማር የሚያስችላቸውን ክህሎት ያዳብራሉ፡፡

**የኮርሱ ይዘቶች**

1. የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት

    2.1 የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ትርጉም
    2.2 የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት አስፈላጊነት

2. የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት በአጸደ ሕጻናት

    2.1. የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት በሕጻናት መዳበር ላይ የሚጫወተው ሚና
    2.2 የአካል መዳበር 3 — 6 ዓመት
    2.3 ስፖርት ባዮሎጂ
    2.4 የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ዓላማ
    2.5 የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ይዘቶች
    2.6 የሰውነት ማጎልመሻን የማስተማሪያ ዘዴዎች
    2.7 የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት
    2.8 ተግባራዊ እንቅስቃሴ
        2.8.1 አትሌቲክስ (ሩውዝ)
        2.8.2 ጂምናስቲክ
        2.8.3 ልዩ ልዩ ጨዋታዎች
        2.8.4 ትልልቅ ጨዋታዎች (ሜጀር ጌምስ)
    2.9 በቅድመ መደበኛ ስርኣተ ትምህርት የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ይዘቶች

# የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍል ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ትርጉምን ይረዳሉ<br>• የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት አስፈላጊነቶችን መጥቀስ ይችላሉ | 2.1. የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ትርጉም<br>2.2. የሰውት ማጎልመሻ ትምህርት አስፈላጊነት | 1<br>2 | - የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ምን እንደሆነ መጠየቅና ማወያየት ማስረዳት<br>- የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርትን አስፈላጊነት መጠየቅ ከዕለት ተዕለት ኑሮአቸው ጋር በማገናዘብ እንዲናገሩ ማነቃቃት በምሳሌዎች ማስረዳት | - | |
| 2 | የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት በአፀደ ሕጻናት | • የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርትበሕፃናት ሁለንተናዊ መዳበር የሚጫወተውን ሚና ይረዳሉ<br>• የሰውነት ማጎልመሻትምህርትዓላማናይዘቶችን ይረዳሉ | 2.1 የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት በሕጻናት መዳበር ላይ የሚጫወተው ሚና<br>2.2. የአካል መዳበር 3 - 6 ዓመት<br>2.3. ስፖርት ባዮሎጂ<br>2.4. የሰውነት ማጎልሻ ትምህርት ዓላማ<br>2.5. የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ይዘቶች<br>• መሰረታዊ | 10 | - የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት በሕጻናት አካል፣ አእምሮ፣ ማህበራዊ ኑሮ፣ እና ስሜት መዳበር የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በቡድን በመወያየት መልሳቸውን እንዲያንጸባርቁ ማድረግና ተገቢውን አቅጣጫ ማስያዝ<br>- የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ዓላማን ማስረዳትና ማወያየት<br>- ዓላማውን ለመፈጸም በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ሊከናወኑ ስለሚገባቸው ነገሮች (ይዘቶች) መጠየቅና ማወያየት በቅደም ተከተል | - የማስተማሪያ ጽሑፍ | - ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- የቡድን ዕብረቃቸ ውን ማየት<br>- ሙከራ |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍል ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርትን የማስተማሪያዘዴዎችን ይገነዘባሉ<br><br>• የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርትን ዕቅድ ዘገጃጀት ይገነዘባሉ | እንቅስቃሴዎች<br>• ጅምናስቲኮች<br>• ጨዋታዎች<br>• ሙዚቃዊ እንቅስቃሴ<br><br>2.6. የሰውነት ማጎልመሻን የማስተማሪያ ዘዴዎች<br><br>2.7. የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀ | 2<br><br>4 | ማስረዳት ከዓላማው ጋር እንዲያገናዝቡ ማድረግ፡-<br>- ስለማስተማሪያ ዘዴዎች የሚያውቁትን እንዲናገሩ መጠየቅና ማበረታታት በሰውነት ማጎልመሻ ትምህርትና በሌሎች ትምህርቶች መካከል ያውን ልዩነት ማስረዳት<br>- ለሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ሊጠቀሙባቸው የሚገቡ ዘዴዎችን ከሕጻናት መዳበር አንጻር ደረጃ በደረጃ ማስረዳት በተግባር ማሳየት<br>- የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት እቅድ ፎርማትን ማሳየትና እንዴት እንደሚታቀድ ማሳየት<br>- በቡድን መከፋፈልና የቤት ስራ መስጠት መርሀ ትምህርቱን በመጠቀም እቅድ እንዲያዘጋጁና በርስ በርስ መማማር ትምህርት እንዲያቀርቡ ማድረግና መገምገም፡-<br>- በቡድን ውስጥ ያሉት አባላት በዝግጅቱ የነበራቸውን ሚና በመጠየቅ | - መሰረታዊ እንቅስቃሴዎችን የሚያሳይ ቻርት<br><br>የማስተማሪያ ጽሑፍ<br><br>ለሰውነት ማጎልመሻ የሚያስፈልጉ መርጃ መሳሪያዎች | መስጠት<br><br>- ጥያቄዎች መጠየቅ<br>- ሙከራ መስጠት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍል ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ተሳትፎአቸውን ማረጋገጥ | | |
| | | • ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን በመስራት የራሳቸውን አካል መዳበርና ቅልጥፍና ያሻሽላሉ<br>• እንቅስቃሴዎችን በመለማመድ ባህሪአቸውን ይረዳሉ ሕጻናትን ደረጃቸውን ጠብቀው እንቅስቃሴ የማሰራት ችሎታ ይኖራቸዋል፡ | 2.8. ተግባራዊ እንቅስቃሴ<br>2.8.1. አትሌቲክስ<br>• ሩጫ<br>• ውርወራ<br>• ዝላይ<br>2.8.2. ጂምናስቲክ | 3<br>5 | - ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን ደረጃ በደረጃ ማሰራትና የእያንዳንዱን እንቅስቃሴ ለአካል መዳበር የሚያደርገውን አስተዋጽኦ እንዲረዱ ማድረግ | | |
| | | .ልዩልዩ ጨዋታዎችን<br>በመጫወት ለሕፃናት ማቅረብ የሚገባቸውን ጨዋታዊ እንቅስቃሴ ይረዳሉ | 2.8.3. ልዩ ልዩ ጨዋታዎች<br>• በመራመድ<br>• በመሮጥ<br>• በመወርወር<br>• በመቅለብ<br>• በመዝለል<br>2.8.4. ትልልቅ ጨዋታዎች (ሚጀር ጌምስ)<br>• የእጅ ኳስ<br>• መሰረታዊ ሕጎችና ስርዓት<br>• የመረብ ኳስ ጨዋታ<br>• መሰረታዊ ሕጎችና ስርዓት<br>• የቡድን ጨዋታ | 10 | -የሚያውቁአቸውንልዩልዩ ጨዋታዎችን በማቅረብ እንዲጫወቱ ማድረግ<br>-ከመሰረታዊ ዕንቅስቃሴዎች ጋር የተያያዙ ጨዋታዎችን ማጫዋትና ለሕፃናት እንዴት ሊያቀርቡአቸው እንደሚችሉ ማስረዳትና ማሳየት<br>-እያንዳንዱ ጨዋታለአካል መዳበር የሚያበረክተውን ስተዋፅኦ መጠየቅና ከተግባራዊ እንቅስቃሴ በኂላ እንዲፅፉ ማድረግና ግንዛቤአቸውን ማስፋት | የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>ለእንቅስቃሴዎች የሚሆኑ መርጃ መሳሪያዎች | ተግባራዊ ስራዎቻቸውን ማየትና መገምገም |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማርያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2.9. በቅድመ መደበኛ ስርዓተ ትምህርት የሰውት ማጎልመሻ ትምህርት ተግባራት | 5 | የቅድመ መደበኛ ስርዓተ ትምህርትን በመመልከት የሰውነት ማጎልመሻ ተግባራትን ከዓላማ አንፃር እንዲገመግሙ ማድረግና በተግባራቱ ላይ ተገቢውን መረዳት ማስጨበጥ | | የተግባር ሥራ ፈተና መስጠት |

## 14. መሠረታዊ የኮምፒውተር ትምህርት

ለኮርሱ የተፈቀደ ጊዜ በሳምንት -2

የኮርሱ አጠቃላይ ኣላማዎች

ከዚህ ኮርስ በኋላ እጩ መምህራን

- ስለኮምፕዩተር ምንነት ግንዛቤ ይኖራቸዋል
- የኮምፒዩተር መሠረታዊ አካላትን ይለያሉ
- የኮምፒዩተር ፕሮግራሞችን (Software) መለየት ይችላሉ
- ስለ ዊንዶ አጠቃቀም መሠረታዊ እውቀት ይኖራቸዋል

### የኮርሱ ይዘቶች

1. የኮምፒዩተር ስርዓት
   - 1.1 የኮምፒውተር የሚታዩ አካላት 1.1.1 መርጃ ማስገቢያ ክፍሎት (Input Units)
     - 1.1.2 መረጃ ማስወጫ ክፍሎት (Out put obits) 1.1.3 ፕሮሴሰር
     - 1.1.4 ውጨአዊ መርጃ ማከማቻ ክፍል
   - 1.2 ዋና ዋና የሶፍት ዌር አካላት 1.2.1 ሲስተም ሶፍትዌር 1.2.2 አፕሊኬሽን ሶፍትዌር
   - 1.3 የኮምፒዩተር ቫይረስ 1.3.1 የኮምፒዩተር ቫይረስ መከላከያ መንገዶች
   - 1.4 ኢንተርኔት 1.4.1 የኢንተርኔት አገልግሎቶች

2 በኦፕሬቲንግ ሲስተም
   - 2.1. መግቢያ 2.1.1. የኦፕሬቲንግ ሲስተም ጥቅሞች
   - 2.2. ኮምፒዩተር ማስነሳት 2.2.1. ማውዝና ኪቦርድ መጠቀም 2.2.2. የዊንዳው ዲስክቶፕ ክፍሎች
   - 2.3 ዊንዶው ላይ መስራት 2.3.1 የዊንዶው ክፍሎች 2.3. 2 ዊንዶው መክፈትና መዝጋት
     - 2.3.3 ፕሮግራም መክፈትና መዝጋት 2.3.4 የተከፈቱ ፕሮግራሞችን እየለዋወጡ ማየት
   - 2.4 የዲያሎግ ቦክስ ክፍሎች
   - 2.5 ፋይሎችን እና ፎልደሮችን በስርዓት አደራጅቶ ማስቀመጥ 2.5.1 ዊንዶው እክስፕሎረር
     - 2.5.2 ፎልደሮችን መፍጠር 2.5.3 ፎልደርና ፋይሎችን ማጥፋት 2.5.4 የፎልደርና ፋይል ስሞችን መቀየር
     - 2.5.5 የጠፉ ፎልደሮችንና ፋይሎችን መመለስ 2.5.6 ፋይሎችና ፎልደሮችን መፈለግ
   - 2.6 ወርድ ፓድ ላይ መስራት 2.6.1 ወርድ ፓድ መክፈትና መዝጋት
     - 2.6.2 ወርድ ፓድ ላይ መፃፍና ማስቀመጥ 2.6.3 ፋይሎችን መክፈት
     - 2.6.4 ፋይሎችን ማስተካከል 2.6.5 ፋይሎችን ማሰማመር
     - 2.6.6 ፋይሎችን ፕሪንት ማድረግ

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍል ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የኮምፒዩተር ስርዓት | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራኑ<br>• ስለኮምፒዩተር ምንነት ግንዛቤ ይኖራቸዋል<br>• ስለኮምፒዩተር አካላት መሰረታዊ ግንዛቤ ይኖራቸዋል<br>• ስለኮምፕዩተር ፕሮግራም (ሶፍትዌር) መሰረታዊ ግንዛቤ ይኖራቸዋል<br>• የኮምፒዩተር ስራ ሊያዛቡ ስለሚችሉ የኮምፒዩተር ቫይረሶች ይረዳሉ መከላከል ይችላሉ | 1.1 የኮምፒዩተር አካላት<br>1.1.1. መርጃ ማስገቢያ ክፍሎች<br>1.1.2. መረጃ ማስወጫ ክፍሎት<br>1.1.3 ፕሮሰሰር<br>1.1.4. ውጫዊ መርጃ ማከማቻ ክፍሎች<br>1.2. ዋና ዋና የሶፍትዌር አካላት<br>1.2.1 አፕሊኬሽን ሶፍትዌር<br>1.2.2. ሲስተም ሶፍትዌር<br>1.3. የኮምፒዩተር ቫይረስ<br>1.3.1. | | ኮምፒዩተርን ማሳየትና ስለጥቅሙና ዘመናዊ መሳሪያነቱ በማስረዳት ለመርዳት ያላቸውን ስሜት መቀስቀስና በቀደም ተከተል (በየተራ) ስለአካላቱ ማሳየትና ማስረዳት<br>ኮምፒዩተር አስነስቶ ስለሲስተምና አፕሊኬሽን ሶፍትዌር ማስረዳት<br>ቫይረሶች የኮምፒውተርን ሥራ | ኮምፒዩተር የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>ኮምፒዩተር የማስተማሪያ ጽሑፍ<br>ኮምፒዩተር የማስተማሪያ | ጥያቄ መጠየቅ እና እያሳዩ እንዲመልሱ በማረግ መገምገም<br>ሙከራ መስጠት<br>ሙከራ መስጠት |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • ስለ ኢንተርኔት አገልግሎት እና ምንነት ሀሳብ ይኖራቸዋል | የኮምፒዩተር ቫይረስ መከላከያ መንገዶች<br><br>1.4. ኢንተርኔት<br><br>1.4.1. የኢንተርኔት አገልግሎት | | እንዴት ሊያዛቡ እንደሚችሉ ማስረዳት መከላከያ መንገዶቹን መጠቆም<br><br>የኢንተርኔትን ምንነት እና ጥቅሞች ማወያየትና ማስረዳት | ጽሑፍ<br><br>ኮምፒዩተር<br><br>የማስተማሪያ ጽሑፍ | ሙከራ መስጠት |
| 2 | ኦፐሬቲንግ ሲስተም | ከዚህ ትምህርት በኋላ እጩ መምህራን<br>• ስለኦፐሬቲንግ ሲስተም ጥቅም ያውቃሉ<br>• ስለኦፐሬቲነግ ሲስተም አጠቃም ግንዛቤ ይኖራቸዋል | 2.1. መግቢያ<br><br>2.1.1. የኮምፒዩተሪንግ ሲስተም ጥቅሞች<br><br>2.1.2. ኮምፒዩተሪንግ<br><br>2.2.1 ማውዝና | | የኮምፕዩተር ጥቅሞችን ማስረዳትና ማሳየት<br><br>ኮምፕዩተር አስነስቶ እንዴት እንደሚሰራ ማሳየት እና እያንዳንዱ እየከፈቱ እንዲለማመዱ በማድረግ | የማስተማሪያ ፅሁፍ | |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • ስለዲያሎግ ቦክስ ጥቅም እና አጠቃቀም ያቃሉ<br>• ፋይሎችን እና | ኪቦርድ መጠቀም<br>2.2.2. የዊንዶው ዲስክቶፕ ክፍሎች<br>2.3. ዊንዶው ላይ መላክ<br>2.3.1. የዊንዶው ክፍሎች<br>2.3.2. ዊንዶው መክፈትና መዝጋት<br>2.3.4. የተከፈተ ፕሮግራም እየለዋወጡ ማየት<br>2.4. ዲያሎግ ቦክስ ክፍሎች<br>2.5. ፋይሎችን እና ፎልደሮችን በስርዓት አደራጅቶ | | ለመጀመሪያ ጊዜ ሁለት ሁለት ሆነው በቡድን እንዲሞክሩ ማድረግ በመቀጠልም ራሳቸውን ችለው ለየብቻ እንዲሞክሩ እድል በመስጠት መከታተል እና መጠበቅ | ኮምፕዩተር<br>• ኮምፒዩተር<br>• የማስተማሪያ | • ግምገማ |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ፎልደሮች ቦታ ቦታ አስይዞ ማስቀመጥ ይችላሉ<br>• ፋይሎችንና ፎልደሮችን ስለመፍጠር ግንዛቤ ይኖራቸዋል በተጨማሪ የማይፈለጉ ፋይሎችን ከኮምፒዩተራቸው ማጥፋትን ያውቃሉ | ማስቀመጥ<br>2.5.1. ዊንዶውኤክስለር<br>2.5.2. ፎልደሮችን መፍጠር<br>2.5.3. ፎልደሮችን እና ፋይል ማጥፋት<br>2.5.4. የፎልደር እና ፋይል ስሞችን መቀየር<br>2.5.5. የተደለ ፋይል እና ፎልደሮችን ማመልከት<br>2.5.6. ፋይሎችን እና ፎልደር መፈለግ<br>2.6. ወርድፓድ | | ፕሪንተር አስነስቶ ዲያሎግ ቦክስ ጥቅምና ስራቸውን እያሳዩ ማስተማርና በግል እንዲሞክሩ ማድረግ<br>ፎልደር እየፈጠሩና እያጠፉ ማሳየት እና ተማሪዎች እንዲሞክሩ ማስደረግ | ጽሑፍ<br>• ኮምፒዩተር የማስተማሪያ ጽሑፍ | • ሙከራ<br>• ግምገማ<br>• ሙከራ |

| ተ.ቁ | ርዕስ | ዓላማ | ይዘት | የክፍል ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ ዘዴዎችና የመምህር አቀራረብ | የመርጃ መሳሪያ | የምዘና ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ላይ መጻፍ<br>2.6.1. ወርድ ፓድ መክፈት እና መዝጋት<br>2.6.2. ወርድ ፓድ መጻፍ እና ማስቀመጥ<br>2.6.3. ፋይሎችን መክፈት<br>2.6.3.1 ፋይልን ማስተካከል<br>2.3.5. ፋይሎችን ማሳመር<br>2.3.6 ፋይሎችን ፕሪንት ማድረግ | | ወርድ ፓድ ከፍቶ አጠቃቀሙን ማስረዳት እና ፋይሎችን ማስቀመጥን ማሳየት ሁለት ሁለት በመቀጠልም በየግል እንዲለማመዱ ማድረግ | • ኮምፒዩተር የማስተማሪያ ጽሑፍ | • የተግባርግምገማ<br>• ሙከራ |

## 15. የመጫወቻና መርጃ መሣሪያዎች

ለኮርሱ የተሰጠው ጊዜ በሳምንት - 2

የኮርሱ አጠቃላይ ዓላማዎች

- የመጫወቻና ማስተማሪያ መሣሪያዎችን አስፈላጊነት ይገነዘባሉ
- የፍሮብልንና የምንቴሶሪን እንዲሁም ሌሎች መሳሪያዎችን አዘገጃጀትና አጠቃቀም ይረዳሉ
- የራሳቸውን ፈጠራ በመጠቀም ከአካባቢ ሊገኝ በሚችል ጥሬ እቃ መሣሪያዎችን የማዘጋጀት ክህሎት ያዳብራሉ
- ከህጻናት ጋር ለሚያከናውኑአቸው ተግባራት የሚያስፈልጓቸውን መሳሪያዎች መለየት ይችላሉ
- መርጃ መሣሪያና መጫወቻዎችን የማዘጋጀት ችሎታ ይኖራቸዋል፡

ማሳሰቢያ፡

1. ከዚህ በታች የተቀመጡት መሣሪያዎች መሰራት ያለባቸውን ለመጠቀም እንጂ እዚህ ብቻ ይበቃሉ ወይም እነዚህ ብቻ ይሰሩ ለማለት እንዳልተዘረዘሩ መገንዘብ ያስፈልጋል
2. መርጃ መሣሪያዎች ለአንድ የተወሰነ ተግባር ብቻ ሳይሆን ለተለያዩ ተግባራት ሊውሉ ስለሚችሉ ይህን ከትኩረት ማስገባት ይገባል፡፡
3. ለኮርሱ ከተወሰነው ጊዜ ጋር በሚጣጣም መልኩ በማቀድ የእጩ መምህራኑን ፈጠራ በመቀስቀስ የተለያዩ መሣሪያዎችን እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይገባል
4. በመርጃ መሣሪያዎች ዝግጅት ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ከሚገበው አንዱና ዋናው ጉዳይ እጩ መምህራን የማምረቻ መሣሪያዎችን በአግባቡ  የመጠቀም ክህሎት እንዲኖራቸው ማድረግና የሰሩአቸውን ናሙናዎች እንደምሳሌ ለመጠቀም ሌሎችን የመስራት ተነሳሽነት እንዲያዳብሩ ማድረግ ላይ ነው፡፡
5. እጩ መምህራን መሣሪያዎችን በጥራት  ማምረት እንዲችሉ ከሕፃናት ባህርይና አቅም ውጪ የሆነ መሳሪያን እንዳያመርቱ  ስለሕጻናት ባህሪ በተለያዩ ኮርሶች ያገኙትን ዕውቀት እንዲጠቀሙ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡
6. ያመረቱአቸው መሣሪያዎች ተገቢነት፣ ጥራት ዘላቂነት ወዘተ ታይቶ ኮርሱ እንደ አንድ የትምህርት ዘርፍ የምዘና ውጤት ሊቀመጥለት ይገባል፡፡

የመጫወቻና መርጃ መሣሪያዎች ናሙና

- አሻንኩሊቶች
- ኳሶች
- ማስኮች (አልባሳት)
- ፐዝሎች (የተለያዩ ናሙናዎች)
- የጫማ፣ የልብሶች ፍሬሞች
- የፍራፍሬ፣ የቤት ቁሳቁስ ሌሎችም
- የአዝእርት የእንሰሳት፣ የአእዋፍ፣ የቅጠል አይነት አልበሞች
- የሥዕል መጽሐፍ
- የፊደል ሰሌዳ
- የፊደል ፐዝሎች
- ተንቀሳቃሽ ፊደላት

- ሻሽ ቦርድና የሻሽ ቦርድ ፊደላትና ሥዕሎች
- የመዳሰስ ሰሌዳዎች (በየደረጃው)
- የተለያዩ ሎቶዎች
- ፓፔት /የጣት ፣የእጅ/
- የክብሪት ቤት (ፊደሎች)
- የቀለም ሰሌዳዎች
- የፊደል ብሎኮች
- የፊደል ቻርት
- የቀለም ቡርሽ (ከአካባቢ ሊገኝ በሚችል ነገር)
- የሥዕል አልበም
- ማጨብጨቢያ (ከፕላው ውድ)
- ፀናፅል
- ሪትም ስቲክ
- የድምጽ ሳጥኖች
- ለመዝሙር ድጋፍ የሚሆኑ ሥዕሎች
- ተቆጣሪ ነገሮች
- የሽመል ቆጠራ ሳጥን
- ተንቀሳቃሽ ቁጥሮች
- የቁጥር ፐዝሎች
- የጂሜትር ቅርፃ ቅርፆች
- ቆጣሪና ተቆጣሪዎች
- ደሚኖስ
- የቁጥር እርከን
- ሮዝ ፎቅ ወዘተ
- አባከስ

## 16.ፕራክቲከም

**ፕራክቲከም አንድ**

ፕራክቲከም አንድ እጩ መምህራን ከሚሰሩበት ቦታ ጋር ማለትም ከአፀደ ሕጻናት ጋር በምልከታ የሚተዋወቁበት ሲሆን በዚህ ስልጠና ከተጀመረ በኋላ ባሉት የመጀመሪያዎች ሶስት ወራት በወር አንድ ቀን በሶስት ወራት 3 ቀናት በአፀደ ሕፃናት ተገኝተው ምልከታ በማድረግ ከተቋሙ ለተሰጡአቸው ጥያቄዎች መልስ በማዘጋጀት ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

የፕራክቲከም አንድ ዓላማ

እጩ መምህራን ከዚህ ልምምድ በኋላ

- የወደፊት ሥራ ቦታቸውን ይተዋወቃሉ
- የአፀደ ሕፃናት የውጭ አደረጃት ይገነዘባሉ
- የአፀደ ሕጻናትን ክፍሎች ስፋትና የውስጥ አደረጃጀት ይረዳሉ
- የአፀደ ሕጻናትን የቀን ውሎ ፕሮግራሞ ቅደም ተከተልና ዓላማ ይረዳሉ
- የሕፃናትንና የመምህራንን ግንኙነት በማስተዋል ሕፃናትን ለማስተማር ሊተኮርበት ስለሚገባው የአቀራረብ ዘዴ ይገነዘባሉ
- ከአፀደ ሕፃናቱ መምህራን ጋር  የልምድ ልውውጥ ይኖራቸዋል

የፕራክቲከም አንድ ይዘት

1. የአፀደ ሕጻናቱን አካባቢ፣ ግቢና ክፍሎች አደረጃጀት መመልከትና በተሰጡአቸው ጥያቄዎች መሰረት ሪፖርት ማዘጋጀትና ማቅረብ
2. አንድ ክፍልን መመልከትና ከመቀበያ ሰዓት እሰከ መሸኛ ድረስ ያሉትን ፕሮግራሞች መከታተልና ሪፖርት ማዘጋጀት
3. ከተመደቡበት ክፍል አንድ ሕፃን መርጦ በመከታተል ሪፖርት ለአማካሪ መምህራቸው ማቅረብ፡፡

**በፕራክቲከም አንድ በእጩ መምህራን የሚመለሱ ጥያቄዎች**

**ተግባር አንድ፡- የአፀደ ሕፃናት አደረጃጀት ምልከታ**

የአፀደ ሕፃናቱን አካባቢ ሁኔታና አጠቃላይ አደረጃጀት በማስተዋልና የሚመለከታቸውን በማነጋገር ሪፖርት አዘጋጁ፡፡

1. አፀደ ሕፃናቱ የሚገኝበት አካባቢ የሕፃናት አስተዳደግና ትምህርት ዓላማን ለማስፈፀም አመቺ ነው ?
2. የአፀደ ሕፃናቱን አመሰረሰረት በተመለከተ/ መቼ በማን ተመሰረተ ተጠሪነቱ ለማን ነው? የመምህራንና ድጋፍ

ሰጪ ሰራተኞች ብዛት፣የትምህርት ደረጃ፣የበጀት ምንጭ

3.የአፀደ ሕፃናቱ ግቢ -ስፋት፣የውስጥ አደረጃጀት

4.የአፀደ ሕፃናቱ ሕንፃ አቀማመጥ ከሥራው አንፃር ሲታይ ምን ይመስላል?

5. አፀደ ሕፃናቱ ስንት የመማሪያክፍሎች አሉት? የክፍሎቹ አመደደብ መሰረቱ ምንድነው?

6. በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ምን ዓይነት መጫወቻዎችና መርጃ መሳሪያዎች ይገኛሉ?ዓይነትና ብዛታቸው በዝርዝር ይገለፅ

7. በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙት መጫወቻዎችና መርጃ መሳሪያዎች አደረጃጀት ምን ይመስላል? የአፀደ ሕፃናትን ዓላማ ከማስፈጸም አንፃር ገምግሙ

8.የመማሪያ ክፍሎች ስፋት ምን ያህል ነው? የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ነው?

9.በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ወንበሮችና ጠረቤዛዎች ከሕፃናት ዕድገት ጋር የተመጣጠኑ ናቸው?መጠናቸው ተገልፆ በስዕል ይቀመጥ፡፡

**ተግባር ሁለት፡-የትምህርት ክፍለ ጊዜ ምልከታ**

የተመደባችሁበትን ክፍል የዕለት ፕሮግራም በመከታተል በሚከተሉት ጥያቄዎች መሰረት ሪፖርት አዘጋጁ

1. የዕለቱ ፕሮግራም ምን ምን አካቷል? የፕሮግራሙን ዝርዝር በማስፈር አብራሩ፣
2. የክፍለ ጊዜው ዕቅድ ዕቅድ ምንምን አካቷል?
3. ከተከታተላችሁት ፕሮግራም አንዱ ላይ በመደገፍ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ
   3.1 በፕሮግራሙ መጀመሪያ የሕፃናትን ሀሳብ ለማሰባሰብ መምህር የተጠቀሙባቸውን ዘዴዎች ጠቁሙ
   3.2 በዕቅድ ላይ የተቀመጠውና በተግባር ሲሰራ የታየው ዓላማና ይዘት ከሕፃናቱ ዕድሜና ችሎታ አንፃር ሲመዘን ምን ያህል ተገቢ ነው?
   3.3 በፕሮግራሙ ሂደት መምህር ሕፃናትን አሳትፈዋል?ስንት ሕፃን ተሳተፈ? ሕፃናትን ለማሳተፍ፣ለማስደሰትና ለማዝናናት፣ የክፍለ ጊዜውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ምን ዓይነት ዘዴዎችን ተጠቀሙ?
   3.4 በፕሮግራሙ ሂደት ጥቅም ላይ ሲውሉ ያያችሁአቸውን መጫወቻዎችና መርጃ መሳሪያዎች በዝርዝር አስቀምጡ፡፡

**ተግባር ሦስት፡-የትምህርት ክፍለ ጊዜ ምልከታ**

1. አፀደ ሕፃናቱ የሚመራበት የድርጅት ዕቅድ አለው?በተግባር እየተተረጎመ ነው?በምሳሌ አስረዱ
2. የሕፃናቱ አስተዳደግና ትምህርት ሂደት የሚገመገምባቸውን ስልቶች በዝርዝር አስቀምጡ
3. በደረሳችሁበት ዕለት አንድ ሕፃን በመምረጥ ከመቀበያ እስከ መሸኛ በመከታተል በፕሮግራሞች ተሳትፎውን፣ከመምህር ከሞግዚቶች ከሕፃናት ጋር በተለያዩ ጊዜአት ያለውን ግንኙነት፣ለጨዋታ ያለውን ዝንባሌ፣ባጠቃላይ የሚገኝበትን ደረጃ በመከታተል ያለውን ጥሩ ጎንና ሊደረግለት የሚገባውን ዕገዛ በመጥቀስ ሪፖርት አቅርቡ፡፡
4. ከዚህ ተግባር ምን ተማራችሁ? በቅደም ተከተል አስቀምጡ፡፡

## ፕራክቲከም ሁለት

ፕራክቲከም ሁለት በመጨረሻው የስልጠና ወር ከማጠቃለያ ፈተና በፊት ለሁለት ተከታታይ ሳምንታት በአፀደ ሕፃናት በመገኘት የማስተማር ልምምድ የሚያደርጉበት ሲሆን ከሁለቱ ሳምንት ውስጥ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ቀናት ነባሩ መምህር ከመቀበያ ሰዓት እስከ መሸኛ ድረስ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በመከታተል ልምድ ይቀስማሉ በመቀጠልም በተማሩት መሠረት እቅድ (Lesson Plan) አዘጋጅተው በመስራት የሚለማመዱበት ጊዜ ነው፡፡በሚሰሩበትጊዜ የሚከታተሏቸው መምህርከማሰልጠኛው በሚሰጣቸው ቅፅ መሰረት የሥራ ሂደታቸውን አይተው ውጤት ያስቀምጣሉ፡፡

የፕራክቲከም ሁለት ዓላማ

- በተመደቡበት አፀደ ሕፃናት የፕሮግራም ትውውቅ ያደርጋሉ
- ለአፀደ ሕፃናት የሚያስፈልጉትን ተግባራት ማቀድ፣ መተግበር እና መገምገም ይችላሉ
- ሕፃናትን ስለማስተማሪያ ዘዴ ያገኙትን ዕውቀት ተግባር ላይ መፈተሽ ይችላሉ

የፕራክቲከም ሁለት ይዘት

1. የሁለት ቀናት ምልከታ ማካሄድ
2. በየዕለቱ ዕቅድ በማዘጋጀት ራስን ችሎ ፕሮግራሞችን መምራት
3. ከአማካሪ መምህራን በሚሰጠው አስተያየት መሠረት በተሻለ መልኩ የማሳደግና የማስተማር ሂደትን ማከናወን፡፡